# የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ

በጣም፡ እናመሰግናለን፡ ወንድም ኔቪል።

አረፍ በሉ።

2 እንዴ እንደተባለው፡ "'ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ፡' ደስ አለኝ፡" መባሉን እምናለሁ።

3 አሁን፡ እዚህ ለተገኛችሁ ሁሉ፡ ቦታ፡ ወይም የመቀመጫ ክፍል ስላልተገኘ፡ እናዝናለን፡ ምናልባት ቀጣይ ሳምንት፡ ስለ ስብሰባው በደንብ እየተሰማ ስለሚሄድ፡ የሚመጡ ሰዎችም ይበዛሉ።

4 ነገር ግን በዚህ ልዩ ጊዜ የምናደርግበት ምክንያት... መንፈስ ቅዱስ ይህ የማስጠንቀቂያ መነሳሳት በልቤ ስላኖረ፡ ይህም፡ "በዚህ ዘመን ያለችው ቤተክርስቲያን ይህ መልእክት መስማት አለባት ነው።" ምክንያቱ፡ በጣም አስደናቂ የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት እንደሆነ አምናለሁ፡ በዚህ ጊዜ ክርስቶስን በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ይገልጠዋልና።

5 ስለዚህ፡ አሳባቸውን ወይም እምነታቸውን መሰረት የሚጥሉበት፡ ከሌላቸው በቀር፡ እምነት ሊኖራቸው አይችልም፡ ወይም የሚያደርጉት ነገር አያውቁትም የት እንደሚሄዱም ማወቅ አይችሉም። ስለዚህ፡ ቅዱሳት መጻሕፍት በመጨረሻው ዘመን፡ ክርስቶስን እና የጊዜውን ሁኔታ ከገለጹልን፡ ፈልገን የት እንዳለን ለመመርመር—አመቺ ይሆንልናል።

6 ቤተ ክርስቲያናችን፡ ትልቅ—ባለመሆኑ እናዝናለን፡ አንድ ቀን እንደሚኖረን ተስፋ እናደርጋለን።

7 የመጨረሻዎቹ አራት ቀናት፡ በተለይም፡ በታሪካዊው—የራዕይ መጽሐፍ ጥናት ላይ፡ ተፈጽመዋል ብዬ ያላሰብኳቸውን ነገሮችን ሁሉ ዳሰሻለሁ። እንደውም፡ ከዚህ **ከሰባት የቤተክርስቲያን ዘመን** በኋላ፡ ምን ማድረግ እንዳለብን—የሚሰማኝ ነገር አለ፡ "እውነተኛይቱ—ቤተ ክርስቲያን እና የውሸት ቤተ ክርስቲያን" በተመለከተ፡ እና ታሪክን እና ቅዱስ ቃልን በመፈተሽ፡ እንደዚህ ያለ ተከታታይ ርዕስ እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ። ከዚህ በፊት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስላለው፡ "እውነተኛው እና ሐሰተኛው የወይን ግንድ፡" በተመለከተ፡ የተጋሁበት ስብከት ነበር። እኛም...

8 ለመቀመጥ የሚሞክሩትን ሰዎች እያሰብኩ ነውና፡ አንዳንድ ወንበሮችን ለማግኘት እንሞክራለን። ክፍሎቹን ከውስጥ፡ እና ከውጭ ለመሙላት፡ ተጨማሪ ወንበሮችን፡ ለመግዛት፡ እንሞክራለን፡ በተጨማሪ፡ በስብሰባው ወቅት ጥቂት ተጨማሪ ሰዎችን ቁጭ ማለት እንዲችሉ ያስፈልጋል።

9 እንግዲህ፡ በዚህ ላይ፡ ስለእነዚህ ነገሮች የምትጨነቁት እያንዳንዳችሁን፡ ዘወትር እንድትመጡ—እኛም እንደምናብራራው—መናገር እፈልጋለሁ። ሌላው እኔ ራሴ አደርጋለሁ ብዬ አልልም፡ ወይም ስለራሴ ሳስበው... [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] ... ቃል አልገባም... [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]... ይህ ታላቅ የመገለጥ መጽሐፍ... [በቴፕ ላይ ባዶ

ቦታ—አርታዒ።]... የሰባቱ የቤተ ክርስትያን ዘመናት። እኔ መክፈት ሰጀምር፡ እግዚአብሔር እራሱ እንዲገልጽልኝ—ሙሉ በሙሉ በርሱ ላይ እታመናለሁ።

10 ሌላውም ተፈጥሯዊው ታሪክ፡ በሚመለከት... እኔ ከማውቃቸው የላቁ የታሪክ ምሁራን የተወሰደ ነው። አሁን ራሱ፡ ወደ አምስት ወይም ስድስት ማብራሪያዎች፡ በጥናት ክፍሌ ውስጥ ደርድሬአቸዋለሁ፡ የሂስሎፕ **ቱ ባቢሎንስ፡ የፎክሰስ ቡክ ኦፍ ማርቲርስ፡** እና ሌሎች ታላላቅ መጻሕፍት፡ እንደ ቅድመ-ኒቅያ ጉባኤ፡ የመሳሰሉ አራት መጻሕፍቶች፡ እያንዳንዳቸው አራት መቶ ገጾች አላቸው። ሌላው የኒቅያ ጉባኤ፡ እና አሉን የምንላቸው ሌሎች ጭምር። ምክንያቱ፡ ከዚህ በመቀጠል፡ በካሴት ከተቀዳ በኋላ፡ ሰባቱ አብያተ ክርስትያናትን በተመለከተ መጽሐፍ እናዘጋጃለን፡ በመጨረሻው ዘመን ውስጥ ስለሆንን፡ በቻልነው፡ ለዓለም ሁሉ እንልከዋለን። በመጨረሻው ዘመን ላይ ነንና።

11 እስካለፈው ምርጫ ድረስ—እስከዚህ ድረስ በልቤ ላይ ጠልቆ አያውቅም፡ ከዚያም የት እንዳለን አይቻለሁ። ከዚያም ሕዝቡን—ለማስጠንቀቅ እና ይህን ለማስቀመጥ፡ መንፈስ ቅዱስ ለእኔ መግለጥ ጀመረ። እንደዚህ ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፡—በበቂ ሁኔታ ማድረግ አልችልም። ቁጭ ብዬ መጽሐፉን ብቻ ከጻፍኩ... ፑልቢት ላይ ወጥቼ፡ በክርስቲያኖች ላይ ያለውን የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሊረዳኝ፡ ወደ እኔ ከመጣ፡ ከዚያም የነገሩ ምሪት ስለማገኘው፡ በካሴት ካስቀዳሁት በኋላ፡ መጽሐፉን ለመጻፍ የበለጠ ችሎታ ይኖረኛል። በርግጥ፡ መጻህፍቶቹ፡ በተወሰነ መልኩ አርትዖት ይደረግባቸዋል፡ ምክንያቱም፡ እዚህ ውስጥ፡ በመጽሐፉ ውስጥ ማስገባት የማንችለውን ነገሮች እናስቀምጣለን። ከዚያም... ለመደጋገም፡ ወይም እኔ ሰፊ ጊዜ እወስዳለሁ። ከዚያም፡ መጽሐፉ ላይ፡ ሁሉም ነገር ይስተካከላል። ነገር ግን፡ ሁሉንም ነገር በተቻለ መጠን፡ በቴፕ ለማግኘት እንሞክራለን።

12 አሁን፡ ካሴቶቹ፡ በእያንዳንዱ ምሽት፡ ሰነ ጽሁፉ እና ሌላው፡ ልጆቹ እዚያው በህንጻው ይሰሩታል።

13 እንግዲህ፡ ስለ እግዚአብሔር ክብር የተቀበልነው አደራ፡ የሰባቱ ቤተክርስትያን መልዕክቶች፡ ወይም—ሰባቱ የቤተክርስትያን ዘመናት፡ ለእንዱ ዘመን፡ አንዳንድ ምሽት ለማድረግ፡ በሰባት ምሽቶች መጨረስ፡ አልችል ይሆናል። ምናልባት፡ ሰኞ ምሽት፡ ኤፌሶን፣ ማክሰኞ ምሽት፡ ሰምርኔስ፣ ረቡዕ ምሽት፡ ጴርጋሞስ፣ ሐሙስ ምሽት፡ ትያጥሮን፣ አርብ ምሽት፡ ሰርዴስ፡ እና ቅዳሜ ምሽት፡ ፊላዴልፊያ፡ እሁድ ጥዋት እና እሑድ ምሽት፡ እኛ የምንኖርበት የቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ ሎዶቅያ። የመጀመሪያውን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፡ ስለ ጸሐፊዎቹ—እና ስለ ታሪክ ተመራማሪዎቹ፡ የዚያን ዘመን መላእክት፡ መ—መልእክቶቹም፡ የቤተክርስቲያኒቱ አጨራረስ፡ እንዴት እስከዚህ ጊዜ ድረስ እንደወረደ።

14 እያንዳንዱ የቅዱስ ቃሉ ትንበያ ከታሪክ ጋር እንዴት አንድ ላይ በትክክል እንደሚጓዝ ማየት፡ አሳቡ በራሱ፡ አስደናቂ ነው። በጣም ስላስገረመኝ፡ ትናንትና፡ አይኔ ማበጡ እስኪታወቀኝ ድረስ፡ እንብቤ ነበር። ወጣሁና ለሚስቴ "እንደዚያ ይሆናል ብዬ አስቤው አላውቅም፡" ብዬ ነገርኳት። እያችሁ? በጣም ድንቅ ነበር!

15 እና አሁን፡ አንዳንድ ጊዜ፡ ቤተክርስቲያንን፡ ለቤተክርስትያን ያለውን መልእክት፡ ሁሉንም በአንድ ሌሊት ላገኘው አልችል ይሆናል። በዚያው ምሽት፡ ካላገኘሁት፡ በሚቀጥለው ቀን ጠዋት በአስር ሰዓት ይሆናል። ሌላው መጥተው ማዳመጥ ለሚፈልጉ ሰዎች፡ በየምሽቱ ማስታወቂያ ይነገራል፡ ምክንያቱ፡ በካሴት ለማስቀመጥ፡ እንሞክራለን። ከዛም ከጠዋት፡ ከአስር ሰአት ጀምሮ፡ እስከ እኩለ ቀን ድረስ፡ በቀን አገልግሎት ይኖረኛል፡ በካሴት መቅዳት ስለሚችሉ፡ የቀሩ መልዕክቶች ሁሉ፡ ለማሳየት እሞክራለሁ። ሌላው...

16 ምንም አይነት የፈውስ አገልግሎት እንደማይኖር አሳውቀናል፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢታዊ ቃል ሥር ለመሰንበት እየተዘጋጀን ስለሆነ ነው። በቅርቡ፡ የፈውስ አገልግሎት አካሂደን ነበርን። ይህ አገልግሎት ካለቀ በኋላ፡ ቦታው ተመልሰን የፈውስ አገልግሎት ይኖረናል።

17 አሁን ግን ሰው ሁሉ እንዲያስታውሰው የምፈልገው፡ ይህን—ግልፅ ማድረግ እፈልጋለሁ፡ አሁን፡ በእዚህ ውስጥ፡ ሁላችንም ሊቆርጠን እና ሊነትተን፡ ታላቅ መንቀጥቀጥ ሊፈጥርብን ይችላል። እኔ ግን ቃሉን ከመሰበክ—በቀር፡ ስለ ሌላው ተጠያቂ አይደለሁም። እንግዲህ፡ ይህ ይታወቅ። ከቃሉ ጋር—በትክክል እወግናለሁ። እንግዲህ በአብዛኛው፡ እነዚህ የቤተክርስቲያን ዘመናት፡ በአንድ ሰው የኃይማኖት ተቋም ላይ ሊንፀባረቁ ይችላሉ። እንዲያ ከሆነም፡ ነገሩን ከባድ ለማድረግ አይደለም። ቅዱሳት መጻሕፍት የተናገሩትን ነገር፡ እና እኔም ስለ እሱ ያለኝን መገለጥ ማስቀመጥ ብቻ—ነው። በዚያ ውስጥ እኔ መሳሳቴን ካሰባችሁ፡ አትያዙብኝ፡ እግዚአብሔር ትክክለኛውን ነገር እንዲያሳየኝ ጸልዩልኝ፡ እኔም መቃናት እፈልጋለሁና።

18 ከዚያም ሌላው ነገር፡ ያለብኝ ኃላፊነት፡ ከግምት በማስገባት—በእንደዚህ ዓይነት ስብሰባ፡ ህዝቡን ማስተማር፡ መንፈስ ቅዱስ በዚህ መድረክ ላይ ስለምናገረው ቃላቶች ተጠያቂ እንደሚያደርገኝ ይታወቅ። ስለዚህ እንዴት በታማኝነት እንደምንቀርብ ታውቃላችሁ። የእኛ፡ ነገር...

19 ይሄኛው ሌላ ቦታ መጠቀም እችል ነበር። ይሁን እንጂ፡ ትምህርት ከመሆኑ ጋር፡ በመድረካችን... በወንጌል አገልግሎት ውስጥ፡ ለብዙ ዘማንት እንደነበረ፡ እያንዳንዳችን የየራሳችን አሳብ—ወይም የመለየት ጸጋ ይኖረናል፡ እና የየራሳችን አብያተ ክርስቲያናት ያስተማሩን፡ እኛም የምናምናቸው ነገሮች፡ እንዲሁም የየራሳችን ቤተ ክርስትያን አለን። እኛ... በሌላ ሰው ቤተክርስቲያን ውስጥ፡ ወይም እንደዚህ ባሉ ሰዎች መካከል ሄጄ፡ ሰዎች ከተማሩት ነገር ተቃራኒ የሆነ ነገር መናገር አልወድም። ለነገሩ፡ አሳቤን በግልጽ ለማስቀመጥ፡ ጥሬአለሁ...

20 አንድ ሰው የካቶሊክ እምነት ተከታይ ከሆነ፡ እና ለመዳን በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሚመረኮዝ ከሆነ፡ ጠፍቷል። ባፕቲስት ከሆነ፡ ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ከተመረኮዘ፡ እሱም ጠፍቷል። ወይም ጴንጤቆስጤ፡ ስለ መዳን በጴንጤቆስጤ ቤተክርስቲያን ላይ ከተመረኮዘ፡ ጠፍቷል። ነገር ግን... የትኛውም ቤተ ክርስቲያን ይሁን! ሰው በቀራንዮ በተሠራው የክርስቶስ ሥራ ላይ በእምነት ላይ የሚያርፍ ከሆነ ግን፡ ድኗል፡ የየትኛው ቤተክርስቲያን እንደሆነ ግድ የለኝም። ምክንያቱም፡ "በእምነት ድናችኋል፡ ይህም በጸጋ ነው።"

21 አሁን፡ አንዳንድ ጊዜ፡ ይህን ስስራ፡ ሳስበው፡ ያረጁ ኮንክሪት ግድግዳ ባሉባት፡ ከብዙ አመታት በፊት የጀመርናት ትንሿ ህንጻዬ፡ ለእኛ የተቀደሰች ቦታ ናት። በአንዱ በኩል፡ ተቀይሮ ማየታችን ደስ እያሰኘንም፡ ደስ እይለንም፡ ምክንያቱም ወለል እንኳን ባልነበራት ጊዜ፡ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መገናኘት የጀመረው በዚህ ነው። አሁን ግን—እርጅቶ የሆነ ነገር እስኪሆን ድረስ ደርሷልና፡ እኛም ግንባታ ውስጥ ነን—ይሄኛው ብሎክ በቸርች ለመሸፈን፡ የግንባታ መርሃ ግብር ይዘናል።

22 አሁን፡ እስከዚያ ድረስ፡ በመልእክትም ሆነ በሌላ፡ ወንድሞችን ሳልጎዳ፡ ጨርሼ፡ ከመስክ ሰመለስ፡ ከዚያም ከዚህ—ከዚህ ከመድረኬ... የራሴን አስተያየት ለመግለጽ፡ መብት አገኛለሁ። ምናልባት "ከዚህ በተለየ መልኩ ተምሬአለሁ፡" የምትሉ ከሆናችሁ ግን፡ እንግዲያውስ... እዚህ ላይ፡ መምጣት የሚፈልጉትን፡ እጋብዛለሁ። እያችሁ? ስፖንሰር ያደረገውም ይሁን፡ ሌላ ነገር የለም፡ ከራሱ ከዚህ ተበርናክል ነው። እና መምጣት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው መምጣት ይችላል። ዝም ብላችሁ ኑ። ስትመጡ መጽሐፍ ቅዱሳችሁ፡ እና እስክርቢቶም ማስታወሻም፡ ይዛችሁ እንድትመጡ እጋብዛችኋለሁ።

23 እንግዲህ፡ ማብራሪያዎቹ እና ሌሎች ነገሮች፡ መጻሕፍቶቹም ይዤ መምጣት አልቻልኩም። ስለዚህ፡ ከታሪክ እና ከማብራሪያ ትንንሽ ማስታወሻዎችን፡ ወዘተ፡ በየጊዜው፡ እየጻፍኩ፡ ይዣለሁ፡ ይህም መጻሕፍቶቹ ይዤ እዚህ በማገላበጥ ፈንታ፡ ከያዝኳቸው ማስታወሻዎች—ማንበብ እንድችል ነው። ቅዱስ ቃል፡ በተመለከተ ግን፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ እጠቀማለሁ። ማብራሪያው ላይ፡ ወይም፡ ታሪኩ ላይ፡ ታሪኩን የተናገረው ምሁር ማን እንደሆነ፡ ወዘተረፈ እዳሰሳለሁ። ከዚያም... የሚመጣው መጽሐፍ፡ በሚሰራበት ሂደት፡ በደንብ አርገን ካሰጻፍነው በኋላ፡ ሌላው ሁሉ፡ ትክክል ሆኖ እናገኘዋለን።

24 አሁን፡ ቶሎ ለመጀመር እና በተቻለ ፍጥነት ለመጨረስ የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን። ከእሁድ እስከ እሁድ፡ የስምንት ቀናት፡ ሰብሰባዎች ይሆናሉ።

25 ዛሬ ጠዋት የራዕይ መፅሐፍ፡ ራዕይ ዮሃንስ 1ኛ ምዕራፍ እጀምራለሁ። ራዕይ ዮሐንስ በሦስት ክፍሎች ተቀምጧል። የመጀመሪያዎቹ ሶስት ምዕራፎች በእነዚህ ስምንት ቀናት ውስጥ የምንመለከተው ነው። አንድ የቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ አንድ ወር ሊወስድብን ይችላል። እንዳልነው ግን፡ ዋና ዋና የተባሉትን ነጥቦችን እንዳሰሳለን። ከዚያ በኋላ መጽሕፉን ስታገኙት፡ በዝርዝር ተጽፎ፡ ይደርሳችኋል።

26 ከዮሐንስ ራዕይ የመጀመርያ ሶስት ምዕራፎች፡ ስለ ቤተክርስትያኒቱ ይዳስሳል፡ ከዛ በኋላ ቤተክርስትያን አትታይም። እስከ መጨረሻ ዘመን ድረስ አናያትም። ከዮሐንስ ራዕይ 1 እስከ 3 ቤተክርስቲያን አለች፡ ራእይ 4 እስከ 19፡ እስራኤል፡ እንደ አገር፡ እና ከ 19 እስከ 22፡ ሁለቱም፡ አንድ ላይ ናቸው። የመጨረሻው ዘመን፡ ወዬዎች እና መቅሰፍቶች፡ ወዘተረፈ! በሦስት ክፍሎች ይመደባሉ። እያችሁ? ቤተ ክርስትያኒቱን የሚዳስሱ፡ እና እኛ እየኖርንበት ያለነውን የቤተ ክርስትያን ዘመን፡ ሦስት ምዕራፎችን እንወስዳለን።

27 አሁን፡ መጀመሪያ አካባቢ፡ ወደ ኋላ ተመልሰን መሰረት መስራት ሰላለብን አሰልቺ ሊመስል ይችላል። የመንፈስ ቅዱስ ስሜትን ለመንካት—የቻልኩትን ሁሉ አድርጌአለሁ፡ ጸልየበታለሁ አጥንቻለሁ፡ ህዝቡ ይሄን ማየት

እንዲችሉ፡ በየትኛው መንገድ ቢዘጋጅ ይሻላል፡ ይህም በመጨረሻ ዘመን ስለሆንን፡ እናንተም፡ በማየታችሁ፡ ብርሃን እንድትሆኑ እና ወደ ክርስቶስ እንድትቀርቡ ነው።

28 እናም ታሪኮቹን ሳጠና፡ ያቺ ቤተክርስትያን እንዴት እንደጀመረች፡ ወደ ኋላ እንዴት እንደተጎተተች፡ ምን እንደተፈጠረ፡ ትንሿ የእግዚአብሔር ዘር በእያንዳንዱ ዘመናት ውስጥ ስትንቀሳቀስ፡ አንድ ስፍራ ላይ፡ ሙሉ በሙሉ፡ እስክትጠፋ ድረስ።

29 ነገ ማታ፡ አንድ ነገር እንጀምራለን፡ አንድ—ቻርት—እንዘጋጃለን፡ ቻርት ሳይሆን፡ ስሌዳ፡ አዘጋጅተን በስሌዳው ማስተማር የምፈልገው ነገር አለኝ። የሰንበት ትምህርት አስተማሪዎች፡ አንዳቸው፡ ጥቁር ስሌዳ አላቸው። ከበስተኋላ ይታየኛል። ከሰራተኞቹ አንዱ፡ ወደዚህ እንዲያመጣልኝ አደርጋለሁ፡ እናንተም እርግጠኞች እንድትሆኑ፡ ስለዳው ላይ እየጻፍኩ አስተምራለሁ። በምናስተምራችሁ ሰዓት፡ እናንተም በማስታወሻ፡ ወይም ሌላ ነገር፡ መሳል ትችላላችሁ።

30 ከመጀመሬ በፊት ግን ይህን መናገር እፈልጋለሁ፦ የቤተክርስቲያንን ዘመን መጀመሪያ፡ ሐዋርያትን፡ እና ትምህርቶቻቸውን፡ እነርሱም ያስተማሩትን፡ እና የመጽሐፍ ቅዱስ መርሆዎች እንድታዩ፡ ከዚያ ቀጥሎም ቤተ ክርስትያኒቱ፡ በሁለተኛው የሐዋርያት ዙር፡ እንዴት መደብዘዝ እንደጀመረች፡ ትክክለኛ፡ እና እውነተኛ ትምህርት እንድታዩ፡ ሦስተኛው ዙር፡ ርቃ መጥፋትዋ፡ አራተኛው ዙር፡ ወደ ሉብታ—ደብዝዛ መጥፋቷ፡ ቤተ ክርስቲያን ሉብ ያለች ቤተ ክርስቲያንን አፈራች።

31 ከዚያም በመንፈስ-የተሞላች ቤተክርስቲያን! ይህን ለእያንዳንዱ ሰው ሃይማኖት በአምላካዊ አክብሮት እናገራለሁ። ከመጀመርያ ጀምሮ፡ እስከዚህ ጊዜ ድረስ፡ እውነተኛዋ ቤተክርስትያን፡ የጴንጤቆስጤ ቤተክርስትያን ናት። እውነት ነው። እግዚአብሔር ይችን ቤተክርስቲያን አቆይቷታል።

32 እና ኢየሱስ የተናገረውን ነገር፡ ብዙ ጊዜ፡ ያስገርመኛል፡ "አንተ ታናሽ መንጋ፡ አትፍራ፡ መንግሥቱን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ በጎ ፈቃድ ነው።" ምን ማለት እንደሆነ ብዙ ጊዜ እጠይቅ ነበር፡ አሁን ግን ገባኝ።

33 ባለፈው ሳምንት በሽሪፖርት፡ ሉዊዚያና ውስጥ ስብሰባ ነበረን፡ በሕይወቴ ውስጥ ከተካፈልኩባቸው ታላላቅ መንፈሳዊ ጉባኤዎች፡ አንዱ ነው። ሽሪፖርት!

34 የ... ሁለት ቀናት የእረፍት ጊዜ ነበረኝ፡ እና የቤተክርስትያኒቱ ዲያቆን፡ ማለቴ ባለአደራ ከሆነው፡ ከወንድም ዉድ ጋር፡ ለአደን፡ ወደ ኬንታኪ ወረድን። ወደ ጫካዎቹ ውስጥ ዘለቅን።

35 የመጀመሪያውን ሽኮኮ መታሁት። ከዛ አንድ ሰው ውሾች ይዞ መጣና፡ "ትንሽ ልጠብቅ፡" አልሁ። እኔም፡ "ሽኮኮዎች ከጉድጓዳቸው ተመልሰው እስኪወጡ ድረስ ልጠብቅ አልሁ። አሁን በዛፎች ውስጥ፡ ወደ ጉድጓዶች፡ ሁሉ ሮጠው ተደብቀዋል።" "እስኪወጡ ድረስ... እዚህ መሽጌ እጠብቃለሁ፡" አልሁ። ምክንያቱ፡ ከባድ ቅዝቃዜ እና፡ ጆሮ የሚያቃጥል ውርጭ ነበር። እንደው፡ እንደምታውቁት፡ ከባድ ንፋስ የተቦረቦረውን ዛፍ—አልፎ ይነፍሳል። "እኔም ሽኮኮቹ እስኪመለሱ ድረስ ብቻ እጠብቃለሁ፡" አልሁ።

36 ገና ቁጭ እንዳልኩ፡ መንፈስ ቅዱስ እንዲህ አለኝ፡ “ተነስተህ፡ ‘ስፖርትስማንስ ሃሎ’ ብለህ ወደምትጠራው ስፍራ ውጣ። በዚያም ከአንተ ጋር እነጋገራለሁ።”

37 እኔም “ስፖርትስማንስ ሃሎ” ብዬ ወደሰየምኩት ስፍራ ወጣሁ። እነዚህ የተቦረቦሩ ዛፎችን፡ እኔ ራሴ ስያሜ የምሰጥበት፡ ምክንያቱ፡ ያለሁበትን ለማወቅ ነው። “ስፖርትስማንስ ሃሎ፡” የተባለበት ምክንያት… ገብቼ አስራ ስድስት ሽኮኮዎች አንድ ዛፍ ላይ ተቀምጠው አገኘሁ፡ የሚበቃኝን ከመታሁ በኋላ፡ ሌሎችን ትቼ፡ ሄድኩ። ስፖርቱም ያ ነው፡ ነገሩም ያ ነበር። በዚህም ምክንያት፡ “ስፖርትስማንስ ሃሎ” ብዬ ሰየምኩት።

38 እርሱም ጠቅሶ፡ “‘ስፖርትስማንስ ሃሎ’ ብለህ የምትጠራው ስፍራ አለኝ።” እሱ እንደጠራው ሳይሆን፡ እኔ እንደጠራሁት።

39 ከዚያም ወደዚያ ወደተቦረቦረው ዛፍ ራስ ላይ ወጥቼ በነጭ የኦክ ዛፍ በታች ተቀመጥሁ፡ ግማሽ ሰዓት ያህል ጠበቅኩት፡ ምንም አልተፈጠረም። ራሴን መሬት ላይ ዘረጋሁና፡ መሬት ላይ ተዘርሬ፡ እጆቼን ዘረጋሁ። ከዚያም ተናገረኝ።

40 እርሱ በተናገረኝ ጊዜ፡ ዛሬ ጠዋት በምናየው በዚህ ቃል፡ ለእኔ የገለጠልኝ ቃላቶች፡ በህይወቴ ሁሉ፡ ከዚህ በፊት አይቼው አላውቅም ነበር።

41 ወደ ሽሪፖርት ሉዚያና፡ በደረስኩ ጊዜ፡ አንድ ሴት ጸጋ ያላት ሴት ናት፡ ስሟ ወ/ት ሽሬደር ትባላለች…

42 ከብዙ አመታት በፊት፡ የጌታ መልአክ እዚህ ወንዝ አጠገብ፡ መጀመሪያ ሲያገኘኝ፡ በዚያም በብርሃን ውስጥ ታየ፡ በዚያም የተናገረው ቃል፡ ከአስራ አንድ አመት በኋላ፡ ወደ ሰብሰባ ሰገባ፡ ይህች ምስኪን ሴት ተነሳች እና በልሳኖች ተናገረች እና ተተረጎመ። መልአኩ የተናገረውን ቃል በቃል ነበር።

43 አሁንም ይህች ሴት ራሷ፡ የነርንበት ሽሪፖርት ውስጥ ወዳለው… ተበርናክል እንደገባሁ፡ ወደ ላይፍ ተበርናክል እንደገባሁ፡ መንፈስ ቅዱስ ወደ ሴቲቱ ወረደና በዚያ በኮረብታው ላይ የተናገረኝን ሁሉ ቃል በቃል ተናገረች። በዚያን ጊዜ ነገሮችን በመገለጥ፡ በትንቢት አስቀድሞ እየተናገረ፡ መንፈስ እየተንቀሳቀሰ ትርጓሜውን ሰጠ፡ በሚቀጥለው ምሽት በስብሰባው ላይ የሚፈጸሙት ነገሮች ሁሉ፡ አንዲት ነገር አልወደቀችም።

44 ከዚያ በፊት፡ አንዲት ሴት በሰብሰባው ላይ ቆመች፡ አንዲት የባፕቲስት ሴት ምን ማድረግ እንደምትችል ሳታውቅ ወደዚያ መጣች። በጉባኤው መካከል ቆማ መንፈስ ቅዱስ ወረደባት፡ ከሽሪፖርት የመጀመሪያው ባፕቲስት ቤተክርስቲያን፡ የመጣች ባፕቲስት ሴት በልሳኖችም መናገር ጀመረች። ምን እንዳደረገችም አላወቀችም። ከዚያም፡ ገና ከመናገሯ በፊት፡ መንፈስ ቅዱስ ፍቺውን ሰጠ፡ እንዲህ ሲል፡ “የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ ‘በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ፡ የሙሴ፡ የኤልያስ እና የክርስቶስ የአገልግሎት መንፈስ፡ በዚህ ተበርናክል ውስጥ ያገለግላል።’” እንዲሁም እንደተባለው፡ ሆነ።

45 ከመሪዲያን፣ ሚሲሲፒ የመጣ አንድ የባፕቲስት ሰውም፡ አንድ ነገር ከማቀዝቀዣው ውስጥ ለመውሰድ፡ እጁን በማቀዝቀዣው እንደዘረጋ፡ የእግዚአብሔርም መንፈስ በእርሱ ላይ ወረደ። ምን እያደረገ እንዳለ ሳያውቅ፡ በልሳን ተናገረ። ምን እያደረገ እንደነበረ… ከማወቁ በፊት፡ መንፈስ ቅዱስ

እንደገና ተናገረው፡ “ወደ ሽሪፖርት፡ ሉዊዚያና ውጣ። ማድረግ ያለብህን ባርያዬ በዚያ ይነግርሃል አለው።”

46 ወደዚያም መጥቶ፡ “ይህ ነገር አልገባኝም፡ ከዚህ በፊት እንዲህ ተከሰቶብኝ አያውቅም፡” አለ። ኡህ፡ ማይ!

የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት በደጅ በደረሰበት በመጨረሻው ዘመን እየኖርን ነው።

47 ታናሿ መንጋ፡ የጴንጤቆስጤዋ ቤተ ክርስትያን ሁሌም ከጥቂቶች ወገን ነበረች። የጴንጤቆስጤ የሃይማኖት ተቋም ማለቴ አይደለም። እንደዛ አላልኩም። ነገር ግን፡ የጴንጤቆስጤ ልምድ ያላቸው ሰዎች! ጴንጤቆስጤ ድርጅት አይደለም። ጴንጤቆስጤ ለተጠማ ሁሉ የሚሰጥ ልምምድ ነው። ካቶሊክ፣ አይሁዳዊ፣ ፕሮሴላይት፣ ሜቶዲስቶች፣ ባፕቲስቶች፣ “የተጠማ ቢኖር፡ ይምጣ።” ግለሰብን የሚዳስስ ልምምድ ነው... እግዚአብሔር በሃይማኖታዊ ተቋም አይሰራም፡ እንዲሁም ከአሕዛብ ጋር በአገር ደረጃ—ወይም በዘር ደረጃ አይሰራም። “የተጠማ ቢኖር፡” በግለሰብ ደረጃ ነው። ነጭ፡ ጥቁር፡ ቢጫ፡ ቡኒም ይሁን፡ ሜቶዲስት፣ ባፕቲስት፣ ፕሮቴስታንት፣ ካቶሊክ፣ የሚፈልግ ሁሉ፡ “ይምጣ፡” ማንም ይሁን። በዚህ መንገድ ስላደረገው በጣም ደስ ይለኛል። እ...

48 በቀደም አንድ ወዳጅ እንዳለ፦ “ዊልያም ብራንሃም ይምጣ ብሎ ስሜን ከሚጠራ፡ ‘ያንን ሲናገር ብሰማ እመርጣለሁ፡’ ምክንያቱ ከአንድ ዊልያም ብራንሃም በላይ ሊኖር ይችላልና። ‘የተጠማ፡’ ሲል ግን፡ ያ እንደሚያደርሰኝ **አውቀዋለሁ**።”

ስለዚህ ሁላችንም ሊሰማን የሚገባው መንገድ በዚህ ነው፡ “የተጠማ ቢኖር፡ ይምጣ።”

49 እንግዲህ፡ ከዓለም ዙርያ ሁሉ የመጡ ብዙ ሰዎች፡ በየሆቴሉ እና በየሞቴሉ እየጠበቁ እንዳሉ አውቃለሁ። አያችሁ? እነዚህን ቀጠሮዎች የሚጠብቁ፡ ከአየርላንድ እና ከተለያዩ ቦታዎች የመጡ ሰዎች እዚህ አሉ። አሁን ግን ለዚያ ጊዜ አይኖረኝም። ጊዜዬን ለዚህ መሰጠት አለብኝ፡ ይገባችኋል።

50 ከእነዚህ ጉዞዎች ስመለስ፡ በአብዛኛውን ጊዜ—የሚገለገል ሰው ይጠብቀኛል፡ ምክንያቱ ቀጠሮን ይጠብቃሉና። አሁን ግን በዚህ ምክንያት እንዲመለሱ ማድረግ አለብን።

51 መጽሐፉ ላይ ከመጀመራችን በፊት፡ አንድ ነገር ብቻ ልበል። መጀመሪያ የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን ነበረች። ያቺ የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ኃይል ወጥታ የሐዋርያት ሥራን ጻፈች። በሁለተኛው ዙር፡ መንገዳገድ ጀመረች፡ ቤተ ክርስትያን ተራ ሆነች። የሁለተኛው የቤተክርስቲያን ዘመን፡ የለየላት ተራ ሆነች፡ ትንሿ የጰንጠቆስጤ፡ መንፈሳዊት ዘር ግን ቀጠለች። ከዚያም ወደ ጨለማ ዘመን ገባች፡ ወደ ሺ አራት መቶ ዓመታት ያክል፡ የጨለመ ሰደት ውስጥ ገባች። ይህች ትንሿ የጴንጤቆስጤ ዘመን በዚያ ሁሉ ውስጥ አለፈች። እንዴት እንዳመለጠች፡ አትጠይቁኝ። ይህን ማድረግ የሚችለው፡ የእግዚአብሔር እጅ ብቻ ነው።

52 ምክንያቱ፡ ምሰሶ ላይ፡ ቁልቁል ያንጠለጥሏቸዋል። ወንዶችን ጉቶ ላይ በሆዳቸው አስጠግተው—የእንጨት ችንካሮችን፡ በእግሮቻቸው ስርስረው ያጣብቋቸዋል፡ አውሬዎች፡ እና ውሾች፡ ከጀርባ እንዲበሏቸው፡ ያደርጋሉ፡ ሳይሞቱ አንጀታቸውን ይጎተታል። ሴቶችን፡ ጡታችውን በመቀስ፡ ቀኝ ጡታቸውን፡ **እንዲህ** ይቆረጣሉ፡ ደማቸውን ፈሰሶ፡ ህይወታቸው እስኪያልፍ ድረስ ያቆሟቸዋል። ከደረሱ እናቶች ህጻናትን አውጥተው፡ አይኖቻቸው እያየ በውሾች እና በአሳማዎች እንዲበሉ ያደርጋሉ። ክርስትያን ተብየው ነው፡ ኢየሱስ ግን፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፡ "እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ እየመሰላቸው፡ እናንተን የሚገድሉበት ዘመን ይመጣል።" አያችሁ?

53 ያ ነገር እስከ ሌላ ዘመን ድረስ ሾልኮ ተጉዘዋል። ከዚያም በመጨረሻ ወጣች። ከዚያም ቤተ ክርስቲያን በተሃድሶ ስትወጣ እንደተመለከትናት፡ ከዚያ ዘመን፡ እየተለየች፡ እየተለየች በሄደች ቁጥር፡ እስከዚህ እስከ መጨረሻው ዘመን ድረስ ከመንፈሱ እየራቀች፡ ከመንፈሱ እየወጣች በመሄድ እራሳቸውን በማደራጀት ለአውሬው ምስል ሰሩለት።

54 ያ ትሑት መንፈስ ግን አሁንም ኢየሱስ እስኪመጣ ድረስ በሰዎች ልብ ውስጥ ይኖራል። መሆን አለበት። ያንን ልብ በሉ።

55 ታሪኩን እና ያለውን ሁሉ አውጥተን በካርታ እናስፍረዋለን፡ በትክክል እንደዛ እንደነበረም እናሳያችኋለን። እናንተ ራሳችሁ፡ ታሪኩን ወስዳችሁ፡ አንብቡ። መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን እዩት፡ ከዛ በኋላ ታሪክ የሚለውን ደግሞ ተመልከቱ። በትክክል እንዲሁ እንዴት እንደሚገጥም እዩት። አቤት!

56 ሁላችንም ይህንን እንደ ትምህርት ብቻ አንቀበለው፡ ነገር ግን በትሕትና፡ የመንፈስ ቅዱስን ማስጠንቀቂያ በትሕትና እየተቀበልን፡ ቀን እና ሌሊት እንጸልይ። ከመጸለይ የሚያግዳችሁ ነገር አትፍቀዱለት።

57 ወደ ውስጥ ስንዘልቅ፡ የእነዚያን ታላላቅ ሰዎች ህይወት፡ ያኔ እንዴት እንደተሰዋ እንቆፍራለን። ምን ያህል ትንሽ እንደሰራችሁ ታያላችሁ። አንዳንድ ጊዜ በራሴ እንዳፍር ያደርገኛል፡ ሁሉንም ነገር ቀላል ሆኖልናል፡ ለእነርሱ ግን ነገር ሁሉ እጅግ ከባድ ነበረ። ጳውሎስ ዕብራውያን 11፡ "የበግ እና የፍየል ለምድ ለብሰው ዞሩ ተሰቃዩ፡ ተጨነቁ፡ ተቸገሩ፡" "ተቅበዘበዙ" አለ። ምስክርነታችን ከነሱ ጋር ቢመዛዘን የእኛ ምንድነው? በዚያ ፊትስ ምን ይጠቅማል? አሁን'ኮ ሁሉንም ነገር ተመቻችቶልናል።

58 አሁን፡ በአክብሮት፡ መጽሐፉን ከመክፈታችን በፊት፡ የምንችል፡ ሁላችንም፡ ለጸሎት ለአፍታ እንድንቆም እፈልጋለሁ። አሁን በልባችሁ ቅንነት፡ የጸሎትን ቃል... በእግዚአብሔር ፊት አቅርቡ።

59 የሰማይና የምድር ፈጣሪ፡ እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፡ የዘላለም ሕይወት ባለቤት፡ የመልካም እና ፍጹም ስጦታዎች ሁሉ ሰጪ። ጌታ ሆይ፡ በመጀመሪያ፡ ስለ ግድየለሽነታችን፡ ስለ ኃጢአታችን፡ በአንተ ላይ እና እርስ በርስ እና በወዳጆቻችን፡ ስለ ፈጸምናቸው በደሎች ይቅር እንድትለን እንለምንሃለን።

60 ይህች ትንሽ የሰብሰባ ጊዜአችን ነፍሳችንን ለማነጽ ብቻ ሳይሆን፡ ወጥተን ለሌሎች መናገር እስክንችል ድረስ፡ በዚህ መንገድ፡ አብርሆት እና ምሪት የምናገኝበት ይሁን። ወቅቱ ከክርስቶስ ሙሉ አካል ጋር አንድ በመሆን፡ ለመነጠቅ እንደገና የምንዘጋጅበት የመዋጃ ጊዜ ይሁን።

61 እግዚአብሔር አባት ሆይ፡ በራሴ ስሜት አይደለም፡ ባሪያህ እና ሌሎች አገልጋዮች ሁሉ፡ ለዚህ ታላቅ ተግባር በቂ እንዳልሆኑ እናውቃለንና። ብዙ ታላላቅ ሰዎች፡ ይህን ለመግለጥ ሲጥሩ፡ ወይም ታላቁ መገለጥን ለመተረክ፡ ይህን በልባቸው አርገው እንዳለፉ፡ ሰንገነዘብ፡ ከእነሱ ይልቅ፡ እኛ ደካሞች መሆናችንን እናውቃለን። አቤቱ አንተ ግን ብርቱ ነህ።

62 የሰማይ አባት ሆይ፡ በዚህ ጊዜ ልዩ ነገር እንድታደርግ፡ እጸልያለሁ፡ መንፈስ ቅዱስ በልባቸው ሁሉ የበላይ ይሁን። የሚናገሩትን ከንፈሮችን የሚሰሙትን ጆሮዎች ግረዝ። ይህን ሁሉ አልፆ፡ ለአንተ አሳልፈን ከሰጠንህ በኋላ፡ ከዚህ ቤት ደጃፍ እየወጣን፡ እንዲህ ማለት ይሁንልን፡ "ለእኛ በዚህ መሆን መልካም ነበር። በዚያ በተቀመጥንበት መንፈስ ቅዱስ ተናገረን። አሁንም የምሽት ብርሃኖች እያንጸባረቁ ባሉበት በዚህ ጊዜ የቻልነውን ሁሉ ለማድረግ ቆርጠናል። ባርከን፡ ጌታ ሆይ።

63 በዚህ በጉባኤው ወቅት፡ ወንዶች እና ሴቶች ሁሉ፡ እንደገና፡ የጸኑ ይሁኑ። ልሳን ተናጋሪዎችን፡ እና ልሳኖችን ተርጓሚዎችን አስነሳ። የትንቢት ሥጦታዎችን ሥጥ። ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽ፡ ሰባኪዎችን፡ ፓስተሮችን፡ ወንጌላውያንን፡ ሁሉ ሥጥ። ወደ መስክ ወጥተው የከበረውን ወንጌል የሚያሰፉትን ሚሽነሪዎችን አስነሣ። ቃሉ በሄደበት ሁሉ፡ በመልካም መሬት ላይ ይውደቅ፡ በዘመኑ መጨረሻ ላይ እንደሆንን ሰለምናምን፡ መቶ እጥፍ የሚያፈራ ይሁን። ፍጻሜው ቅርብ ነውና።

64 አባት ሆይ፡ በእነዚህ ነገሮች ሁሉ ባርከን። ከሁሉም በላይ፡ ጌታ ሆይ፡ በዚህ ጊዜ፡ እኔን ችግረኛውን፡ እርዳኝ። ስለነዚህ ጉባኤዎች፡ እራሴን ለአንተ ሰሰጥ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም እለምናለሁ። ኣሜን።

[አንዲት እህት ልሳን ተናገረች፡ ሌላ ወንድም ተረጎመ—እርታዒ።]

65 ኢየሱስን ከሞት ያሰነሳው፡ ኃያል አምላክ ሆይ፡ መንፈስህ በመካከላችን እንዲኖር በማወቃችን በጣም ደስተኞች ነን። ሁል ጊዜም እውነተኛ ነው መቼም የውሸት ቃል አይደለም። አሁንም፡ አባት ሆይ፡ ቃልህ ስለ ክብርህ ሲነበብ፡ የበለጠ አረጋግጠው። እንደ ተናገርህ፡ "የሆነ ነገር ይመጣልና፡ ልብ ሁሉ በተጠንቀቅ የተዘጋጀ፡" ይሁን። ምናልባት ህዝቡ አሁን ከሚያደርጉት ነገር ወደ ትክክለኛው መንገድ እንዲመለሱ፡ የመጨረሻ ማሰጠንቀቂያቸውን ይድረሳቸው። ቅዱስ እግዚአብሔር ሆይ፡ በልጅህ፡ በጌታ በኢየሱስ ሰም፡ እናመሰግንሃለን። ኣሜን።

66 አሁን የራዕይ መጽሐፍ፡ ምዕራፍ 1 እንከፍታለን። አሁን፡ በመጀመሪያ፡ የመጀመሪያዎቹን ሦስት የራእይ ቁጥሮችን ማንበብ እፈልጋለሁ።

**እግዚአብሔር ለእርሱ የሰጠው፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ይህ ነው፡ ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ነገር፡ ለባሪያዎቹ ያሳይ ዘንድ፡ ኢየሱስም በመልአኩ ልኮ ለባሪያው ለዮሐንስ አመለከተ፡**

**እርሱም ለእግዚአብሔር ቃልና፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር፡ እንዲሁም... ላየውም ሁሉ መሰከረ።**

## ዘመኑ ቀርቦአልና የሚያነበው፡ የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና፡ በውስጡ የተጻፈውን የሚጠብቁት፡ ብፁዓን ናቸው።

67 አስቀድሜ እንዳልኩት፡ አሁንም፡ ከታሪኮች እና ከተለያዩ ነገሮች በዚህ ውስጥ ስለ መፅሃፉ፡ ትንሽ ማብራሪያ ለመስጠት እንሞክራለን። የጻፍኳቸውን ገፆች እያጣቀስኩ ባያችሁኝ ቁጥር፡ ከማብራሪያዎች እና ከተለያዩ ነገሮች የወሰድኳቸው ማስታዎሻዎች ናቸው።

68 እንግዲህ፡ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ቅዱስ ዮሐንስ ዘመለኮት፡ ለመጪው ትውልድ ጻፈው፡ ጸሐፊው ዮሐንስ ነው (ሀ)። (ለ) ከዘመነ ሐዋርያት እስከ ጌታ መምጣት ድረስ ላለው ዘመን፡ ለሰባቱ የተለያዩ የክርስትና ዘመናት ወደ ሰባቱ መላእክት የተመራ ነው። እና... አሁን፡ ከጌታችን ዕርገት ጀምሮ፡ እስከ ዳግም ምጽአቱ ድረስ፡ እያንዳንዱም ዘመናት በየተራ ይታያሉ። እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ዘመን የየራሳቸው መንፈሳዊ ሁኔታ የሚገልጹ ናቸው። (ሐ) እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ስለ እያንዳንዳቸው በሚነገራቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና መንፈሳዊ ንግግር መታየት ይችላል። መንፈስ ሲናገር፡ እያንዳንዱ ዘመን ራሱን ማሣየት ይችላል። እያንዳንዱ ዘመን እውነተኛውን የክርስቶስ ወይን፡ ልባም ድንግልን ይወልዳል። እንዲሁም እያንዳንዱ ዘመን ተቆርጦ የተዳቀለውን ወይን፡ ሰነፍ ድንግልንም ይወልዳል።

69 ዮሐንስ የመጨረሻ ዘመኑን በኤፌሶን ከተማ እንደ ኖረ በዚያም እንደ ሞተ ይነገራል። ይህ ዮሐንስ ሕይወት ነው፡ የታሪክ ምሁራንም ይስማሙበታል። የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ፡ በጻፈበት ጊዜ፡ በፍጥሞ ደሴት ላይ ነበር። የጻፈው የህይወት ታሪኩ ሳይሆን፡ የወደፊት የክርስቶስ ታሪክ በሚመጡ ዘመናት ነበር። እያችሁ? ትንቢት ነውና። የዮሐንስ ሕይወት አይደለም፡ የክርስቶስ ሕይወት ሳይሆን፡ ስለሚመጣው ዘመን ትንቢት መናገሩ ነው። የራሱ ትንቢታዊ ንግግሮቹ አልነበሩም፡ ነገር ግን፡ ጌታን በትሕትና፡ ከፍ ከፍ የሚያደርግ ነበር። የቅዱስ ዮሐንስ ዘመለኮት መገለጥ ሳይሆን፡ የጌታ የክርስቶስ መገለጥ ነበር።

70 የመጨረሻው የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ነው፡ ነገር ግን የወንጌልን ስርጭት መጀመሪያ እና መጨረሻ ይናገራል። የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራንም ይስማሙበታል።

71 ለሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት የተጻፉት ደብዳቤዎች፡ በትንቢታዊነት፡ ወደፊት ለሚመጡት ዘመናት የተጻፉ ናቸው። ጳውሎስ በዘመኑ ስለነበሩ ስለ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ሕይወትና ክብር ጽፏል። ዮሐንስ ግን ወደፊት ስለሚመጡ ስለ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ሕይወትና ክብር ጻፈ፡ ዮሐንስ ለሰባቱ ፓስተሮች ወይም መልእክተኞች በቀጥታ ሲናገር በእነዚህ ሰባት የተለያዩ መላእክት ሥር ያሉ ክርስቲያኖችን ሁሉ እየተናገረ ነው።

72 አሁን፡ የራዕይ መፅሐፍ፡ ይህንን ከፋፍለን፡ ለዛሬ ጠዋት እና ለዛሬ ማታ እንወስደዋለን። እና አሰራ አንድ ሰዓት፡ ወይም አሰራ አንድ-ተኩል አካባቢ ለመጨረስ እንሞክራለን፡ እንደገና ዛሬ ማታ በሰባት ላይ እንጀምራለን።

73 አሁን የ1ኛው ምዕራፍ ይዘቶች። 1ኛው ቁጥር፡ ስለራሱ—የሚናገር ስለሆነ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ነው። 2ኛው ቁጥር፡ ዮሐንስ ዘመለኮት ባርያው ስለመሆኑ ነው። 3ኛው ቁጥር፡ የተላከው በረከት። ከ4ኛው እስከ 6ኛው ቁጥር፡ ለቤተ ክርስትያን የተሰጠ ሰላምታ። ቁጥር 7፡ አዋጅ። 8ኛው

ቁጥር፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክነት። ከ9ኛው እስከ 20 ቁጥር፡ የፍጥሞ ራእይ።

74 እና፡ እንዲሁም፡ 14ኛው እና 15ኛው ቁጥር የሰብዕናው ሰባት ዘርፍ ክብሩ ይገልጻል። ክርስቶስን በሰባት የሰብዕናው ዘርፍ ማየት፡ አቤት እጅግ ደስ ያሰኛል-... በከበረው ትንሳኤው፡ በሰባት ዘርፍ የሰብዕናው ማንነት።

75 አሁን፡ ርዕሱ ራሱ ባህሪውን ገላጭ ነው።

## የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ፡...

76 የቅዱስ ዮሐንስ ዘመለኮት መገለጥ ሳይሆን፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ነው።

77 በግሪክ ቋንቋ **መገለጥ** የሚል ቃል፡ **አፖካሊፕስ** ይባላል፡ ትርጉሙም "መከፈት" ማለት ነው። እኔም ቃሉን ይዤ እየመረመርኩት ነበር። አፖካሊፕስ፡ ማለት፡ አንድ... የቅርጻ ቅርጽ ሰሪ፡ ታላቅ ሐውልት ሰርቶ፡ በመጋረጃ ሸፍኖታል። ከዚያም ሄዶ ይህን መጋረጃ ቀደደ እና ከመጋረጃው በስተጀርባ ያለውን ገለጠ። አለመሸፈን ማለት ነው።

78 እናም የዚህ መጽሐፍ፡ ዋናው አትኩሮት፡ የኢየሱስ ክርስቶስን አካል መገለጥ አይደለም። በርግጥ፡ ስለ አምላክነቱና ስለ ሰባት ዘርፍ ማንነቱ፡ ስለ ክህነቱ፡ ንጉስ፡ እና የመሳሰሉት፡ እሱ ስላሉት ነገሮች ይናገራል። ነገር ግን ወደፊት በሚመጡ በሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ውስጥ ስለ ሥራዎቹ የወደፊት መገለጥ ነው። አዎን...

79 ጌታችን በምድር በነበረ ጊዜ፡ ደቀ መዛሙርቱ፡ ጠየቁት፡ "ጌታ ሆይ፡ በዚህ ጊዜ መንግሥቱን ለእስራኤል ትመልሳለህን? "

80 ኢየሱስም አለ፡ "ይህን ግዜ ወይም ዘመን ማወቅ ለእናንተ አልተሰጣችሁም።" ማንም አያውቀውምና። "ልጅ እንኳን፡" ሳይቀር፡ "አያውቀውም፡" አላቸው።

81 ከሞተ፡ ከተቀበረ፡ ከተነሣ፡ እና ወደ ክብር ካረገ በኋላ ግን፡ የቤተክርስቲያንን የወደፊት ሁኔታ ከእግዚአብሔር ተሰጠው። ከዚያም ይህን መልእክት፡ እና የመምጣቱ መልእክት፡ ቤተክርስትያኖቹ በዘመናት ሁሉ የሚኖራቸው ሁኔታ ለቤተ ክርስትያን ለማሳየት ተመልሶ መጣ።

82 ከመሞቱ፡ ከመቅበሩና፡ ከትንሣኤው በፊት ሊያደርገው አይቻለውም ነበር፡ ገና አላወቀውም ነበርና። ቅዱስ ቃላት የሚናገሩትን እዚህ አስተውላችኋልን?

## **እግዚአብሔር ለእርሱ** (ለክርስቶስ) **የሰጠው የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ**፡...

83 እግዚአብሔር አባት ለልጁ ለኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥን እንደሰጠው። ኢየሱስም መልእኩን ወደ ዮሐንስ ላከ፡ ይህም ያለፉትን ነገሮች፡ የነበረው፣ ያለው፣ የሚመጣውን ያሳይ ዘንድ ነው። አቤት፡ እንዴት ውብ ተደርጎ ተሰራ!

84 አሁን፡ ዮሐንስ ባየው በሚመጣው ታላቅ ዘመን! ይህ መገለጥ፡ በተለየ መልኩ፡ ለእርሱ፡ በተሰጠው ጊዜ፡ የክርስቶስን ልዩ ዓላማ እንዲያሳይ፡ በየአንዳንዱ ዘመን ምን እንደሚመስል፡ እና ምን እንደሚሆን ለማሳየት ነው። ዛሬ

ጠዋት፡ አሳባችሁን በእውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን ላይ አድርጉ፡ ያልኩት ለዚህ ነው። የእውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን ጅማሬ በበዓለ ሃምሳ ቀን ነው።

85 በማርቲን ሉተር፡ በዌስሊ፡ በካቶሊክ ዘመን ወይም፡ በሌላ ዘመን እንደጀመረች፡ የሚናገር የሃይማኖት ምሁር፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁር፡ ወይም የታሪክ ምሁር በጭራሽ የለም። በበዓለ ሃምሳ ጀመረች። የቤተክርስቲያን ምርቃት ያኔ ነበር። ጅማሬዋ ያ ነበር። ስለዚህ፡ ከማንም ጋር በምታደርጉት ውይይት ላይ፡ በበዓለ ሃምሳ ደጃፍ ላይ ከቆማችሁ፡ ወደ የትም መንቀሳቀስ አይችሉም።

86 ጥንቸልን በሜዳ ላይ እንደማስቀመጥ ነው። ጉድጓድ ባለበት ሁሉ፡ ትቆማላችሁ። መጀመሪያ ወደገባባት ተመሳሳይ ስፍራ መመለስ አለበት።

87 እንግዲህ፡ እንደዛ ነው፡ ማንም ስለ ቤት ክርስቲያን እና ስለ ቤተ ክርስቲያን ዘመናት፡ እና ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራዎች የሚናገር፡ ወደ መጀመርያው፡ ወደ ኦሪጂናሉ መመለስ አለበት። እግዚአብሔር ፍጻሜ የሌለው ሁሉንም የሚችል ስለሆነ፡ ወደዚያ መመለስ አለበት። ስለዚህ፡ ፍጻሜ የሌለው በመሆኑ፡ **እዚህ ጋር** አንድ ነገር አድርጎ፡ **እዚህ ጋር** ያደረገውን የሚጻረር ነገር ማድረግ አይችልም። መጀመሪያ እንዳደረገው በእያንዳንዱ ጊዜም ያኑኑ ማድረግ አለበት።

88 ጴጥሮስም በዚያ ቀን፡ እንደተናገረው... አሕዛብ መንፈስ ቅዱስን እንደ እኛ ከተቀበሉ፡ "እኛ በመጀመሪያ እንደተቀበልነው መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ አይተናቸዋልና፡ ውኃን እንከለክላቸው ዘንድ እንችላለን? " አለ፥

ኢየሱስ፡ በምድር በነበረ ጊዜ፡ እንዲህ ተናግሯልና፡ "አንዱ... "

89 አንዱ መጣና እንዲህ አለው፡ "በፈለግነው ምክንያት፡ ሚስቶቻችንን መፍታት የተፈቀደ ነውን? "

90 ኢየሱስም "ወንድን ያደረገው፡ ሴትን ደግሞ አድርጓልና። በዚህ ምክንያት ሰው... " አለው፡

እርሱም "ሙሴ ግን የፍችዋን ጽሕፈት እንድንሰጣት ፈቀደልን፡" አለው።

ኢየሱስም "ከመጀመሪያው እንዲህ አልነበረም፡" አለው።

91 ወደ መጀመሪያው ተመለሱ። ስለዚህ፡ ስለ ቤተ ክርስቲያን ዘመን የምንነጋገር ከሆነ፡ ማንም ሰው በዘመናት የተናገረውን አሳብ ሁሉ፡ ወደ ጎን ጥለን ወደ መጀመሪያው መመለስ አለብን።

92 ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከየትኛውም መጽሐፍ ውስጥ በጣም ምሳሌአዊ መጽሐፍ ነው። ክርስቶስ ማሕተሙን ያሳረፈበት መጽሐፍ ይህ ብቻ ነው። በበረከት ተጀምሮ በእርግማን ይጠናቀቃል። "የሚያነቡት ብጹአን ናቸው።" እና፡ "ከእርሱ አንዳች የሚያጎድል የተረገመ ነው።"

93 ከመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ክርስቶስ ራሱ የጻፈው፡ ብቸኛው መጽሐፍ ነው። አሥርቱን ትእዛዛትን፡ በጣቱ ጻፈ። ትክክል ነው። አይሁዶችም ይህንኑ አጥብቀው ያዙ። እንዲሁም፡ ዛሬም፡ የራዕይ—መጽሐፍን ነው።

94 መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰይጣን እጅግ የሚጠላው መጽሐፍ፡ የዮሃንስ ራእይን ነው። መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ እና የቅዱስ ቃል ቀነኖናውን በሙሉ

ይጠላል... በተለይ ሁለቱን። በአብዛኛው የሚጠላቸው፡ ግን፡ የዮሃንስ ራእይ፡ እና ዘፍጥረትን ነው። ምክንያቱም፡ ዘፍጥረት አጀማመሩ ይነግረናል። የዮሃንስ ራእይ በመጨረሻው ቀን በእርሱ ላይ የሚሆነውን ይገልፃል። አንድ ሺህ ዓመት ይታሰራልና፡ ከዚያም እርሱ፡ ሐሰተኛው ነቢይ፡ አውሬውም፡ በሕይወት እያሉ፡ ወደ እሳቱ ባሕር፡ ይጣላሉ።

95 የዘፍጥረት መጽሐፍንም—ከትክክለኛነቱ በማያያዝ ያጠቃዋል። ማለት፡ "ትክክል አይደለም፡" በማለት። የሰዎችን አእምሮ ያነሣሣል። ዲያብሎስ የተደበቀበትን ተመልከቱ፡ የዘፍጥረት መጽሐፍ ወይም የራዕይ መጽሐፍ፡ የመጀመሪያውና የመጨረሻው።

96 የራዕይ መፅሐፍ ደግሞ በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት ሌሎች መፅሃፍት በበለጠ ምሳሌአዊ ምልክቶች አሉት። የትንቢት መጽሐፍ ስለሆነ ብዙ ምልክቶች አሉት። የትንቢት መጽሐፍ ነው። ስለዚህ በትንቢታዊ ትምህርት ሊታውቅ ይገባል። ይህ መጽሐፍ ለሁሉም አይደለም። ማንም ሊረዳው የሚችል የለም፡ በጭራሽ። ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው ለተመረጡ ሰዎች ነው። በዘዳግም ላይ፡ እንዲህ ይላል፡ "ምስጢር የሆነውን የ—የ—ጌታ ነው።" ልክ ነው። ለእኛም፡ ለልጆቹ፡ የተሰወሩ ነገሮችን ይገልጥልናልና። ስለዚህ...

97 ሥጋዊ አእምሮ የቅዱሳት መጻሕፍትን ታላቅ ነገር ሊረዳቸው አይችልም፡ ምክንያቱም ለእነርሱ ሞኝነት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ለሚወዱ፡ ለቤተክርስትያን፡ መጽሐፉ ለእነርሱ ተጻፈ። የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ፡ "በኤፌሶን ላለች ቤተ ክርስቲያን፡ ለሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን፡ ለቤተ ክርስቲያን፡ ለአብያተ ክርስቲያናት፡" እያለ ይቀጥላል። የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ለቤተ ክርስቲያኒቱ። ደስ ይላል።

98 በተጨማሪም፡ የቅዱሳን መጻሕፍት መደምደሚያ፡ የሙላት መደምደሚያ መሆኑን አስተውሉ። እና በጂኦግራፊያዊ አቀማመጥም በትክክለኛው ቦታ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ መጨረሻ ላይ ተቀምጧል። የሁሉም ነገር መገለጥ ለሚያነበው እና ለሚሰማው በረከት ሆኖ በዚያ ውስጥ ተቀምጧል፡ ለሚጨምሩ እና ለሚቀንሱም እርግማን ይዟል። ሙሉ የሆነ ቀኖና፡ ኧረ፡ ፍጹም ነው። ምንም ሊጨመርበት አይችልም። አንዳች ሊጨምርበት፡ ወይም ሊያጎድል የሚሞክር ማንም ሰው ቢኖር፡ እግዚአብሔር እጣፈንታውን ከሕይወት መጽሐፍ እንደሚወስድበት ተናግሯል። አያችሁ? አንዳች ከጨመረበት፡ ዕጣ ፈንታውን ከመጽሐፉ ይወስድበታል።

99 ስለዚህም ስለ ጌታችን፡ እርሱ ማን እንደ ሆነ፡ ምን እንደ ሆነ፡ ዘርፈ ብዙ መገለጥ ሰናይ፡ ማንም ሰው በላዩ ላይ አንዳች ቢጨምር ወይም አንዳች ቢወስድበት፡ የውሸት ትንቢት ነው። ብዙዎች በዚያ ጉዳይ የሆነ ነገር እንዳላቸው ለመናገር ሞክረዋል። ነገር ግን ይህ የጌታ ኢየሱስ በቤተክርስቲያኑ ዘመን እና በገዛ ቀኑ የተገለጠው ሙሉ መገለጥ ነው፡ የጌታችን መገለጥ ነው።

100 እንግዲህ—አሁን፡ **መክፈት**፡ በግሪክኛ ቋንቋው፡ ተከድኖ የነበረውን ክርስቶስን፡ በግልጽ-... "መግለጥ" ነው።

አሁን፡ የሚቀጥለው ቁጥር፡ በ2ኛው ቁጥር ውስጥ እናገኘዋለን።

101 1ኛው ቁጥር ክርስቶስን አለመጋረድ፡ ወይም መገለጥ፡ ወይም አለመክደን ነው። አቤት! የመጨረሻው ዘመን እና የጌታ ምጽአት-... ለሐዋርያት፡ እንዴት

ተከድኖባቸው ነበር! እነርሱ ጥያቄውን ጠየቁ፡ አንዱ ብቻውን ግን መገለጡን ለመቀበል ኖረ። ቢሆንም ግን፡ ታሪክ ገና ስላልተሰራ፡ እሱም አልተረዳውም ነበር።

102 ስለዚህ፡ የዚህ መጽሐፍ ታሪክ፡ ወይም—የዚህ መጽሐፍ ይዘት፡ ያኔ በወቅቱ፡ በእስያ ለነበሩ ለሰባቱ አብያተ ክርስትያናት የተጻፈ ነው። ወደ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ተጻፈ። በወቅቱ፡ ከሰባቱ ይልቅ ሌሎች ብዙ አብያተ ክርስትያናትም ነበሩ። እያንዳንዳቸው አብያተ ክርስቲያናት ግን ዘመኑን ተከትላ የምተመጣ ቤተክርስትያን መገለጫ፡ የቤተ ክርስትያኒቱ አስፈላጊነት፡ እና መገለጫ የሚያስረዳ ነገር ነበረባቸው። ለምሳሌ ኤፌሶን፡ የራሷ መገለጫዎች ነበሯት። ሰምርኔስ፣ ጴርጋሞስ፣ እና ሌሎች፣ ፊላደልፊያ፣ አብያተ ክርስቲያናት እያንዳንዳቸው ወደፊት በሚመጣው ዘመን የሚታይ፡ የየራሳቸው መገለጫዎች ነበሯቸው። አቤት! ማየት ብቻ በቻላችሁ…

103 ማንም ሰው የቅዱሳን ቃላት መንፈሳዊ አተገባበር አይቶ—የመንፈስ ምሪት አልባ ናቸው ሊል ይችላልን? የገዛ ሰራችሁ፡ የገዛ አሳባችሁ፡ የሕዝቡ ዓላማ ራሱ፡ እግዚአብሔር እነዚያን ነገሮች እንዴት እንደሚሠራ፡ ሲታዩት፡ መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ምሪት መጻፉን ያረጋግጣል። እናንተ፡ **እዚህ** የምታደርጉት ነገር፡ የሌላው ነገር ጥላ ነው።

104 አብርሃም አንድያ ልጁን ይስሐቅን እንዳቀረበ፡ ከመቶዎች ዓመታት በኋላ፡ ስለ ልጁ የሚሰጠው፡ የእግዚአብሔር ምሳሌ ነበረ። ዮሴፍ እንደ ተሸጠ በወኅኒም ታሰሮ፡ በወንድሞቹ ተጠልቶ በአባቱ ዘንድ እንደ ተወደደ፡ ይህም የኢየሱስ፡ ጥላ ነበረ። ይህ ሰው ዮሴፍ፡ መንፈሱ በርሱ ዘንድ የሰራቸው ነገሮች ሁሉ፡ የክርስቶስ፡ ፍጹም ጥላ ነበረ። ዳዊትም፡ እንዴት ነበር፡ የዳዊት ልጅ በተራራው ላይ እንደወጣ። ዳዊት ንጉሥ ሆኖ ተጥሎ ወደ ተራራው በወጣ ጊዜ፡ ወደ ደብረ ዘይት ተራራ ላይ በወጣ ጊዜ፡ ወደ ኋላ እያየ፡ እንደ ተጠላ ንጉሥ፡ እያለቀሰ ወደ ተራራው ወጣ፡ ከጥቂት መቶ ዓመታት በኋላ፡ የዳዊት ልጅ እንደ ተጣለ ንጉሥ፡ ወደዚያው ኮረብታ ወጥቶ፡ ሰለ ኢየሩሳሌም አለቀሰ። መንፈሱ በጥላ እና በአካል። ኦህ!

105 ታዲያ በዚህ የመጨረሻ ዘመን ታላቋን የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያንን ማየት ትችላላችሁን? እግዚአብሔር በጴንጠቆስጤ ቀን እንዴት እንዳሰመረቃት ይታያችኋልን? ያ መንፈስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሁሉም ዘመናት መቆየት አለበት።

106 እነርሱ ተራ እና ግዴለሽ ሆኑ። የሐይማኖት ተቋም መሰረቱ። ቤተ ክርስትያን እና መንግስትን አንድ አደረጉ፡ በመጨረሻ ፈጸሙት ይህም ለብዙ መቶ ዓመታት ሰደት አስከተለ። ቀጥሎ፡ ተሐድሶ ሆነ፡ ከዚያም ወጡ። በየዓመቱም ከመንፈስ እየወጡ፡ ፍጥረታዊው ግን እየጨመሩ ቀጠሉ፡ ከመንፈስ ወጥተው ተፈጥሯዊው ጨመሩ፡ አሁንም እንደገና ይህን ለማድረግ ዝግጅት ላይ ናቸው። አሁን በቤተክርስትያን መደምደሚያ፡ በመጨረሻ፡ የመዝጊያ ሰዓቶች ደርሰናል። በፊላደልፊያ ውስጥ… ወይም በሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ውስጥ ነን።

107 አሁን፡ 1ኛው ምዕራፍ፡ 1ኛ ቁጥር፡ ለዮሐንስ—አስተዋወቀው። ጸሐፊው ማን ነው? ዮሐንስ። ዮሐንስ። የዮሐንስ መገለጥ አልነበረም፡ እንዳልሆነ እናውቃለን፡ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ነውና። እርሱ ግን፡ ደቀ

መዝሙር ለመሆን የተመረጠ ሰው ነበር። መጽሐፉ ራሱ እርሱ ለሚገልጥለት፡ አስቀድሞ የነበረውን፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ይገልጣል።

108 የተላከው ደግሞ… "ይህም በመልአኩ ልኮ ለዮሐንስ አመለከተ።" መጽሐፍ ቅዱስ መልአኩ ማን እንደሆነ አይናገርም። ስለዚህ መልአኩ ማን እንደ ሆነ እናውቅም። ነብይ እንደሆነ ግን እናውቃለን፡ ምክንያቱም በኋላ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፦ "እኔ ኢየሱስ በቶሎ ሊሆን የሚገባውን እንዲመሰክር መልአኬን ላክሁ፡" አለ።

109 ከዚያም ዮሐንስ ለመልአኩ መስገድ በጀመረ ጊዜ፡ መልአኩም "እንዳታደርገው ተጠንቀቅ፡" አለው። ራእይ 22፡ ይመስለኛል። በኋላም እርሱ "እኔ ከአንተ ጋር ከነቢያት ጋር ባርያ ነኝ፡" ብሎታልና። ኤልያስም ሊሆን ይችላል። ከነቢያት አንዱም ሊሆን ይችላል። ዮሐንስ ግን ሐዋርያ ነበር። ይህ ነቢይ ግን የተላከ።

110 ዮሐንስም ሐዋርያ ሆኖ፡ የቀረውን የመልእክቱን ባሕርይ፡ ተመልከቱ፡ የጻፈው ዮሃንስ እንዳልሆነ አረጋግጡ፡ እንደ ዮሐንስ ዓይነት ተፈጥሮ የለውምና። አንደኛ ዮሐንስ፡ ሁለተኛ ዮሐንስ፡ ወዘተ፡ ይዛችሁ አንብቡ። የዛንም ተፈጥሮ ተመልከቱ፡ ከዚያም የዚህን ባህሪ ደግሞ ተመልከቱ። ዮሐንስ ጸሐፊ እና ሐዋርያ ነበር፡ ይሄኛው ግን የነቢይ መንፈስ ነው። በአጠቃላይ፡ የተለየ ሰው ነው። አያችሁ? የዮሐንስ ጽሑፍ አይደለም። የዮሐንስ መገለጥ አልነበረም። ከእግዚአብሔር ዘንድ ለአብያተ ክርስቲያናት የተሰጠ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ነው። በዚያ ውስጥ… ዮሐንስ ከታቢ፡ ጸሐፊ ብቻ ነበረ፡ መጽሐፉም—ተመሳሳይ ምስክርነት ይገልጻል።

111 የተላከውም፡ ለዮሐንስ አይደለም። የተላከው ለቤተ ክርስትያን ነው። እሺ። ዮሐንስ፡ በዚያ ወቅት፡ የኤፌሶን ቤተክርስትያን ፓስተር ነበረ። አሁን ደግሞ መጽሐፉ የተነገረው ለዮሐንስ… ወይም ለቤተ ክርስቲያን እንጂ፡ ለዮሐንስ አይደለም።

112 አሁን 3ኛው ቁጥር፡ በረከቱን ያውጃል። ስሙት።

**ዘመኑ ቀርቦአልና የሚያነበው፡ የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና፡ በውስጡ የተጻፈውን የሚጠብቁት፡ ብፁዓን ናቸው።**

113 የትኛው ዘመን ነው የቀረበው? እነዚህ ነገሮች የሚፈጸሙበት ዘመን፡ ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ በእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ዘመን የሚጠናቀቅበት ዘመን ነው።

114 እንግዲህ እንዲህ ብሎ የጻፈበት ምክንያት ይህ ነው። እንዲህ'ኮ ማለት ይችል ነበር፡ "እሺ፡ አሁን፡ እሱ… " እርሱንም ደግሞ እየፈለጉት ነበርና፡ ለእርሱም… ተገልጾለት ቢሆን፡ አብያተ ክርስትያናት ልክ ሲጨርሱ፡ ወዲያውኑ እርሱ እንደሚመጣ ለዮሐንስም ይገለጽለት ነበር። ዮሐንስ ያሰበበት መንገድ ነው። እነዚያ አብያተ ክርስቲያናት፡ እንደጨረሱ፡ ይመጣሉ፡ ቢሆን… ወደፊት ሰባት የቤተ ክርስቲያን ረጃጅም ዘመናት እንደሚሆኑ ቢገለጥለት ኖሮ፡ ቢያውቀው ኖሮ፡ ማለት ብዙ ሺህ ዓመታት፡ ወይም ብዙ መቶ ዓመታት፡ እንግዲያውስ ምንም የመጠበቅ ምክንያት አይኖረውም ነበር። የቤተ ክርስቲያናቸውን ዘመን ብቻ ይኖሩ ነበር።

115 ስለዚህም፡ እግዚአብሔር ተናገረ እንጂ፡ አልተገለጠላቸውም። ጆን ዌስሊ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚያውቀውን፡ ለማርቲን ሉተር አልተገለጠለትም። ዘመናቸው ስለሚለይ፡ ጴንጤቆስጤዎች ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚያውቁት ነገር፡ ለባፕቲስቶች አልተገለጠም። የተለየ ጊዜ ነው። እግዚአብሔርም ነገሩን በየዘመኑ ይገልጠዋል። ኦህ!

116 በፀደይ ወቅት በቆሎ መትከል እና በተመሳሳይ ጊዜ ማጨድ አይቻልም። ዘር ትዘራለህ ቀስ ብሎ ያድጋል። እግዚአብሔር ቃሉን ይዘራል ወዲያውም ይበቅላል። ከዚያም ወደ ኋላ ተመልክተን "ይኸው ነው፡" እንለዋለን። ለምን፡ ከተገለጠ በኋላ ስለምናየው፡ አዎና።

117 አሁን ቃሉ፡ "ብጹአን" ሲል፡ በ3ኛው ቁጥር ያለውን፡ የብጽእና አዋጅ፡ "ምሥጢሩን ለሚያነቡ ወይም ለሚሰሙት።"

118 ይህም… ሥጋዊ አእምሮ ይነቀዋል፡ ምክንያቱም የሥጋ አእምሮ ምንም አያውቅምና። በዚያ የሚኖረው ሰይጣን ነውና፡ ሥጋዊ አእምሮ ባያውቀው ምንም አያስደንቅም። ሰይጣንም እንዲጋለጥ አይወድም፡ ሰይጣን ግን ተጋልጧል።

119 ሰይጣን ልጋለጥ ነው ብሎ ሲያስብ ምን ያህል አስቃቂ እንደሆነ አስተውላችኋል? በጉባኤዎቼ በአንዱ ላይ እዩት። የሰዎቹ ሁኔታዎች ተከታተሉ። ሰብሰባው ላይ፡ ተከታተሏቸው። ሰይጣን በአንድ ሰው ውስጥ፡ ሊጋለጥ ሲቃረብ፡ ፊታቸው ሲቀያየር ታያላችሁ። አያችሁ፡ ምን ማሰብ እንዳለባቸው አያውቁም። ወድያው፡ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ ዲያብሎስን ያጋልጠዋል። አቤት! እንዲህ ዓይነቱን ሰብሰባ ይጠላል። የእግዚአብሔር ቃል ዲያቢሎስን ስለሚያጋልጥ፡ እንዲህ አይነት ውጊያዎች የነበሩን በዚህ ምክንያት ነው። አያችሁ? ምንነቱን ይናገራልና።

120 ምሳሌ ያክል፡ "እዚህ ቁጭ ብላ ያለችውን ሴት፡" ከመንፈስ ቅዱስ ምሪት ስር ሆናችሁ፡ "ስሟ ወይዘሮ **ጆንስ** ይባላል። የመጣችበት **እንዲህ-እና-እንዲያ** ነው፡" ትላላችሁ። ያ ምን ያደርጋል? መንፈሷን ያነሳሳል፡ ወደ አንድ ሰፍራ ያወጣታል።

121 "ከወዴት ታውቀኛለህ? ይህ ሰው አያውቀኝም፡ ስለዚህ የሆነ መንፈስ መሆን አለበት። ምን አይነት መንፈስ ነው? "

"የእግዚአብሔር መንፈስ ነው።"

"እንዴት? ችግሬ ምንድነው? "

122 "ሳንባ ነቀርሳ፡ ካንሰር አለብሽ፡" ምንም ቢኖር ግን፡ "**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**… "

"አቤት!" አቤት፡ ሰይጣን እቺን እንዴት እንደሚጠላት፡ ስለምታጋልጠው ነው።

123 ከዚያም፡ ባለ አእምሮዎቹ አይተው፡ "አእምሮን-የማንበብ ብቃት ነው፡ ሜንታል ቴለፓቲ፡" ይሉታል። አያውቁትም። ለእነርሱ ሞኝነት ነው።

124 ምን እንደሆነ ለሚያውቁ ግን፡ ኦህ፡ እንዴት ያለ መታደል ነው! ምንድነው ይሄ? መገለጥ ነው። የማን መገለጥ? መድረክ ላይ ካለው ሰው ነውን? የኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ በመጨረሻዋ የቤተ ክርስትያን ዘመን፡ እንዲህ አደርጋለሁ ብሎ በገባው ቃል መሰረት እራሱን በመግለጥ ላይ ነው። አያችሁ?

125 መገለጥ ነው፡ አያችሁ፡ ሰይጣንም ይጠላዋል። አቤት፡ እንዴት እንደሚጠላው! ተጋልጧል፡ እቅዱ ሁሉ ከሽፏል። ሰይጣን ራዕይንና ዘፍጥረትን ይጠላቸዋል፡ እዚህ ጽፌዋለሁ። በትክክል እውነት ነው።

126 እሺ፡ መገለጥን ለምን ይጠላዋል? መገለጥ ለምን ይቃወማል? ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል እና የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን አጠቃላይ ቀኖና በመገለጥ መሰረት ላይ የታነጸ ነው።

127 የቱንም ያህል ጥሩ ትምህርት ቤቶች ቢኖሩንም፡ በጭራሽ—በትምህርት በኩል ሊሆን አይችልም። እነዚያ'ማ ገና በተፈረደበት ዘመን ላይ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ እና ቤተ ክርስቲያን ፍፁም መገለጥ ናቸው።

128 እዚህ ላይ አንዳንድ ቅዱሳት መጻህፍት ተጽፎ አግኝቻለሁ፡ ማቴዎስ፡ ከ—16ኛው ምዕራፍ 18ኛው ቁጥር፡ እንክፈት። ከማቴዎስ 16:18፡ ላይ—ትንሽ ወሰደን እንመልከተው፡ ቃሉ ምን ላይ እንደሆነ፡ መገለጥ የት እንዳለ እንመልከተው። ከተራራው እየወረዱ፡ 17ኛው ቁጥር።

> **ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፡ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፡ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ፡ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና፡ ብፁዕ ነህ።**
>
> **እኔም እልሃለሁ... አንተ፡... ጴጥሮስ ነህ፡ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፡ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።**

129 የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ትላለች፡ "በጴጥሮስ ላይ ሠራት።" ይህ፡ በእውነት፡ ሥጋዊ አስተሳሰብ ነው። መንፈሳዊ አእምሮ እንደዚህ ያለ ግምት ሲሰጥ ማየት መገመት ይከብዳል፡ እንደ እግዚአብሔርነቱ፡ ከልጁ ጋር በዚያ ቆሞ፡ ቤተክርስቲያኑን ተራ በሆነ፡ በኃጢአት-በተወለደ ሰው ላይ፡ አይሠራትም። ሰውየው'ኮ አረጋግጧል። እሱ፡ ያው መንፈስ በእርሱ ዘንድ ሆኖ፡ ኢየሱስን ረግሞ ፊት ለፊት ካደ። ጴጥሮስን አይደለም።

130 ወይም፡ አንዳንድ አብያተ ክርስትያናት እንደሚሉት፡ እዚያው የተጋደመ—ድንጋይም አልነበረም። ድንጋይ አልነበረም። ምክንያቱ፡ ጴጥሮስ...

131 በዚያ የተናገረው ዐለት፡ ስለ ጴጥሮስ አልነበረም፡ ስለ ራሱም አልነበረም።

132 ብዙ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች፡ "በኢየሱስ ነው። ቤተክርስቲያኑን የሠራት በርሱ ዘንድ ነው ይላሉ። እሱ!" አይደለም፡ ይህም ስሕተት ነው። ካስተዋላችሁት፡ በኢየሱስም አይደለም፡ በጴጥሮስም አይደለም። መገለጥ ላይ እንጂ።

> ... **ሥጋና ደም** ይህን **አልገለጠልህም፡** ነገር ግን **በሰማያት ያለው አባቴ** ይህን መገለጥ ሰጠ።

133 ተመልከቱ። ልጠይቃችሁ። በኤደን ገነት ውስጥ፡ የተጻፈ ቅዱስ ቃል ገና አለነበረም። ሁለቱ ልጆች፡ ቃየን እና አቤል፡ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን ለማግኘት ሁለቱም መሰዋዕት ማቅረብ ፈለጉ። ይህንም ማድረግ በፈለጉ ጊዜ፡ ቃየን መጣና መሰዊያን ሰራ፡ አቤልም መሰዊያን ሰራ። ታዲያ፡ የእግዚአብሔር ቅድመ ሁኔታ ያ ቢሆን ኖሮ፡ እግዚአብሔር ቃየንን መኰነኑ ትክክል አይሆንም። እሺ። ቃየን መሰዋዕት አቀረበ፡ አቤልም እንዲሁ። ሁለቱም መሰዋዕት አቀረቡ። ቃየን አመለከ፡ አቤልም እንዲሁ። ቃየን አቤል ያደረገውን ሁሉ አድርጓል።

134 ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዳችሁ፡ የቤተ ክርስቲያን አባል ሆናችሁ፡ መስዋዕት እያደረጋችሁ፡ እየጸለያችሁ፡ እግዚአብሔርንም የምታመልኩ ከሆናችሁ፡ እግዚአብሔር የሚፈልገውም ያ ከሆነ፡ ቃየንም የታዘዘውን በማድረጉ እግዚአብሔር ቢኰንነው ትክክል አይሆንም ነበር።

135 አቤል፡ ግን፡ እንዳያችሁት፡ በመገለጥ፡ ዛሬ ብዙ ሥጋዊ አእምሮዎች እንደሚያስቡት፡ ከኤደን ገነት ያወጣቸው ፍሬ እንዳልሆነ ተገለጠለት። አቤል መጥቶ የምድሪቱን ፍሬ አቀረበ፡ ይቅርታ፡ ቃየን ማለቴ ነው፡ እግዚአብሔርም ግን፡ አልተቀበለውም… ነገር ግን ተገለጠ። ቃየን የምድርን ፍሬ አቀረበ ምክንያቱም ከዔድን ገነት ያወጣቸው ያ ነው ብሎ ስላሰበ ነው። ያን መገለጥ ተመልከቱት። አብሮ የሚመጣ አለመግባባትም ተመልከቱት። ዛሬም እንዴት እንደሚጎዳ እዩት። ያወጣቸው ግን ፍሬ አልነበረም። ሔዋን በጭራሽ አፕል አልበላችምና። በትክክል። አፕል በመብላትዋ፡ እራቁት መሆኗን እንዴት አስተዋለች? ከጾታዊ መነካካት የተያያዘ ነው። መሆንም አለበት!

136 ይህም፡ እንደ ጥናት ወሰደነዋል፡ ወደሱም፡ ተመልሰናል። አንድም ቃል ማምጣት አይችሉም።

137 አንዳንዶቹ እንዲህ ይላሉ፦ "'ከጌታ ዘንድ ወንድ ልጅ አገኘሁ፡' ብላለች።" አዎን፡ ወዳጄ። አመንዝራም ታገኛለች። የሕይወት ሁሉ ሰሪ እግዚአብሔር ነውና።

138 ነገር ግን የተዛባ ህይወት ነው። የዚያን ልጅ ተፈጥሮ ተመልከቱት። እርሱ ከአባቱ፡ ከዲያብሎስ ነበር፡ ጥል፡ ክርክር፡ ግዲያ። አያችሁ?

139 ከዚያም፡ አቤል፡ እንደነሱ… ወላጆቹ እንዲህ ብለው ሳይነግሩት አልቀረም—ዛፎቹ ፍሬ አላቸው፡ ወዘተረፈ። አቤልን ግን፡ ተገለጠለት። አቤልም የበግ ጠቦት አመጣ፡ ስለ ደም፡ ህይወትን ሠዋ። አፕል እና ሙዝ እና ፒር የሚሰጥ፡ የፍራፍሬ ዛፍ አይደለም። "አቤል ግን፡ በመንፈሳዊ መገለጥ።" ዕብራውያን 11፡ "ለእግዚአብሔር የሚበልጥ መሥዋዕት አቀረበ። በእምነት ተገልጦለት ነበርና፡ እግዚአብሔርም መሰከረለት።"

140 እግዚአብሔር ቤተክርስቲያኑን የሠራው በዚያ ነው። "ሥጋና ደም ይህን ከቶ አልገለጠልህምና።" በሴሚናሪ ውስጥ ፈጽሞ አልተማረውም። የሆነ ሰው የሆነ ቦታ ላይ ያስተማራችሁ አይደለም። "በሰማያት ያለው አባቴ ግን ገለጠልህ።" ስለዚህ መላ ነገሩ፡ መላ ቤተክርስትያኒቱ፡ የመገለጥ ጉዳይ ነው፡ "በዚህ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ዓለት ላይ፡ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ።"

141 ፓስተሩ የሚለውን ልትቀበሉ ትችላላችሁ። ሴሚናሩ የሚያስተምረውን ልትቀበሉ ትችላላችሁ። ቤተክርስቲያን የምትለውን ልትቀበሉ ትችላላችሁ። ቢሆንም፡ ትክክል አይደለም። በአንደበተ ርቱዕነት ልታብራሩት ትችሉ ይሆናል። ነገር ግን እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ልጁ እንደሆነ እስኪገልጥላችሁ፡ እናንተም በደሙ፡ "እርሱ አዳኜ ነው፡" በሚለው በዚያ መገለጥ፡ ድናችኋል።

142 "በዚህች ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፡ የገሃነም ደጆች አይችሏትም።"

143 ስለዚህ ሰይጣን የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍን የሚቃወመው ለምን እንደሆነ ታያላችሁ። የተገለጠው ማንኛውም፡ መንፈሳዊ መገለጥ፡ ሰይጣን

ይቃወመዋል። ዛሬም ይህን አገልግሎት በጣም የሚቃወመው ለዚህ ነው። ምክንያቱ፡ ምንድን ነው? ክርስቶስን የሚገልጥ ስለሆነ።

144 ቤተ ክርስቲያን ከታላላቅ የሐይማኖት ተቋማቶቿ እና ድርጅቶቿ፡ እስከነ አበባ የመሰለ መልዕክቶቿ ትሂድ ግድ የለም። ይሂዱ ተዋቸው፡ ሰይጣን በዚያ አይደነግጥም። ችግር የለባቸውም። ሰው ሁሉም ጀርባቸውን መታ መታ ያደርጋልና።

145 እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት፡ ክርስቶስን በቤተክርስቲያኑ ውስጥ፡ የታመሙትን በሚፈውስ ኃይሉ እና ሥራው፡ አማኞቹን እንደሚከተሏቸው የተናገራቸውን ምልክቶች፡ ሲፈጸሙ በማሳየት፡ የሚገልጥበት ጊዜ ሲመጣ፡ ሰይጣን አልጋው ላይ ይገላባበጣል። የሆነ ነገር ለማድረግ ይፈልጋል። ያ ጊዜ እስኪመጣ ድረስ ግን፡ ምን ያህል ቤተ ክርስትያን ቀየርክ ሰይጣን አይገደውም። ምንም አይገደውም። ነገር ግን ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ፡ እርሱ የሠራውንም ሥራ እናንተ ደግሞ እንደምትሰሩ ሲገልፅላችሁ፡ ሌሎች ሰራዎች አይደለም፡ ያንኑ ተመሳሳይ ሰራዎች እንጂ።

146 "በእኔ የሚያምን..." ቅዱስ ዮሐንስ 14:7። "በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል። እኔ የማደርገውን ያደርጋል፡ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል።" ምክንያቱ፡ ክርስቶስ ስለመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ አይሰብክምና፡ የሚበልጥ ይህ ነው። መንፈስ ቅዱስ ገና አልተሰጠምና፡ ወደ እነርሱ ሊያመጣው አልቻለም። ኢየሱስ መጥቶ ነፍሱን በሠዋ ጊዜ ግን፡ መንፈስ ቅዱስም ተመለሰ፡ ከዚያም ለሰዎች የዘላለም ሕይወትን ማካፈል ቻሉ። "የሚበልጥ" ይህ ነው።

147 ስለ ድንቆች እና ምልክቶች ግን፡ ኢየሱስ በማርቆስ 16 ላይ፡ በግልጽ ተናገረ፡ "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ሰበኩ።" ምን ያህል ርቀት? ወደ ዓለም ሁሉ። ለነማን? ለፍጥረት ሁሉ። ወንጌል እስከተሰበከ ድረስ፡ የሚያምኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል። ወንድሜ ሆይ፡ ያ ደግሞ በመገለጥ ሲሆን፡ ለመንግስቱ ቅርብ ነህ። "በዚህች ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፡ የገሃነም ደጆችም ሊያሸንፏት አይችሉም።"

148 ምክንያቱ፡ እንደ ሙሴ፡ ምድረበዳ ላይ ብቻውን ቆይታ ያደረገ ሴትም ይሁን ወንድ፡ የእግዚአብሔርም መገለጥ በመንፈስ ቅዱስ የተገለጠለት ሰው፡ በምንም አይናወጥም። መሆን የሚችለውን ያህል ጤናማ እና ብርቱ ሆኖ ይጸናል።

ሰይጣን መገለጥን ይጠላል። ፈጽሞ አይወደውም፡ ዕቅዶቹን ሁሉ ይመታበታልና።

149 የመፅሀፋ ተፈጥሮ ራሱ ዮሐንስ እንዳልፃፈው ያሳያል። ትክክል ነው። የሌላ—የሌላ ናቸው... ጽሑፎቹ የእርሱ ናቸው፡ ምሪቱ ግን የእርሱ አይደለም። መጽሐፉን የጻፈው የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ምሪት ነው። በጣም ጥሩ።

150 አሁን ምን እንደሚል እንይ።

**ዘመኑ ቀርቦአልና የሚያነበው፡ የትንቢቱን ቃል... የሚሰሙትና፡ በውስጡ የተጻፈውን የሚጠብቁት፡ ብፁዓን ናቸው።**

151 አሁን፡ “ጊዜው ደርሷል።” የምን? ኢየሱስ ክርስቶስ ለአብያተ ክርስቲያናቱ የሚታወቅበት ሙሉ መገለጥ። ጊዜው እያለቀ ሲሄድ፡ እየተገለጠላቸው ነው።

152 አሁን በመጨረሻው ሰዓት ላይ፡ በትክክል በዓለም መጨረሻ ላይ ነን። የዓለም ታሪክ ፍጻሜ ላይ ደርሰናል። ይህ ሳምንት ከማለፉ በፊት፡ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆኖ፡ እየረዳን፡ በቤተ ክርስቲያን ዘመን ፍጻሜ ላይ መሆናችንን እናረጋግጣለን። በፊላዴል-... ወይም በሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ የዘመናት ሁሉ ፍጻሜ ላይ ነን። የፖለቲካው ዓለም ፍጻሜ ላይ ደርሰናል። እኛ የተፈጥሮው ዓለም—ፍጻሜ ላይ ደርሰናል። የሁሉም ነገር ፍፃሜ ላይ ደርሰናል። በሁሉም የተፈጥሮ ነገር ሁሉ መጨረሻ ላይ ነን፡ ለመግባት ተዘጋጅተናል።

153 በቀደም እየመጣሁ፡ ወደ ሽሪፖርት እየሄድኩ፡ ወይም ከሆነ ቦታ እየመጣሁ መሰለኝ። አንድ ነገር አየሁ። እንዲህ አልኩም፡ “ዛፎቹ እየሞቱ ነው። ሳሩ እየሞተ ነው። አበቦቹ እየሞቱ ነው። እኔም እየሞትኩ ነው። አለም እየሞተች ነው። ሁሉም ነገር እየሞተ ነው። በዚህ ዓለም ውስጥ ያለው ሁሉ እየሞተ ነው።” ዛሬ ጠዋት እዚህ ቁጭ ብለን እየሞትን ነው።

154 በእርግጠኛነት ሁሉም ነገር የማይሞትባት ዓለም፡ በሆነ ስፍራ አለች። ሁሉም ነገር የሚሞትበት ካለ፡ ሁሉም ነገር የሚኖርበት ሌላ መኖሩ ግድ ነው። ዛፎች... ቆመው ወደማይሞቱባት፡ ወደዚያ ስፍራ መድረስ እንናፍቃለን። እቤት፡ ነገር ሁሉ በ—እግዚአብሔር ክብር የማይሞት ሆኖ ጸንቶ የሚቆምባት።

155 እስከ፡ አሁን፡ የመጀመርያዎቹ ሶስት ቁጥሮች፡ የነገሩን ዳራ በማስቀመጥ አይተናቸዋል። 1ኛ፡ “የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ።” 2ኛ፡ “ለዮሐንስ የተሰጠው በመልአክ መሆኑ።” እና 3ኛ፡ “በረከት፡ ለሚያነቡ በረከት፡ እና፡” ማንበብ ካልቻሉ ግን፡ “ለሚሰማው በረከት ነው።” ማንበብ አትችልም? ዝም ብለህ ስማው። ይኼው ነው። “የሚያነበው ብጹዕ ነው፡ እና፡” ማንበብ ላልቻለ፡ “ለሚሰማው ብጹዕ ነው፡ ጊዜው በደጅ ነውና።”

156 አሁን፡ አስቡት የዚህ ነገር ቀኖናው ምን ማለት እንደሆነ፡ ይህ፡ ዮሐንስ፡ ጸሐፊው፡ ሲጽፈው፡ የነበረ... **ይህ** ዮሐንስ፡ ስለ፡ “ብጽዕና” እና ስለ ሌላ ተናገረ። አሁን፡ እኔ እንደማስበው፡ በብሉይ ኪዳን፡ ካህኑ በማለዳ ተነስቶ ቅዱሳት መጻሕፍትን ያነባል። ጉባኤው ያዳምጣል። ብዙዎች ማንበብ አይችሉም። ስለዚህ እንዲህ አለ፡ “የሚያነቡት፡ እና የሚሰሙት ብጹአን ናቸው።” አያችሁ? አንባቢ እና ሰሚ፡ ያነበበ፡ የሚሰማ፡ የተባረከ ነው። ስለዚህ ቁጭ ብላችሁ ካዳመጣችሁ፡ ብሩካን ናችሁ። “ዘመኑ ቀርቦአልና፡ የሚያነቡት፡ እና የሚሰሙት ብጹአን ናቸው።”

157 ከዛ በኋላ፡ ከ 4 እስከ 6 ለቤተክርስቲያን የተሰጠ ሰላምታ ነው። አሁን 4ኛው እና 6ኛው እናያለን።

158 አሁን፡ በደንብ ከመግፋታችን በፊት፡ ሁሉም ሰው በደንብ እንዲያስብበት እፈልጋለሁ። ይህ ነገር ምንድነው? እግዚአብሔር የዘመኑን መጋረጃ ያወለቀበት፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ነው። ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ፡ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት፡ ምን እንደሚፈጠር ማየት ያልቻለው ጊዜው **እዚህ** ነው። ስለዚህ፡ እግዚአብሔር መሸፈኛውን ገፈፈው፡ ወደ ኋላም ጎተተው፡

እና ዮሐንስ ወደ ውስጥ እንዲመለከት እና እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ምን እንደሚያደርግ እንዲያይ ፈቀደለት፡ እርሱም በመጽሐፍ ጽፎ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ላከ።

159 ምንድነው ይሄ? በተግባር በሚታይበት—በዘመኑ የተገለጠ ክርስቶስ ነው። መጽሐፉም፡ በተግባር የተሞላ ነውና። ክርስቶስ የሰጠው—ትንቢታዊ መጽሐፍ፡ እግዚአብሔር በመልአኩ ለእኛ ሰጠን፡ በዮሐንስም ተጻፈ። ስለዚህ ለሚያነበው ወይም ሲነበብ ለሚሰማው ለሁሉ በረከት ነው፡ ይህ ሁሉ—የሚፈጸምበት ጊዜ ቀርቧልና።

160 አሁን ጥሩ ቅንብር ነው። ቤተክርስቲያንን በአሳባችን ውስጥ እንደያዝን፡ አስታውሱ። በአንድ በኩል፡ የቤተክርስቲያን ጅማሬ ሲሆን፡ በሌላ በኩል፡ የቤተክርስቲያን ፍጻሜ ነው። በበለጠ ደግሞ፡ ሰኞ ማታ፡ የቤተ ክርስትያን ዘመናት እንጀምራለን።

**ዮሐንስ፡ በእስያ ላሉት ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት፡ ካለውና፡... ከነበረው፡ ከሚመጣውም፡ በዙፋኑም ፊት ካሉት ከሰባቱ መናፍስት፡ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።**

161 አሁን ወደ ምልክቶቹ እና ወደ ምስጢራዊ እና ጥልቅ ክፍሎች ውስጥ እየገባን ነው። የተላከው በትንሿ እስያ ላሉ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ነው። እነዚያ ዘመናት—በዚያ ወቅት፡ ወደፊት ሊመጡ ያሉትን፡ ዘመኖች... ነበሩ—ነበሩ። ስለ ሰሩት እና—ሰላደረጉት ሰለሰራቸውም ከፍ ከፍ አደረጋቸው እና አመሰገናቸው። አሁን፡ ግን፡ በትንሿ እስያ ላሉት ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የተላከ ነው።

162 ትንሿ እስያ ማለት፡ እስያን በሙሉ ማለት አይደለም። አነስተኛ ክፍል ብቻ ነበረች። የፔንሰልቬንያ ግዛትን የሚያክል ቦታ፡ ወይም፡ የኢንዲያና፡ አይነት ነገር፡ እንደነበረች ይናገራሉ፡ እነዚህ ሰባት አብያተ ክርስቲያናት የተቀመጡባት ትንሽ ግዛት ናት። በወቅቱ ከእነዚህ አብያተ ክርስትያናት የሚበዙ ሌሎች ነበሩ። ይሁን እንጂ፡ መገለጫዎቻቸውን፡ አሳየ። አሁን ከታሪክ ንባቤ ያገኘሁትን እዚህ እያነበብኩ ነው።

163 "ለእርሱ ግን... ለማይሰማው፡ ወይም ነገሩን ለማያዳምጥ፡ ለእሱ እርግማን ነው።"

164 እና—እና አሁን፡ ጊዜው የ4ኛ ቁጥር አንድ ነገር እዚህ መግለጽ ወዳለብን ጊዜ ደርሰናል። "ካለውና፡ ከነበረው፡ ከሚመጣውም፡ ከሰባቱ መናፍስት፡ በዙፋኑም ፊት ካሉት ከሰባቱ መናፍስት፡" ስለ፡ "መናፍስቱ፡" በኋላ እንመለስበታለን።

165 እዚህ፡ ካስተዋላችሁ፡ እዚህ—ጋር አንድ ነገር ይተነትናል። ደግሞ በ7ኛው ቁጥር፡ ወይም በ8ኛው ቁጥር፡ ዳግመኛ መጥቶ፡ በድጋሚ ይተነትነዋል። አሁን ተመልከቱ። ለሰባቱ አብያተ ክርስትያናት የተላከ ነው። "ካለውና፡ ከነበረውም፡ ከሚመጣውም ከእርሱ። ይህም አንድ ጊዜ፡ የነበረ፡ አሁን ያለው፡ እና ወደፊት የሚመጣው ነው።" እንግዲህ፡ ሶስት መአዝናዊነቱ፡ የሰራው ሶስት መአዝናዊ መገለጫውን እያስረዳ ነው።

166 ለምሳሌ 8ኛውን ቁጥር እንውሰድ። በአንድ ደቂቃ ውስጥ፡ እንመለሰበታለን። 8ኛውን ቁጥር እንውሰድ።

**ያለውና የነበረው፡ የሚመጣውም፡ ሁሉንም የሚገዛ ጌታ እምላክ፡ አልፋና፡... ዖሜጋ፡ እኔ ነኝ፡ ይላል።**

167 አሁን እያየን ያለነው ቁጥር 4ን እና 6ን ነው፡ ይሁን እንጂ ሁለቱም አንድ አይነት ይዘት ናቸው። አንዱ፡ እንዲህ ይላል፡ “ለነበረው፡ ላለው፡ ለሚመጣው።” በቤተክርስትያኒቱ ፊት ምን ማሳየት ፈለገ? አምላክነቱን። ዛሬ፡ ሰዎች እርሱን—ነብይ ሊያደርጉት ይፈልጋሉ። ከነብይ በላይ ነው። አንዳንዶች ደግሞ ሦስት አማልክት ሊያደርጉት ይፈልጋሉ። ሰሦስት አማልክት አይደለም። ነገር ግን በሶስት አገልግሎቶች የኖረ አንድ አምላክ ነው፡ የአንዱ አምላክ ሶስት መገለጫዎች።

168 አሁን፡ አስተውሉ፡ መገለጡ እዚህ ላይ ነው፡ “ስምቶም የዚህን መጽሐፍ ቃል የማይጠብቅ፡ ድርሻው ከሕይወት መጽሐፍ ይወሰድበታል።” ኢየሱስ ራሱን እንደ ሶስት አምላክ ሳይሆን፡ ሶስት አገልግሎቶች እንዳሉት አንድ አምላክ እየገለጠ ነው። አቤት! ወደ ቤተ ክርስትያን ዘመናት ገብተን የት እንደሳቱት ካየነው በኋላ፡ እየወፈረ ይሄድልናል። በኒቂያ ጉባኤ ትልቅ መከፋፈል ተፈጠረ። ሁለቱም ወደ ጽንፍ ጫፍ ሄዱ።

169 ዳግመኛም በዚህ በመጨረሻው ዘመን ተመሳሳይ ነገር አደረጉ፡ ልክ እንደ ቅድመ-ኒቂያ ጉባኤ፡ እንደገና ሌላም ሰለሚኖር ነው። እኔ እዚሁ መቆሜ እርግጥ እንደሆነ ሁሉ፡ የካቶሊክ እና የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት አንድ ነገር ላይ አንድ ይሆናሉ፡ ወይም እርስ በርሳቸው ይሰማማሉ። የካንተርቤሪ አርክቢሾፕን ተመልከቱት። ሁሉም አንድ ላይ እየተከመረ ነው። በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ ሥስት አምላክ የሚያስተምር የለም። አንድ አምላክ ብቻ አለ።

170 በዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ውስጥ የተገለጠ ነገር ነው፡ ማለት፡ የቅዱሳን ቃላት ሙሉ ቀኖና እዚህ ውስጥ ተረጋግጧል፡ ክርስቶስም ማሕተሙን አሰፍሮበታል። ይኸው ነው። ማንም ቢያጎድል ወይም በእርሱ ላይ ቢጨምር፡ እጣው፡ ከህይወት መጽሐፍ ይወሰድባታል። ሰለዚህ በራስ ወዳድነት ሳይሆን፡ በተከፈተ ልብ እና በተከፈተ አእምሮ ተመልከቱት።

171 አሁን፡ በኒቂያው ጉባኤ፡ ወደ ሁለት ታላላቅ ውሳኔዎች ደረሱ። ኦህ፡ በዚያ ዘመን... በቀደሙት የቤተክርስቲያን አባቶች መካከል፡ በብዙዎቹ ሁለት ጽንፈኛ አመለካከቶች ነበራቸው። አንዳቸው በእግዚአብሔር ሦስትነት የሚያምኑ፡ ሰላሴአውያን። ሌላው ደግሞ አንድ—አምላክ የሚሉ ነበሩ። ሁለቱም በህልውና፡ **እንዲህ** ዘለቁና ወደ ሁለት ቅርጫፎች አደጉ። ሶስትነት የሦስት-አምላክ አካላት ወደ መሆን አመራ። አንድነት ወደ አሃዳዊነት ሆነ፡ ማለት ከዛኛው ባልተናነሰ መልኩ ወደ ስሕተት አመራ። ሰለዚህ ሁለቱም ወደዚያ ቅርንጫፎች አደጉ፡ **እዚሁ** ላይ ግን እውነቱን ይገልጠዋል።

172 መቼም ኢየሱስ የራሱ አባት ሊሆን አይችልም። ከመንፈስ ቅዱስ ውጭ ሌላ አባት ያለው ከሆነም፡ እርሱም ሕገወጥ ልጅ ይሆናል። ይህ ሳይሆን... ከመንፈስ ቅዱስም ፀነሰው፡ በተጨማሪም እግዚአብሔር አባቴ ነው አለ። ሰለዚህ መንፈስ ቅዱስ እና እግዚአብሔር... ማቴዎስ 1፡18 ነው። እንዲህ ከሆነ... መንፈስ ቅዱስ እና እግዚአብሔር አንድ አካል ነው፡ ካልሆነ ግን

ሁለት አባቶች ነበሩት። እርሱም **አማኑኤል**፡ ተብሎ ተጠራ፡ ትርጉሙም፡ “እግዚአብሔር ከኛ ጋር ነው።” እዚህ ምድር ላይ በነበረ ጊዜ፡ እርሱና አብ አንድ መሆናቸውን ተናግሯል።

173 ይህ ነገር—ጥያቄ ሆኖባችሁ ከነበረ፡ እናንተም እንድታገኙት፡ ቃላቶቹን እዚህ ጽፌ ይዣቸዋለሁ።

174 ስለዚህ፡ እሱ ስለ ማንነቱ፡ ባለ ሶስት መአዝናዊ አገልግሎት ሆኖ ሲተረክ፡ “የነበረው፡ ያለው፡ የሚመጣው፡ ሁሉም የሚገዛ፡” በዚህ ውስጥ፡ ሦስት አማልክት የሉም፡ አንድ አምላክ እንጂ።

175 በኒቂያው ጉባኤ ግን፡ ይህን ለመፈጸም፡ ይህንንም ለማድረግ፡ ሥላሴን መቀበል ነበረባቸው፡ የዚህ ምክንያትም ሮማውያን ብዙ አማልክት ስለነበሯቸው ነው። በሙታኖች ቅድመ አያቶቻቸው ጸሎት ያደርጋሉ። ልንጠቅስበት የምንችልበት ታሪክ እዚህ ይዣለሁ። አያችሁ? በሙታን ቅድመ አያቶቻቸው ላይ ይጸልያሉ። ለዚህም ነው ቅዱስ ሴሲሊያ፡ እና ቅዱስ ማርቆስ እና ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ያሏቸው።

176 ሐዋርያው ጴጥሮስ፡ “በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ሌላ መካከለኛ የለም፡ ሰው ከሆነው ከክርስቶስ ኢየሱስ በቀር፡” አለ። አንድ።

177 ስለዚህ ሥላሴአዊ አምላክ ሊኖራቸው ግድ ነበር። በዚህም ደግሞ—ጁፒተር፣ ማርስ፣ እና ቬነስ ነበሯቸው። “ትክክልም አልነበረም፡ ሁሉንም በአንዱ አምላክ ላይ አደረጉት፡” ስለዚህም ከፋፍለው፡ ባለ ሶስት መአዝናዊ አገልግሎት ሶስት የተለያየ አማልክት አደረጉት።

178 በዚህ በራዕይ ግን፡ እርሱ ማን እንደሆነ፡ በግልጽ ተናግሯል። “የነበረው፣ ያለውም፣ የሚመጣውም፣ ሁሉን የሚገዛ እኔ ነኝ።” ከትንሽ ቆይታ በኋላ እንየዋለን፡ እንዲኢህ አለ፡ “እኔ አልፋና ኦሜጋ ነኝ፡” ከሀ እስከ ፐ፡ ጠቅላይ፡ የግሪክ ፊደል እኔ ነኝ። “የሸለቆ አበባ፡ የሳሮን ጽጌረዳ፡ አባት፣ ልጅ፣ መንፈስ ቅዱስ፡ የነበረው፣ ያለው፣ የሚመጣው፣ የዳዊት ሥርና ሐረግ።” እርሱ እግዚአብሔር፡ አምላክ ነው። “በ-... ” እንደኛ ጢሞቴዎስ 3:16፡ “ያለ ጥርጥር፡ እግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር ታላቅ ነው፡ እግዚአብሔር በሥጋ ተገለጠ፡ ለመላእክት ታየ፡ በዓለም ታመነ፡ በክብር አረገ።” እግዚአብሔር! ሦስተኛ ሰው ወይም ነቢይ ሳይሆን እግዚአብሔር ራሱ በሰው አምሳል ተገለጠ። አስታውሱ፡ መገለጥ፡ ይህ ነው።

179 እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያ፡ በእሳት ዓምድ ውስጥ የሚኖር፡ ታላቁ ጀሆቫ ነበረ፡ ከእስራኤል በላይ እየተጓዘ፡ ይመራቸው ነበር። ያ የቃል ኪዳኑ መልአክ፡ እግዚአብሔር እርሱ ነበር። ወደ ተራራው በወረደ ጊዜ፡ ተራራው ሁሉ በእሳት ነደደ። እሳት ከተራራው በረረ፡ እና አሰርቱን ትእዛዛት ጻፈ። ያም ደግሞ ለተመረጡት ለልጆቹ፡ ለተመረጠው ዘር ለህዝቡ፡ ማለት ለአይሁድ፡ “የእግዚአብሔር አባትነት፡” ተብሎ ተጠራ።

180 ይህ አምላክ ራሱ በማርያም ማሕጸን በድንግልና-በተወለደ ስጋ እራሱን ገለጠ፡ ኖረ፡ ተቀመጠ፡ ድንኳኑንም በሰው ልጆች መካከል ዘረጋ። ይህ አምላክ ራሱ ስጋ ሆነ በመካከላችንም አደረ። መጽሐፍ ቅዱስም መሰከረ። “እግዚአብሔር በክርስቶስ ነበረ።” ስጋው ኢየሱስ ነበር። በኢየሱስም “በእርሱ የመለኮት ሙላት በስጋው አደረ።” አሁን፡ እርሱን ሶስት ሰዎች ማድረግ

አትችሉም። ለሶስት አማልክት አትጠመቁ። አንድ አምላክ ብቻ አለና። አያችሁ? አንድ አምላክ ነው። ይህ አምላክም፡ ስጋ ሆነ።

"ከእግዚአብሔር ዘንድ መጥቻለሁ፡ ወደ እግዚአብሔርም እሄዳለሁ፡" አለ።

181 በመሞት፡ በመቀበር፡ እና በትንሳኤ፡ በዕርገቱም፡ ከምድር ላይ ከተሰወረ በኋላ፡ ጳውሎስ ገና "ሳኦል" ይባል በነበረ ጊዜ፡ በደማስቆ መንገድ ላይ አገኘው። ድምፅም መጣና፡ እንዲህ አለው፡ "ሳውል፡ ሳውል፡ ስለ ምን ታሳድደኛለህ? "

እርሱም "ማን ነህ፡" አልው?

"እኔ ኢየሱስ ነኝ፡" አለው።

182 ያኔ የእሳት አምድ ነበረ፡ የሐዋርያውን ዓይኖች ያጠፋ ብርሃን ነበር። ተመልሷልና። ያው ኢየሱስ፡ እንደገና ወደ እግዚአብሔር አብ፡ ተመልሶ ነበር። እዚህ ጋር ስጋ ከመሆኑ በፊት የነበረውን ምሳሌ ጠቅሶ፡ "ሁሉን የሚገዛ እኔ ነኝ፡" ብሎ የሚናገርበት ምክንያት ያ ነው፡ እርሱ ይኖርበት የነበረው ስጋም፡ ኢየሱስ ይባላል፡ ይህም ኢየሱስ፡ ሁላችንም የምናውቀው ነው።

183 አሁን፡ እንደ ብዙዎቻችሁ ውድ የአሃዳያን ሰዎች፡ "በኢየሱስ ስም፡" ማጥመቃችሁም ስሕተት ነው። ዛሬ በዓለም ላይ በመቶዎች የሚቆጠሩ ኢየሱሶች አሉና፡ ግን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ አለ። እርሱም ክርስቶስ ሆኖ ተወለደ። ብዙ ኢየሱሶች። ብዙዎቹን አግኝቻለሁ። ግን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለ፡ እርሱም አምላክ ነው።

184 በተጨማሪም አባት፡ ልጅ፡ እና መንፈስ ቅዱስ **ስሞች** አይደለም። ለአንድ ሰም የሚሰጡ መዓርጎች ናቸው። "'በአባት፡ በልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ ሰም፡'" ያጠምቃሉና። **አባት** ሰም አይደለም፡ **ልጅ** ሰም አይደለም፡ **መንፈስ ቅዱስም** ሰም አይደለም። "ሰው፡" እንደሚባለው መዓርግ ናቸው። መንፈስ ቅዱስ፡ መንፈስ ነው። ሰው... ወይም፡ መንፈስ፡ መንፈስ ቅዱስ እንደማለት ነው። እነርሱም "'በአባት' ሰም፡" ይላሉና። አባቶችን ተመልከቷቸው፡ የልጆቻችሁ ልጆችም እዩአቸው። እዚህን ሰዎች ተመልከቷቸው። አያችሁ? "አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ" ሰም አይደለም። "ጌታ ኢየሱስ ክርሰቶስ" ለሚባለው ሰም የተሰጡ መዓርጎች ናቸው።

185 ሐዋርያዊ የሆነችው የመጀመርያዋ ቤተ ክርሰቲያን፡ የተጠመቀችበት መንገድ ይህ ነው። ከታሪክ ውስጥ ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ፡ አንዲት ቃል አውጥቶ፡ የካቶሊክ ቤተ ክርሰትያን እስክትመጣ ድረስ የክርሰትና ቤተ ክርሰትያን በሌላ መንገድ የተጠመቀችበት... "በኢየሱስ ክርሰቶስ" ሰም በቀር ሌላ ዘዴ ካለ እንዲያሳየን እጠይቃለሁ። "አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ" በሐይማኖት ሰርዓት ያሳደጉት አዋልድ ነው። አሁን፡ እናንተ የታሪክ ምሁራን፡ እስኪ ታሪካችሁን አውጡ። አዎን። እንዲህ ያለ ነገር የለም። ከ 304 **ዓ/ም**፡ ከ304 በኋላ፡ ስለ ሶስት አማልክት የመጣ ሶስታዊ ጥምቀት ነው፡ "እግዚአብሔር አባት፣ እግዚአብሔር ልጅ፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ።" አረማዊነት ነው።

186 ይህ ሳምንት ከማለቁ በፊት፡ ከመጻሕፍቱ ውስጥ አንብቤ በመጽሐፍ ቅዱስ አሳያችኋለሁ። ዛሬ ጠዋት በመገለጥ ዙርያ እየተነጋገርን ነው፡ እና የት እንደገባ፡ ወደ ህልውና እንዴት እንደመጣ አረጋግጡ። ወንድሜ ሆይ፡ ወደ እውነታው ተመለስ! በመጨረሻ ቀን ላይ ነን።

187 ወደ ኤፌሶን ቤተ ክርስትያን ደርሰን ከሎዶቅያ ጋር እስክናስተያየው ድረስ ጠብቁ፡ ከዚያ በመካከላቸው ምን እንደተፈጠረ ተመልከቱ። ያ ነገር ሾልኮ እንዴት እንደገባ ታያላችሁ። ወደ ሉተር ዘመን ስትደርሱ፡ እንዲህ ይለዋል፡ "'ሕያው' እንደመሆንህ ስም አለህ፡ ሞተህማል።" **ሰርዴስ** የሚለው ቃል ራሱ "የሞተ" ማለት ነው። በአስራ አምስት መቶ የጨለማ ዘመን ላይ ጠፋባቸው። እያንዳንዳቸው አብያተ ክርስትያናት እስከዚያ ዘመን ድረስ አቆይተውታል። ከዚያም በ606 የኒቂያ ጉባኤ ካደረጉ በኋላ፡ ያንን ስም አፍርሰው ሦስት አማልክትን አደረጉ።

188 እዚህ ጋር እንዲህ አለ፡ "የነበረውም፡ ያለውም፡ የሚመጣውም፡ ሁሉንም የሚገዛ እኔ ነኝ።" አዎን።

189 ምድር ሶስት መኢዝናዊ ስብእና ነበረው። በምድር በነበረ ጊዜ፡ ሶስት መኢዝናዊ ስብእና ነበረ። በምድር ላይ፡ ነብይ ነበረ። ደግሞ በሰማይ ውስጥ፡ ካህን ነው። ዳግመኛም ወደ ምድር ሲመጣ፡ ንጉሥ ይሆናል። ነቢይ፣ ካህን፣ እና ንጉስ። የነበረውም፡ ያለውም፡ የሚመጣውም። "የነበረው፡" ነቢይ የነበረው ማለት፡ ኢየሱስ። "አሁን ያለው፡" መንፈሳዊው መሰዋዕት የሚያቀርብ፡ ካህን ነው፡ በድካማችን ሰሜት የሚነካ ሊቀ ካህናት፣ እራሱን ገልጦ በመካከላችን እንዳለ እራሱን አረጋግጧል። ነቢይ፣ ካህን፣ እና ንጉስ፣ ግን አንድ አምላክ።

190 በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ነቢይ፡ ማለት ቃል ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ፡ በኋላ ሰለሱ፡ "ታማኝ ምስክር" ይለዋል። ታማኝ ምስክር ማለት፡ ነብይ ነው። እንዲሁም፡ ካህን ነበር... አሁንም ካህን ነው፡ ሲመጣም፡ ንጉስ ይሆናል።

191 ከቻላልችሁ፡ የዮሐንስ ራዕይ 15:3 አንብቡ፡ በዮሐንስ ራዕይ 15:3 ላይ መመልከት ትችላላችሁ። እንክፈት እና... ንጉስ ሊሆን ከሆነ፡ ሲመጣ ንጉስ ሊሆን ከሆነና ምን እንደሆነ እንየው። አሁን ወደ ራዕይ፡ ምዕራፍ 15 ከ—ቁጥር 3 እንሂድ።

**ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ፡ *ሥራህ* ታላቅና ድንቅ ነው፡ የቅዱሳን ንጉሥ ሆይ፡ መንገድህ ጻድቅና እውነተኛ ነው፡ እያሉ፡ የእግዚአብሔርን ባሪያ የሙሴን ቅኔና፡ የበጉን ቅኔ ይዘምራሉ።**

192 እሱ በምድር ላይ ምን ነበር? ነብይ። ህዝቡ ነብይ መሆኑን እንዴት አወቁ? ነቢይ የሆነውን፡ የመሲሑን ምልክት ሰላደረገ። አቤት፡ የጌታ ስም የተባረከ ይሁን! እሱን እንዴት ሳቱት? ምክንያቱማ ሌላ ነገር ይፈልጉ ስለነበር ነው። እርሱ ግን የመሲሑን ምልክት አደረገ፡ መሰማትም እምቢ አሉ። እርሱም ነብይ ነበር።

193 ሙሴም ሲናገር፡ "ጌታ አምላካችሁ እንደ እኔ ያለ ነብይ ያስነሳላችኋል። ይህንን ነብይ ካልሰሙ፡ ከህዝቡ መካከል ይቆረጣሉ አላቸው።"

194 በምድር ላይ ነብይ ነበር፡ አሁን፡ እሱ ምን ነበረ? "የእግዚአብሔር ቃል ታማኝ ምስክር።" ኣሜን። የተገለጠው የእግዚአብሔር ቃል ነበር።

195 ቅዱስ ዮሐንስ፡ 1ኛው ምዕራፍ።

**በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።**

**ቃልም ሥጋ ሆነ፡ በመካከላችንም አደረ፡...**

196 ስለ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ቃል እውነተኛ እና ታማኝ ምስክር ነበር። እርሱ ቃል ነበር፡ የእግዚአብሔር ቃል ነበር። እርሱም፡ ቃል ስለ ሆነ፡ ነብይ ነበር። የእግዚአብሔር ቃል በእርሱ ዘንድ ይፈሳልና። ጉዳዩን ብቻ ይናገር ነበር። "አብ እንዳደርገው ከሚያሳየኝ በቀር፡ በራሴ ምንም ማድረግ አልችልም። ሥራውን የምሠራ እኔ አይደለሁም። በእኔ የሚኖረው አብ ግን እርሱ ሥራውን ይሠራል። እኔና አባቴ አንድ ነን። አባቴ በእኔ ውስጥ ነው፡" ማደሪያ የሆነው፡ ሰው የሆነው፡ ኢየሱስ እንዲሁ ተናገረ።

197 እግዚአብሔር ብዙ የማዕረግ ሰሞች አሉት፡ ጆሆቫ፡ ጆሆቫ-ጂሬ፡ -ራፋ፡ -ምናሴ። ኦህ፡ ብዙ! ሰባት የመቤዠት፡ የውህደት ሰሞች አሉት። እሱ ብዙ ማዕረጎች አሉት፡ የሳሮን ጽጌሬዳ፣ የሸለቆው አበባ፣ የንጋት ኮከብ፣ አባት፣ ልጅ፣ መንፈስ ቅዱስ። ያ ሁሉ አለው። ይሁን እንጂ አንድ የሰው ሰም አለው። እግዚአብሔር አንድ ሰም ብቻ ነበረው፡ እርሱም "ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ።"

198 ሲወለድ፡ ክርስቶስ፡ ጌታ ተባለ። ከሰምንት ቀን በኋላ፡ መንፈስ ቅዱስ ሰሙን "ኢየሱስ" ብሎ ጠራው። እናቱ አስገረዘችው፡ "ኢየሱስ፡" ተባለ። ሲወለድ ክርስቶስ ነበረ።

199 ለምሳሌ፡ እኔ ብራንሃም ሆኜ ተወለድኩ። ሰወለድ ብራንሃም ነበርኩ፡ "ዊልያም" ብለው ሰም አወጡልኝ።

200 አሜን። ሲወለድ አዳኝ፡ ክርስቶስ ሆኖ ተወለደ። ሰምንት ቀንም ሲሆነው፡ "ኢየሱስ" የሚባል ሰም ተሰጠው። እርሱም፡ የተገለጠ የክብር ጌታ ነበር። ስለዚህ፡ በመካከላችን የተገለጠ የክብር አምላክ፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ኦህ፡ ይኸው ነው እርሱ!

201 በምድር ላይ፡ ነብይ ነበር። በክብር፡ ካህን ነው። ሲመጣ፡ ንጉስ ነው። ኦህ! ባረከኝ።

ነቢይ፡ "የቃሉ ታማኝ ምስክር።"

"በገዛ ደሙ በእግዚአብሔር ፊት፡" ካህን ነበር።

ንጉሥ፡ "የቅዱሳን ንጉሥ።" የአለም ንጉስ፡ አይደለም። የቅዱሳን ንጉሥ ነው። በሰዎች ላይ ምድራዊ ነገሥታት አሉን። እኛ ግን ንጉሥ፡ እና፡ መንግሥትም አለን። ህይወታችን የተለየው ለዚህ ነው።

202 ከረጅም ጊዜ በፊት እንዳልኩት፡ ሰለ ባለቤቴ፡ አንዴ ወደ ሱቅ እየሄድን ነበር እና ከሞላ ጎደል፡ ተአምር አየን። በበጋ ወቅት ነበር፡ እና አንዲት ሴት ቀሚስ ለብሳ ነበር። እኔም "እንግዳ ነገር ነው፡" አልኳት። "ካሜራዬ ቢኖረኝ፡ የሴትየዋን ፎቶ አነሣ ነበር፡" አልኳት። አያችሁ? ምክንያቱም... አያችሁ፡ ከነዚህ ሴቶች ሁሉ፡ እንዴ እመቤት፡ ቀሚስ ለብሳ ያየናት የመጀመሪያዋ ሴት እሷ ነበረች።

203 እሷም ጠየቀችኝ፡ "ቢሊ፡ ቆይ፡ ህዝባችን ቀሚስ የሚለብሰው፡ ለምንድነው፡ እንዲህ ልበሱ——ተብለን ነው? "

204 እንዲህ አልኳት፡ “ህዝባችን አይደለም። የእግዚአብሔር ህዝብ ነው። የእግዚአብሔር ህዝብ ደግሞ፡ ቅድስና ይጠበቅበታል።”

“ታዲያ፡ እነርሱስ ቸርች ይሄዱ የለምን፡” አለች?

205 “**እዚያ** ጋር ያለች እመቤትም ዘማሪ ናት፡ አንድ ቸርች ትገባለች፡” አልኳት።

“ታዲያ፡ እንደዚያ፡ ለምን ሆነ? ”

206 “የተሻለ ትምህርት ስላላገኙች” አልኳት። እውነቱ ያ ነው።

207 ያ የሰጋዊ ቤተክርስትያን ነው፡ በዚህ ሳምንት የምናየው ይሆናል፡ መንፈሳዊ ቤተ ክርስትያን፡ እና ስጋዊ ቤተክርስትያን። መጽሐፍ ቅዱስ በራእይ 17 ላይ ያደርጉታል ተብሎ እንደተጻፈባቸው፡ ሁሉም ወደ ማሚ ቤተ ክርስቲያናቸው፡ እየተመለሱ ነው። አሁን፡ ሁሉንም እየተመለሱ፡ እንደ መደራጀት፡ እያረጋቸው ይገኛል። “እኛ፡ **እከሌዎች** እንባላለን… ተደራጅተናል። **እንዲህ** ነን **እንዲያ** ነን።” ከመጀመሪያ እንዲህ አልነበረም። ሥልጣን ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን አውጥተው በቢሾፕ ወይም በጳጳስ ላይ እያደረጉት ነው። እግዚአብሔር ግን በቤተክርስቲያኑ፡ በህዝቡ መካከል ነው፡ በሁሉም ቦታ፡ እራሱን በምእመናን ይገለጣል። በዚህ ዘመን ግን…

እንዲህ አለች፦ “ታዲያ፡ እኛ አሜሪካውያን አይደለንም’ዴ? ”

208 “አይ እኛ እዚህ እንኖራለን እንጂ፡ አሜሪካውያን አይደለንም። እኛ ክርስቲያኖች ነን። መንግሥታችን ከላይ ነው፡” አልኳት።

209 እና ህይወታችን ከላይ ከሆነ፡ ድርጊታችንም እንደዚያው ከላይ ነው። ምክንያቱ፡ ህይወታችን… የመጣው ከተቀደሰ ስፍራ ነው። የተለየ ነው። ልብሳቸው ይለያል። በላይ ያሉ ሴቶች ጸጉረ ረጃጅም ናቸው። ፊታቸው ላይ ማኒኩር አይጠቀሙም። ቁምጣዎችም—አይለብሱም። እነሱ—ቀሚሶችን፡ እና ረጅም ልብሶችን፡ እና መጎናጸፍያቸውን ይለብሳሉ። ረጅም ፀጉር፡ እና ሌላ አላቸው። ስለዚህ—ከላይ የሆነውን፡ ተፈጥሮ፡ በእኛ ዘንድ ይንጸባረቃል።

210 ወንዶቹ አያጨሱም፡ አያኙኩም፡ አይዋሹም፡ አይሰርቁም። መንፈሳቸው፡ ከተቀደሰ ስፍራ፡ ስለመጣ፡ የቅድስና ስራ እንዲያደርጉ ያደርጋቸዋል፡ እርስ በእርስ እንደ ወንድም ይተዋወቃሉ። አሃ-ሃህ። ይኸው ነው።

211 እኛ የመንግስት ልጆች ነን፡ ንጉስም አለን። እርሱም የቅዱሳን ንጉስ ነው። **ቅዱስ** የሚለው ቃል “የተቀደሱት” ከሚል የወጣ ቃል ነው። አንድ ሰው የተቀደሰ ሲሆን፡ ክርስቶስ የሆነው፡ መንፈስ ቅዱስ ወደ ልባቸው ይመጣል ንጉስም ይሆናቸዋል። ኦህ፡ ማይ! ይህ ቤት መምታት አለበት። ኦህ! የተቀደሠ የእግዚአብሔር ዕቃ ሲዘጋጅ… ንጉስ የሆነው፡ ክርስቶስ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ መጥቶ ይገባል። ንጉስም… የራሱ ግዛት አለው። አሜን። ሁለንተናህም በቅዱሳን ንጉሥ ይገዛል። በመንግሥቱ! በምድር ላይ ያለ መንግሥት ሁሉ ይናወጣል፡ በአቶሚክ ኃይል ይፈርሳል። “እኛ ግን የማይናወጥ መንግሰት አለን፡” ይላል መጽሐፍ ቅዱስ። አሜን። የቅዱሳን ንጉስ፡ እርሱ ነው።

212 የክርስቶስን መዓርጎች በመጽሐፍ ቅዱስ፡ እና በምድር ላይም፡ እንድታስተውሉት እፈልጋለሁ። በምድር ላይ፡ ነብይ ነበር። ታምናላችሁ? ነቢይ ቃል ነው። ያንን እናውቃለን። **ነቢይ** ማለት “የቃሉ መለኮታዊ ተርጓሚ” ማለት ነው። መለኮታዊው ቃል ተጽፏል፡ ነቢዩም በውስጡ የእግዚአብሔር መለኮታዊ

መንፈስ አለው። እንደምታውቁትም፡ በብሉይ ኪዳን ነብይ “አምላክ፡” ይባል ነበር። ስንቶቻችሁ ይህን ታውቃላችሁ?

213 ኢየሱስም፡ “አማልክት ከተባሉ… በሕጋችሁስ… ‘አማልክት ናችሁ፡’ ተብለው የለምን? የእግዚአብሔር ቃል ለመጣላቸው፡ ለእነርሱ፡ ማለት ነብያት ‘አማልክት’ ናችሁ ከተባለ፡ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላልኳችሁ እንዴት ትኮንኑኛላችሁ? ”

214 ምክንያቱ፡ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ እርሱም “አምላክ፡” ተብለዋልና፡ የእግዚአብሔር ቃል በእርሱ ዘንድ ነበርና። ስለዚህም **ነቢይ** የሚለው ቃል፡ “የእርሱ ትርጉም—ከምንም ጋር መቀላቀል የለበትም።” አያችሁ? እንዴ እግዚአብሔር… እንዲህ ካለ፡ “ከእናንተ፡ መንፈሳዊ፡ ወይም ነቢይ የሆነ ማንም ቢኖር፡ እኔ እግዚአብሔር እናገረዋለሁ። የተናገረው ከተፈጸመ፡ እኔ ከእርሱ ጋር ነኝና፡ እርሱን ስሙት። ካልተፈጸመ ግን፡ እኔ አልላኩትምና፡ አትሰሙት።” የማወቂያው መንገድ ያ ነው። ከዚያ በኋላ፡ ደግሞ፡ የቃሉ መለኮታዊ ትርጓሜ ከዚህ ለቤተክርስቲያን ከተሰጠው የመጨረሻው መገለጥ ጋር መገጣጠም አለበት።

215 ሁሉን የሚገዛ አምላክ፡ እርሱ ነው። በምድር ላይ፡ ነብይ፡ ማለት ንስር ነበር። ነብይ እንደ ንስር እንደሚቆጠር ስንቶቹ ታውቃላችሁ?

216 ንስር አሉ ከምንላቸው አእዋፋት ጠንካራው፡ እና ኃይለኛው ወፍ ነው። የአንዳንዶቹ ክንፎቻቸው ከጫፍ እስከ ጫፍ ድረስ፡ አስራ አራት ፊት ይዘረጋል። እጅግ ከፍ ብሎ ስለሚበር ሌላ አይነት ወፍ ሊከተለው ቢሞክር፡ ይሰነካከላል፡ ላባዎቹ ተነቃቅለው ሊሰነጣጠቅ ይችላል። ለምን? በልዩ ሁኔታ ስለተፈጠረ። ወደ ላይ ሲወጣ ምንን እያደረገ እንዳለ ማየት ካልቻለ መውጣቱስ ምን ይጠቅመዋል? ስለ ጭልፊት ዓይን ታወራላችሁን? የንስር ዓይን ማየት አለባችሁ።

217 ጭልፊት፡ ዶሮ ሊያይ ይችላል። ትክክል ነው። ዛሬ ጭልፊቶች አንዳንዶቹ የሚያጋጥማቸው ነገር ይኸው ነው። እሃ-ሃህ። ይሄውላችሁ፡ ልንገራችሁ፡ ንስር በኃይል ይወጣል፡ ጭልፊት ሊከተለው ቢሞክር፡ ይታፈናል። ይሞታል። ንስር ወደሚወጣባቸው ህዋዎች መግባት አይችልም።

218 ከወጣ በኋላ፡ እጅግ ከርቀት ማየት የሚያስችሉት፡ አይኖች አሉት። ስለዚህም እግዚአብሔር **ነቢያቱን** “ንስሮች፡” በማለት የሚጠራው ስለዚህ ነው። ንስር ነው፡ ወደላይ ይወጣል፡ ከርቀትም፡ ማየት ይችላል።

219 ክርስቶስም፡ በምድር ላይ፡ ንስር ነበር። ሲሞት፡ ካህን ነበር፡ ስለዚህ ያም በግ አደረገው። ልክ ነው? ዳግመኛም ሲመጣ፡ ንጉሥ ነው፡ ስለዚህም አንበሳ ይሆናል፡ አሜን፡ የይሁዳ ነገድ አንበሳ ነው። ኣሜን። እርሱ ንስር፡ በግ፡ እና አንበሳ ነው፤ አሜን፡ አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ፤ ነቢይ፡ ካህን፡ እና ንጉስ፤ የነበረው፡ ያለው፡ የሚመጣውም፤ ሁሉን ቻይ፡ አልፋ እና ኦሜ፤ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ፡ የዘላለም አምላክ።

220 እናንተ እንዲህ የምትሉ፡ የተወደዳችሁ የካቶሊክ ሰዎች ሆይ፡ ልጠይቃችሁ፡ “የእግዚአብሔር ዘለአለማዊ ልጅነት፡ እግዚአብሔር፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ዘለአለማዊ ልጅነት ከእግዚአብሔር ጋር።” እንዱህ አይነት ቃል እንዴት ትላላችሁ? እኔ የሰባተኛ-ክፍል፡ መሃይም ሆኜ እንኳን፡ ከዚያ የበለጠ

አውቃለሁ። ልጅ የሚል ቃል ጅማሬ ሊኖረው ግድ ይላል። ልጅ ከሆነ እንዴት ዘለአለማዊ ይሆናል? ዘላለማዊነት መጀመሪያም መጨረሻም የለውም። ስለዚህ፡ ጅማሬ ያለው ሆኖ፡ ልጅ፡ ዘለአለማዊ ልጅ ሊሆን አይችልም፡ ምክንያቱም ዘላለማዊ ልጅ የሚባል ነገር ስለሌለ። ልጅ መጀመርያ አለው፡ ስለዚህ ዘለአለማዊ አይሆንም።

221 አያችሁ፡ እርሱ ዘለአለማዊ አምላክ ነው፡ እንጂ ዘለአለማዊ ልጅ አይደለም። ክብር! ሁሉን የሚገዛ፡ ጀሆቫ-ጂሬ፡ ጀሆቫ-ራፋ፡ ስጋ ሆነ፡ “በእርሱ የመለኮት ሙላት በስጋ አደረ።”

222 በበዓለ ሃምሳም ቀን፡ ያ የእሳት ዓምድ በሰዎች ላይ በወረደ ጊዜ፡ እራሱን እንደከፋፈለ፡ አስተውላችኋል? በእያንዳንዳቸውም ላይ የእሳት ልሳኖች ታዩ። እንደ ልሳን የመሰለ፡ እሳት፡ በእያንዳንዱ ላይ ወረደባቸው። እግዚአብሔር ምን እያደረገ ነበር? እራሱን ለቤተ ክርስትያን እያከፋፈለ፡ በእያንዳንዳቸው፡ በሴቶች፡ በወንዶች፡ እና በሁሉም ዘንድ፡ ሰጠ፡ የመንፈሱ አካል፡ በቤተ ክርስትያኒቱ ዘንድ መከፋፈሉ ነበር።

223 ሰው እንዴት መጥቶ፡ “ቅዱስ ሰው ጳጳሱ ነው። ቅዱሱ ሰው ኤጲስ ቆጶሱ ነው” እንዴት ይላል? ቅዱሱ ሰው መንፈስ ቅዱስ፡ በእኛ ዘንድ ያለው ክርስቶስ ነው። ምእመናን የሚናገሩት ቃል የላቸውም እንዴት ትላላችሁ? እያንዳንዳችሁ የምትናገሩት ነገር አላችሁ። እያንዳንዳችሁ የምትሠሩት አላችሁ። እያንዳንዳችሁ መልእክት መሸከም አለባችሁ። ክብር!

224 መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ሃምሳ ቀን ራሱን ከፈለ። እግዚአብሔር፡ ራሱን ከፋፈለ። “እኔ በአብ እንዳለሁ፡ አብም በእኔ እንዳለ፡ እኔ በእናንተ፡ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ በዚያ ቀን ታውቃላችሁ።”

225 “በዚያ ቀን፡” መንፈስ ቅዱስ፡ “ከሁሉ በላይ፡ ከሁሉ ጋር፡ በሁሉ በኩል።” አሜን። ይኸው ነው። መንፈስ ቅዱስ በሚፈልገው በማንኛውም ቦታ፡ እና በማንኛውም ሰው የመንቀሳቀስ መብት አለው። ቢሾፕ ወይም ቄስ የሚሉትን መውሰድ አይጠበቅብህም። ካህናችን፡ የእውነት፡ ሊቀ ካህናችን እርሱ ነው። አሁን፡ ነብይ፡ ካህን፡ ኣና ንጉስ።

226 አሁን፡

> **እና... ከታመነውም ምስክር:... ከሙታንም በኩር፡ የምድርም ነገሥታት ገዥ ከሆነ:... (ወደዚያ እንገባበታለን።) ... ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን። ለወደደን፡ ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን፡**

227 በነገራችን ላይ፡ **ላጠበን** የሚለው ቃል፡ በግሪክኛ ቃል “መፈታት፡” ይለዋል። ከምናችን ፈታን... በኃጥያታችን ምክንያት፡ በምድር ታሰረን ነበርን። ማየት የማንችል፡ መሰማትም የማንችል፡ ስለ መንግሥተ ሰማያትም ሆነ ስለ ምንም ሐሳብ አልነበረንም። ደሙ ሲወርድ ግን፡ ገመዱን ቆርጦ ፈታን። ኦህ!

228 እንዴ ያነበብኩት ታሪክ አለና፡ ይህም... ከዚህ ርዕስ ጋር ይሄዳል። አንድ ገበሬ ቁራ ያዘና አሰረው። “ለሌሎቹ ቁራዎች ለትምህርታቸው አደርገዋለሁ፡” ብሎ አሰበ። ምስኪኑን ቁራ፡ በገመድ፡ እግሩን አሰረው፡ ምስኪን እጅግ ተራበ። መራመድ እስኪያቅጠው ድረሰ፡ ተዳከመ።

229 አንዳንድ ድርጅቶች፡ እና አብያተ ክርስትያናት፡ ህዝቡን እንዲህ አሰረዋል። “አይቻልም! መሄድ የምትችለው ርቀት፡ **ይህ** ነው። የተአምራት ቀናት አልፈዋል።” አዎ። በቃ ታሰረሃል። ይኼው ነው። “መንፈስ ቅዱስ የሚባል ነገር የለም። እንደ ቀድሞው በልሳኖች መናገር አይችልም።”

230 ኧረ አምላክ ነው። “ትናንትናና፡ ዛሬም፡ እስከዘላለም ያው ነው፡” ዕብራውያን 13፡8፡ እርሱ በሁሉም አብያተ ክርስትያናት የሚኖር ነው። የጠዋቱ ክፍለ ጊዜ ሲያበቃ እንረዳዋለን። አያችሁ? እርሱ በእያንዳንዱ ቤተ ክርስትያን ዘመን የሚኖር፡ አምላክ ነው። በእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ እና በህዝቡ ውስጥ ለዘለአለም... ይኖራል። አሁን፡ በውስጣችን፡ የዘላለም ሕይወት አለንና።

231 ስለዚህ፡ ይህ ተቋም አሰሮት ነበረ፡ አያችሁ፡ “ታዲያ፡ የተአምራት ዘመን’ኮ አልፏል። መለኮታዊ ፈውስ የሚባል ነገር የለም።” ምስኪኑ ቁራ በጣም መራመድ እስኪከብደው ድረስ እየተንገዳገደ ነበር።

232 አንድ ቀንም አንድ ደግ ሰው መጣና፡ እንዲህ አለ፡ “ታውቃለህ፡ ይህ ምስኪን ቁራ፡ በጣም ያሳዝናል። ምናልባት፡ ቦቆሎ እንኳን ያገኝ ይሆናል፡ ግን መኖርያው ያቺ ብቻ ናት። የሚበላ ነገር ሊኖረው ይገባል። ከቦቆሎ በቀር ሌላ አያውቅም፡ ዝም ብሎ ይበላል። ስለዚህ... ” ቢላውን... ቢላውን አወጣና ምስኪኑን ቁራ ፈታው።

233 አያችሁ፡ ሌሎች ቁራዎች መጡና፡ መጥተውም፡ “ጆኒ ቁራው፡ ና እንሂድ። ወደ ደቡብ እንሂድ። ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ እየመጣ ነው፡” አሉት።

234 ምን እንደተፈጠረ ታውቃላችሁ? ቁራው ከተመደበበት ክልል በላይ መውጣት አልቻለም። “እኔ ይህን አልችልም። በዚህ ዘመን ላለነው፡ ለእኛ አይደለም። ይህን ማድረግ—አንችልም እና፡” አለ። አያችሁ? አሁንም የታሰረ እስኪመስለው ድረስ በጣም ረጅም ጊዜ ታሰሮ ኖሯል። አያችሁ?

235 የብዙ ሰዎች ችግር እንደዚህ ነው፡ በአሮጌትዋ ጋለሞታ እናት፡ በእምነት መመሪያዎቿ እና በኃይማኖት ተቋም ታሰራችኋል፡ እርሷም፡ የምታስተምራችሁ፡ “ኢየሱስ ክርስቶስ ያው አይደለም። ፈውስ ብሎ ነገር የለም። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የለም። እንደዚህ አይነት ነገሮች የሉም።” እነዚህን ስታስተምራችሁ ቆየች። አሁንም መታሰራችሁን እስክታሰቡ ድረስ ለረጅም ወቅት ታሰራችሁ ቆይታችኋል።

236 ደጉ ሰው፡ ማለት ክርስቶስ፡ እኛን አጥቦ ከኃጢአታችን ነፃ እንዲያወጣን ደሙን ሰጠ። ኃጢአት ምንድን ነው? ማንም እንዲነግረኝ እጠይቃለሁ። ኃጢአት ምንድን ነው? **ኃጢአት** “አለማመን ነው።” ትክክል። “ያላመነ አሁን ተፈርዶበታል።”

237 ነጻ እንዳትሆኑ የሚከለክላችሁ ኃጢአትህ ብቻ ነው። ምክንያቱ እግዚ አብሔር ከአለማመናችሁ ፈትቶአችኋል፡ እናንተ ግን አሁንም በእምነት መመሪያዎች መታሰራችሁን ታስባላችሁ። በረሃብ መሞት፡ አያችሁ፡ ዙርያውን ትንገዳገዳላችሁ፡ “እኔ ፕሪስባይቴሪያን ነኝ። እኔ ሜቶዲስት ነኝ። ባፕቲስት ነኝ። (ቸርች ኦፍ ክራይስ ነኝ)፡ ‘የተአምራት ዘመን አልፏል። እንደዚህ ያለ ነገር የለም፡’” ብለውኛል።

238 አንተ ምስኪን የተራበ ቁራ! በዛሬው ማለዳ ወዲህ ለምን አትወጣም? ለምን አትበርም? ሃሌ ሉያ! "በማለዳ ክንፍ ተነሥና፡ ፈውስ በክንፎቿ ወደያዘች፡ የጽድቅ ፀሀይ ብረር።" አሜን። በቃ። ወንድም፡ እህት ሆይ፡ ያ ነው። አቤት! "ልጁ ነጻ ያወጣው ሁሉ፡ በእውነት ነጻ ነው።" አዎን፡ ወዳጄ!

239 "ፓስተራችን፡ ግን... " ምንም መናገር አያስፈልግም። መጽሐፍ ቅዱስ "ነጻ ናችሁ፡" ብሎናል። ትክክል። ነጻ ናችሁ።

"ቤተ ክርስቲያናችን ግን... "

240 ይህም፡ ቁረጡት። "በገዛ ደሙ አጥቦ፡ ከኃይማኖት ተቋማችን ነፃ አውጥቶናል፡" ለራሳችን እንድናስብ፡ ለራሳችንም እንድንሠራ፡ ለራሳችንም እንድንነጋገር፡ እና ለራሳችን እንድንሠራ ነፃ አድርጎናል።

241 "እሺ፡ አሁን ወደ ፓስተሩ ሄጄ እንደገና መጠመቅ እንዳለብኝ ብነግረውስ፡ ምን ይላል... "

242 "ነጻ ነህ፡" የተባልከውስ? ታውቃላችሁ፡ መገለጥ ነው። ነጻ ናችሁ። በጣም ጥሩ።

243 **እንደዚህ** ባለው በተበጠበጠ ጨው "በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡" የተረጫችሁ ከሆናችሁ፡ ልክ አይደለም። አዎን፡ ወዳጄ። ዛሬ ጠዋት ዝግጁ የሆነ፡ ውሃ የሞላ፡ ገንዳ እዚህ አለ። አያችሁ?

244 ስለዚህ፡ ከአሁን በኋላ ነጻ ናችሁ። ነጻ ናችሁ፡ ምናልባት ግን ላይታያችሁ ይችላል። ዛሬ ጠዋት ግን፡ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ልንገራችሁ፡ "የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ እንቀበል ዘንድ፡ ከኃጢአት፡ እና ከአለማመን ፈታን።" በነጻነት፡ ሂዱ!... ሌላ ቸርች የምትለውን ነገር አትቀበሉ። እግዚአብሔር የተናገረውን ተቀበሉ። እርሱ ማን እንደሆነ የገለጠው መገለጡ ይህ ነው።

245 "ሁሌ ስለ እግዚአብሔር አብ ሳስብ፡ ባለ ረጅም ነጭ ጺም፡ እና ባለ ነጭ ጸጉር ይመስለኛ ነበር፡ ልጅ ደግሞ ባለ መካከለኛ-ዕድሜ፡ መንፈስ ቅዱስ የመልካም ዕጣ ልጅ ይመስለኛ ነበር።" ወንድሜ፡ ያ ጣኦት ነው። በሶስት አማልክት የምታምኑ ከሆናችሁ የጣኦት አምልኮ ነው።

246 ፊተኛይቱ ትእዛዝ፡ ፊተኛይቱ ትእዛዝ ምንድን ናት? "እስራኤል ሆይ፡ ስማ፡ እኔ ጌታ አምላካችሁ፡ አንድ አምላክ ነኝ።" በቃ።

247 እርሱ አንድ አምላክ እንጂ፡ ሦስት አማልክት አይደለም። በሶስት አገልግሎቶች የኖረ፡ በሶስት መዓርጎች ያገለገለ። ነብይ፡ ካህን፡ እና ንጉስ ነው። ንስር፡ በግ፡ እና—አንበሳ ነው። የሸለቆ አበባ፡ የሳሮን ጽጌሬዳ፡ የሸለቆ አበባ፡ የንጋት ኮከብ፡ የዳዊት ሥርና ዘር። ከ A እስከ Z ነው። አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ ነው። እሱ ያ ሁሉ ሲሆን፡ ግን አንድ ነው። አንድ አምላክ ነው። አንድ አምላክ አለ፡ እነዚህ ግን እርሱ የሚጠራባቸው መዓርጎች ናቸው።

248 ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ገጾች ይሁን ከታሪክ፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፡ በጥልቅ ውሃ ውስጥ፡ "በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ" እስክታጠምቅ ድረስ በሌላ አልነበረም።

249 ገጾቹን ወይም የትኛውም ይሁን ነገር ካያችሁ፡ ጽፋችሁ ያዙትና፡ ዛሬ ማታ፡ አሳዩኝ፡ እኔም በዚህ ቤተ ክርስትያን፡ ለሰዎች የተሳሳተ ትምህርት ያስተማረ፡ "ግብዝ ነኝ እያልኩኝ እወጣለሁ።" አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል፡

ወይም ከታሪክ፡ የተረጋገጠ ታሪክ ካሳያችሁኝ፡ ማለት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰዎች፡ “በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡” መጠመቃቸውን የሚያሳየኝ ከሆነ። ወይም፡ አንዲት ቃል-... ወይም፡ ከታሪክ፡ አንዲት ገጽ፡ ከታሪክ አንቀጾች፡ እስከ የኒቂያዋ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስትያን ጉባኤ “በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡” የተጠመቀ ማንም ሰው አለ ከተባለ አምጡልኝ። ኑ፡ አምጡልኝ፡ እና በጀርባዬ ላይ ምልክት ሰክቼ በጄፈርሰንቪል እዞራለሁ፡ እናንተም፡ ከኋላዬ ጥሩምባ ትነፋላችሁ። ከኋላዬ “ሰዎችን የሚያስት፡ ሐሰተኛ ነብይ፡” ብየ እለጥፋለሁ።

250 አንተም፡ ፓስተር፡ ዛሬ እዚህ ያለኸው፡ ያንን ማድረግ ከቻልክ፡ እኔ አንተ ላይ እንዳደርግ ልትፈቅድልኝ ይገባል። አየህ? ናና፡ አሳየኝ። ነገር ግን ትፈራለህ።

251 አሁን፡ ይህ ምንድን ነው? **ይህ** መገለጥ ነው። **ይህ** መገለጥ ነው። ይህም መንፈስ ቅዱስ፡ ማለት ክርስቶስ፡ መልእክቱን ወደ አብያተ ክርስቲያናት እየላከ ነው። ሰሙት። ሰሙት። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ይህ ነው።

252 ይህ የገባው የት ነው? ካልተበሳጫችሁ፡ በዚሁ ሳምንት፡ ቀጥሉበት፡ እና—የኒቂያ ጉባኤ ታያላችሁ። ሃይስሎፕን **ቱ ባቢሎኖስ** ፈትሹት። አንብቡ...

253 የጆሲፈስ ታሪክም፡ ደህና ነው፡ ስለ ክርስቶስ የጻፈው ግን አንዲት አንቀጽ ብቻ ናት፡ እንዲ አለ፡ “ኢየሱስ የሚባል ሰው እንደነበረ፡ ሰዎችን እየፈወሰ ይዞር ነበር። በኋላም—ሞተ፡ ማለት፡ ማለቴ፡ ጲላጦስ ገደለው፡ ወይም—ደግሞ፡ ሄሮዶትስ፡ አስገደለው። ደቀ መዛሙርቱም ሄዱና፡ ሥጋውን ሰርቀው ሸሸጉት። ከዚያም በየሌሊቱ እየሄዱ ትንሽ ትንሽ እየቆራረጡ በሉት።” “የሰው ስጋ ተመጋቢዎች ነበሩ፡” ይላቸዋል። ይህ ግን፡ የጌታን እራት ስለሚወስዱ ነው፡ አያችሁ። ሥጋዊ አእምሮ! ጆሴፈስ ሊሰማም አይገባውም።

254 **ፎክሰስ ቡክ ኦፍ ዘ ማርቲርስ** ግን አንብቡት። ጥሩ ነገር አለው። **ፎክሰስ ቡክ ኦፍ ዘ ማርቲይርስ፡** ሰንቶች አንብባችሁታል? የእውነት። ዘ ፐምበርስ **እርሊ ኤጅ**፡ ወይም—ሃይስሎፕስ **ቱ ባቢሎንስ**፡ ወይም—አንዳንድ እውነተኛ። ወይም፡ አለን—የምንለው ትልቁ የኒቂያ ጉባኤን ነው፡ ቅድመ-ኒቂያ ጉባኤ እና የኒቂያ ጉባኤ ነው። በዚያ ውስጥም ብትፈትሹ፡ የተጠቀሰ፡ አንድም ሰው አታገኙም።

255 መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፈትሻችሁ በእነዚያ መዓርጎች የተጠመቀባቸው አንድ ሰው፡ ማለት “በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ” ሰም፡ የተጠመቀ ካለ መርምሩ። ሦስት አማልክትን ያመላክታልና። ጣኦታዊ ባዓል ነው። ካቶሊካዊነትም በዓለም ላይ—ጣኦታዊ የክርስትና ቅርጽ ብቻ ነው። ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ማርቲን ሉተር፣ ጆን ዌስሊ፣ ባፕቲስት፣ ፕሪስባይቴሪያን፣ ወዘተ ወጡ።

256 በመጨረሻው ዘመን ግን፡ እውነትን እንደገና የሚከፍት በር ተዘጋጅቷል፡ ይህም፡ “መጽሐፍ ቅዱስ፡” እና በመጨረሻው ዘመን በምድር ላይ ስለሚመጣው ታላቁ ነቢይ ይናገራልና። እኛም እንደሚመጣ እናምናለን። ጠብቁት። ቤተ ክርስትያንም ይኖረዋል። ይህን፡ ገና እናየዋለን።

257 አሁንም—አስታውሱ፡ ይህ መገለጥ ነው። ከዚያም መቀነስ አትችሉም። ይህ፡ ከባድ ፈተና ነው! በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ሰው፡ አንድም ቦታ “በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ” ሰም የተጠመቀ ካለ ፈትሹ፡ ወይም

ስለ ሐጢአታቸው ስርየት፡ በውኃ የተረጩ ሰዎች ካሉ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፈልጉ። በጭራሽ የለም። ስለዚህም ማንም ይሁን ሰው፡ ከዚህ በፊት ቢጠመቁም አይገደኝም፡ መንፈስ ቅዱስ ለመቀበል፡ "በኢየሱስ ክርስቶስ" ስም፡ እንደገና ለመጠመቅ፡ መምጣት አለባቸው።

258 የሐዋርያት ሥራ 19፡ "ጳውሎስ በላይኛው አገር አልፎ ወደ ኤፌሶን መጣ፡ አንዳንድ ደቀ መዛሙርት አገኘ።" ታላቅ ጉባኤ እያደረጉ ነበርና... እናንተ ደቀ መዝሙር ሆይ፡ አላቸው። አጵሎስ የሚሉትን የተለወጠ ጠበቃ፡ ይከተሉ ነበርና፡ በመጥምቁ በዮሐንስ ያመነ ባፕቲስት ነበረ፡ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ከቅዱሳት መጻሕፍት የተረዳ ሰው ነበረ።

259 ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 18 ላይ አቂላንና ጵርስቅላን፡ አይቷቸው አለፈ። ከዚያም ከአቂላ እና ከጵርስቅላ ጋር፡ እራት ለመብላት፡ ወይል ሌላ ነገር ለማድረግ ሄደ። እና ስለዚህ ታላቅ ሰው ነገሩት። እነርሱም ሊሰሙት አብረው ሄዱ። በዚያች ሌሊት አዳመጠው። እንዲህ አለው፡ "በጣም ደህና ነው። በጣም ጥሩ ነው። ጥሩ ነው። ግን፡" አላቸው፡ "ካመናችሁ ወዲህ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?"

260 ባመንን **ጊዜ** መንፈስ ቅዱስን ተቀብለናል ብላችሁ የምታምኑ፡ እናንተ ምስኪን ባብቲስቶችስ?

ያለው'ኮ፦ "ካመናችሁ **ወዲህ** መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?"

"ኧረ እንዲህ የሚል ቃል የለም፡" አለኝ አንዱ።

261 በደንብ እቃወማለሁ። የተረጋገጠው፡ የግሪክ እና የእብራይስጡ፡ ከእኔ ጋር ይዤዋለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ በግሪክ፡ እና በሁሉም፡ ዕብራይስጥ፡ በአረማይክም ጭምር ይላል። ሦስቱም የሚሉትን፡ ይዤዋለሁ፡ እንዲህ ይላል፡ "ካመናችሁ **ወዲህ** መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?" ልክ ነው። "ካመናችሁ ወዲህ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?"

262 እነርሱም፡ "መንፈስ ቅዱስ እንዳለስ እንኳ አላወቅንም፡" አሉት።

ታዲያ "በማን ስም ተጠመቃችሁ፡" አላቸው?

263 አሉትም፡ "ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ባጠመቀ ሰው በእርሱ ተጠመቅን። በዮሐንስ ጥምቀት ተጠመቅን አሉት፡" እንደው፡ እኛም በተመሳሳይ ወንዝ፡ "በተመሳሳይ ሰው።"

264 ጳውሎስ እንዲህ አለ፡ "ያ አሁን አይሰራም። ያጠመቀው ለኃጢአት ስርየት ሳይሆን፡ ለንስሐ ብቻ ነው።"

265 አሁን፡ አንዳንዶቻችሁ አሃዳውያን—የምትጠመቁበት መንገድ፡ ስሕተት ነው። ጥምቀታችሁ፡ ለመዳን ነው ትላላችሁና። ንስሓው፡ እና ደሙ እንጂ፡ ውኃ ማንንም ሰው አያድንም። ጥምቀት ለዳግም መወለድ አይደለም። አይደለም፡ ወዳጄ። ዳግም መወለድ የሚመጣው ከመንፈስ ነውና። ጥምቀት ግን—ስለ ውስጠኛው ዳግም መወለድ የሚደረግ ውጫዊ ምስክርነት ነው። አያችሁ? በጣም ጥሩ። እስተውሉ።

266 እንዲህ አላቸው፦ "ካመናችሁ ወዲህ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?" እንዲህ አሉት...

“መንፈስ ቅዱስ እንዳለስ እንኳ አልሰማንም፡” አሉ።

ታዲያ “እንዴት ተጠመቃችሁ፡” አላቸው?

“በዮሐንስ ጥምቀት፡” አሉት።

267 እርሱም አላቸው፡ “ዮሐንስማ በንስሓ ጥምቀጥ፡ እናንተ በእርሱ ታምኑ ዘንድ፡ በበጉ፡ ሊመጣ ባለው መሰዋዕት፡ ማለት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ታምኑ ዘንድ፡ ‘የንሰሓን ጥምቀት እያጠመቀ መጣ።’” ይህን በሰሙ ጊዜም፡ ዳግመኛ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ። ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜም መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ በልሳኖችም ተናገሩ፡ ትንቢትም ተናገሩ።

268 ያ መጽሀፍ ቅዱስ ካልሆነ ንገሩኝ፡ ወይም በአድስ ኪዳን ውስጥ፡ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በቀር በሌላ መንገድ የተጠመቀ አንድ ሰው ካለ ልየው። አሳዩኝ።

269 ቅዱስ አጋቦስ፡ እና ሌሎች ብዙዎችም ነበሩና፡ እነዚህም—እስከ ኒቂያ ጉባኤ—ዘመን ድረስ የተጠመቁ ናቸውና፡ እያንዳንዳቸውም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ። ሚሽነሪዎቹ ሁሉ መሰኩን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አረሱት።

270 የኒቂያው ጉባኤ በመጣ ጊዜ ግን፡ ሦስት አማልክት መከተላቸው ግድ ሆነ። ጳውሎስን መርጠው... ወይም ጁፒተርን መረጡና፡ ጳውሎስ አሉት። ቬነስን መርጠው፡ ማርያም አሏት። አስቀድመው ብዙ አማልክት የነበራቸው ናቸው፡ ሁሉም ዓይነት ቅዱሳን እና ሌላም ሁሉ ነበሯቸው፡ ስላሴአዊ ጥምቀትም ፈብርከው ለፕሮቴስታንቶች መገቡት። እነርሱም እስከአሁን ድረስ ይጋልቡታል።

271 ሲመሽ የሚበራው ብርሃን ግን አሁን መጥተዋል። ነብዩም ሲናገር “ሲመሽ ብርሃን ይሆናል፡” ብሏል።

> ሲመሽ ብርሃን ይሆናል—ይሆናል፡
> የክብርን መንገድ በእውነት ይገኛል፡
> በውኃው መንገድ፡ የዛሬ ብርሃን፡
> በኢየሱስ ስም ላይ እየተቀበርን።
> ወጣት ሽማግሌ፡ ሁሉም ንሰሃ ይግባ፡
> መንፈስ ቅዱስ በእርግጥ እንዲገባ፡
> የምሽቱ ብርሃን መጥቷል፡
> እግዚአብሔር እና ክርስቶስ አንድ መሆናቸው ተረጋግጧል።

272 ታምናላችሁ? ጴጥሮስም፡ በበዓለ ኃምሳ ቀን እንዲህ አለ፡ “የእስራኤል ቤት ሆይ፡ ይህ በእናንተ ዘንድ፡ የታወቀ ይሁን አለ፡ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን፡ እግዚአብሔር፡ ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው ይታወቅ፡” 2ኛው ምዕራፍ 36ኛ ቁጥር። አዎን። “እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን፡ እግዚአብሔር፡ ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው። የእስራኤል ቤት ሁሉ፡ በእርግጥ ይወቅ።”

273 እዚህ በዘሃውስ ኦፍ ዴቪድ፡ በቅርብ ጊዜ ነው ከአንድ አይሁዳዊ ጋር ተነጋግረን፡ እንዲህ አለኝ፡ “እናንተ አሕዛብ እግዚአብሔርን በሦስት ከፍላችሁ ለአይሁዳዊ መስጠት አትችሉም። እኛ ከዚያ በተሻለ እናውቃለንና።”

274 እኔም አልኩት፦ "እውነት ነው፡ ራባይ። እኛም እግዚአብሔርን በሦስት አልከፈልንም።" "ነቢያትን ታምናለህን፡" አልኩት?

"በደንብ፡" አለኝ፡

"ኢሳይያስ 9:6ን ታምናለህን፡" አልኩት?

"አዎን፡" አለኝ።

"ነቢዩ ስለ ማን ነበር የተናገረው፡" አልኩት?

"መሲሕ።"

"መሲሑ ከእግዚአብሔር ጋር ምን ግንኙነት ይኖረዋል፡" ብዬ ጠየቅኩት?

"እራሱ እግዚአብሔር ይሆናል፡" አለኝ።

እኔም፡ "ልክ ነው።" አሜን አልኩት።

አየህ፡ እውነቱ ይህ ነው። አየህ፡ በሦስት ክፍል መስንጠቅ አይቻልም።

275 እናንተ ሚስዮናውያን... ከመካከላችሁ አንዳችሁ ወደ አይሁዶች ትሄዳላችሁ፡ ይህ **እዚህጋ** የተቀመጠው ሰውዬ፡ እንደሚሄድ አምናለሁ። "አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ" ለአይሁድ ለመስጠት አትሞክር። "ከኒቂያ ጉባኤ፡" እንደመጣ ያውቀዋልና፡ ወዲያው ይመልስልሃል። ይህን አይሰማህም። ነገር ግን ሥጋ የለበሰው እግዚአብሔር ወዴት እንደ ሆነ እንዲያይ ተወው፡ አምላክ ማለት እርሱ ብቻ ነው። እግዚአብሔር፡ በሰው አምሳል ሥጋ ሆኖ ሊቀድሰን፡ በመካከላችን ኖረ፡ እርሱ ራሱ በመንፈስ ቅዱስ መልክ መጥቶ፡ ያሰወግድልን ዘንድ። አባት የሆነው፡ እግዚአብሔር፡ ማለት መንፈስ ቅዱስ፡ አንድ ሰው ነው።

276 መጽሐፍ ቅዱስ—በኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ፡ በማቴዎስ ምዕራፍ 1 ላይ እንዲህ ይላል፡ እንዲህም አለ፡ "አብርሃም ይስሐቅን ወለደ። ይስሐቅ ያዕቆብን ወለደ።" እያለ ይወርዳል፡ እና፡ እስኪ... ላንብበውና፡ ምን እያወራሁ እንዳለሁ ይገባችኋል። የማቴዎስ ወንጌል፡ ምዕራፍ 1። ከዚያም... አሁን በ 18 ኛው ቁጥር እንጀምር።

**የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንደዚህ ነበረ፡ እናቱ ማርያም፡ ለዮሴፍ በጣጨች ጊዜ፡ ሳይገናኙ... የማን ልጅ ጸንሣ ተገኘች...**

277 "'የእግዚአብሔር አብ'"? እንደዚያ ይላልን? [ጉባኤው ሁሉ፡ "አይልም" አለ።—እርታዒ።] የማን ልጅ ጸንሣ ተገኘች? ["'የመንፈስ ቅዱስ።'"] የ... [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ።] እግዚአብሔር አብ አባቱ ነው ብዬ አልነበረም'ዴ? ታዲያ፡ እግዚአብሔር፡ አብ እና መንፈስ ቅዱስ፡ አንድ መንፈስ ናቸዋ፡ ካልሆኑ ግን ሁለት አባቶች ነበሩት ማለት ነው።

**እጮኛዋ ዮሴፍም፡ ጻድቅ ሆኖ ሊገልጣት ስላልወደደ፡ ... የህዝብ መቀጣጫ ሊያደርጋት፡ ሰላልወደደ... በሰውር ሊተዋት** አሰበ።

**እርሱ ግን ይህን ሲያስብ፡ እነሆ፡ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፡ እንዲህም አለ፡ የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፡ ከእርሰዋ የተፀነሰው... ከመንፈስ ቅዱስ ነውና፡ እጮኛህን ማርያምን፡ ለመውሰድ አትፍራ...**

278 “‘እግዚአብሔር አብ’”? ነውን? [ጉባኤው ሁሉ፡ “አይደለም። ‘መንፈስ ቅዱስ ነው አሉ።’”—አርታዒ።] “መንፈስ ቅዱስ።” ታዲያ የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ማን ነበር? [“መንፈስ ቅዱስ።”] መንፈስ ቅዱስ። በእናንተ ውስጥ ያለው ምንድን ነው? [“መንፈስ ቅዱስ።”] ታዲያስ፡ እግዚአብሔር፡ አብም፡ ደግሞ ነው። አይደለም’ዴ? አዎን።

**ወንድ ልጅም ትወልዳለች፡ ስሙንም ኢየሱስ ትለዋለህ፡...**

279 እግዚአብሔር አባት **ይኸው፡** እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ **ይኸው፡** እግዚአብሔር ልጅ **ይኸው፡** እያችሁ፡ ሦስት አማልክት ማለት ይህ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን አይናገርም። እነዚህ ሁለቱ አንድ መሆን አለባቸው፡ ወይም ሁለት አባቶች ነበሩት። እያችሁ? ሁለት አባቶች ሊኖሩት ግን አይችልም። እናንተ ታውቃላችሁ።

**ልጅም፡ ትወልዳለች፡ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና፡ ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።**

**በነቢይ** ከጌታ ዘንድ፡ **እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፡ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል፡**

**... የተባለው ይፈጸም ዘንድ፡ ይህ ሁሉ ሆኖአል፥ ትርጓሜውም፡ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር**፡ የሚል **ነው።**

280 ይህ የማቴዎስ ምዕራፍ 1 ነው።

281 ማቴዎስ 28፡19 ላይ፡ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ተናግሯል፡ “ሂዱ፡ በአባት፡ በልጅ፡ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ።” የአባት፡ የልጅ፡ የመንፈስ ቅዱስ ስም ማን ነው? ኢየሱስ ክርስቶስ ይባላል፡ አዎን።

282 “ጆን እና ሜሪ በደስታ ኖሩ፡” የሚል፡ የፍቅር ታሪክ ካነበባችሁ። ጆን እና ሜሪ እነማን ናቸው? ወደ ታሪኩ መጀመሪያ ተመለሱና፡ እወቁ።

283 እንደዚህ አይነት ስም ከሌለ፡ የለምና፡ “አብ፣ ወልድ፣ ወይም መንፈስ ቅዱስ፣” ማን ነው፡ የማን ስም ነው? ወደ ኋላ፡ ወደ ታሪኩ መጀመርያ ተመለሱ፡ እና ስለ ማን እንደተናገረ ተመልከቱ።

284 ጴጥሮስ፡ በበዓለ ሃምሳ ቀን፡ እንዲህ አለ፡ “ንስሐ ግቡ፡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ፡ እያንዳንዳችሁ ‘በኢየሱስ ክርስቶስ’ ስም ተጠመቁ።” መገለጡን አግኝቶት ነበርና።

ዮሐንስ መገለጡን አውቆታል።

285 መገለጡ ኢየሱስ **ነበረ**፡ እራሱን በቅዱሳን መጻሕፍት ውስጥ ተርኳልና፡ “የነበረውና፡ ያለው፡ የሚመጣውም፡ ሁሉንም የሚገዛ እኔ ነኝ።” ዋው! በጣም ጥሩ።

286 አሁን፡ 7ኛውን ቁጥር፡ አሁን በፍጥነት፡ ‘ከመውጣታችን በፊት፡ የምንችለውን ያህል እንፍጠን። ሁሉንም የሚገዛ።

**... ኃይል-... ክብር እና ኃይል ለዘለአለም ይሁን። አሜን።**

**ለአምላኩና... ለአባቱም፡ ነገስታት እና ካህናት እንድንሆን... ላደረገን ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን። አሜን።**

287 ያንን መገለጥ እንዴት እንደተገለጠ፡ እዛ ላይ አያችሁት? ስለ እግዚአብሔር... ሰዎች ጭንቅላታቸውን እያከኩ ፀጉራቸውን እየነጩ፡ ወዘተ፡ ይህ ሦስት፡ በአንድ፡ "አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ" ምን እንደሆነ ለማወቅ ይሞክራሉ።

ጸጉራችሁን አትንጩ ጭንቅላታችሁንም አትከኩ። አይናችሁን ወደላይ አንሡ። መገለጥ ከላይ ነው። ይህም እውነት ነው። "አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ውዱስ፡" አለመሆኑን ራሱ ይገልጣል። አንዱ አምላክ የኖረባቸው ሦስት አገልግሎቶቹ ናቸው።

288 ብቻውን፡ "መንፈስ፡" የነበረበት አገልግሎት ነበረ፡ ምክንያቱ የሰው ልጆች ከበታች ነበሩና፡ ቀጥሎ እርሱ የሚኖርበት፡ የራሱ ደም የሚሰራበት፡ ለራሱ የሆነ ሰጋ አደረገ፡ ይህ ግን በኤደን ገነት እንደነበረው፡ በፆታዊ ግንኙነት ሳይሆን፡ የተፈጠረ አካልን በመፍጠር ነው። በድንግልና-በተወለደ ሥጋ ነው፡ በእርሱ እናምን ዘንድ የቀደሰን፡ እና ከአለማመናችን የፈታን ደም ሰጠ። እኛም፡ ያንን ሰናደርግ፡ ወደ ልባችን እንቀበለዋለን፡ ያም እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ፡ እግዚአብሔር ማለት፡ አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ ነው። አያችሁ? ልክ እንደ ነቢይ፣ ካህን፣ እና ንጉስ፣ ያው ተመሳሳይ ነገር ነው። በጣም ጥሩ።

289 አሁን፡ 7ኛው ቁጥር፡ ይሄኛው አዋጁ ነው። ያን አዋጅም፡-

**እነሆ፡ ከደመና ጋር ይመጣል፡ ዓይንም ሁሉ፡... የወጉትም ያዩታል፡ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ።**

290 ኦህ! ምን ያህል ጊዜ ቀረን? መልካም ነው። ሃያ... ሰላሣ ደቂቃ ትሰጡኛላችሁ? [ጉባኤውም "አዎን፡" አለ።—አርታዒ።] ትፈቅዳላችሁ? ["አሜን።"] በጣም ጥሩ። እሺ፡ እንግዲህ፡ ነገ... ዛሬ ማታ፡ ቀሪውን **የፍጥሞ ራእይ** እናየዋለን፡ ዛሬ ማታ። ዛሬ፡ አዋጁን እንጨርሰዋለን።

291 እሺ! ደስ አላችሁ ወይ? [ጉባኤውም "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] ይህ የጥንቱን መጽሐፍ ቅዱስ ወደዳችሁት ወይ? ["አሜን።"] መገለጥ ነው። ምን፡ ምንድን ነው? እግዚአብሔር፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ወርዶ፡ መጋረጃውን ገፈፈውና፡ እንዲህ አለ፡ "ይኸው እርሱ፡ ነቢይ፡ ካህን፡ ንጉስ፣ አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ፣ የነበረው፡ ያለው፡ የሚመጣው። እነዚህ ሁሉ ነገሮች፡ እግዚአብሔር ነው።"

292 አሁን፡ መጋረጃውን እንገፈፈውና፡ ለጥቂት ደቂቃዎች፡ ጌታ እየረዳን፡ ከዓይኖቻችን መጋረጃውን እናንሳ። እና ይህን ያዙ...

**እነሆ፡ ከደመና ጋር ይመጣል፡...**

293 እሺ፡ ከምን ጋር ይመጣል? "ከደመናዎች ጋር።" ምን ዓይነት ደመና? የክብር ደመና። እነዚህ ነጎድጓዶች፡ የዝናብ ደመናዎች ሳይሆኑ፡ የክብር ደመና።

294 ጴጥሮስና ሌሎቹ በተራራ ላይ ራእዩን ባዩ ጊዜ ደመና ሲጋርደው፡ በምን አይነት ደመና እንደተሸፈነ ታያላችሁ። ልብሱ አበራ። በደመና፡ በእግዚአብሔር ኃይል ተሸፈነ።

295 ኦህ፡ ወደነዚህ የቤተ ክርስትያን ዘመናት ስንገባ፡ እነዚህን እናያቸዋለን። እላችኋለሁ፡ እንደው ማሰቡ ብቻ—የውስጤን፡ ያደርሳል። ስለ መምጣቱ...

አሁን እኛ እየኖርንበት ያለውን ቀን ሳየው፡ ከእርሱ መምጣት በቀር፡ የቀረ ተስፋ የለም።

296 አሁን ይህንን በፍጥነት እናየዋለን። አሁን አስታውሱ።

**... ዓይኖች ሁሉ ያዩታል፡...**

297 ይህ ማለት፡ ስለ ንጥቀት አይደለም፡ ነው ወይ? [ጉባኤው "አይደለም፡" አለ።—አርታዒ።] አያችሁ? ንጥቀት አልነበረም። ስለ መነጠቅ አልነበረም። ስለምን እያወራ ነው? ስለ ሁለተኛው መምጣት።

**... የወጉትም ደግሞ፡ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ።**

298 አሁን ወደ ኋላ ተመልሰን የተወሰነ ታሪክ እናያለን። ወደ ዘካርያስ እንመለስና፡ የዘካርያስን ምዕራፍ 12 እንመልከት። ዘካርያስ። በጣም ጥሩ።

299 "ጌታም በየቀኑ የሚድኑትን ወደ ቤተ ክርስቲያን ይጨምር ነበር።" ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መልካም መገለጥ ምንኛ ደስ ይለናል! ስለ እርሱ ደስ አይላችሁምን? አሁን፡ ይህንን በተቻለን በፍጥነት በመጽሐፍ መልክ አዘጋጅተን፡ ለሰዎች እናደርሳለን፡ ከዚያ በኋላ ክፍላችሁ ውስጥ፡ በጸጥታ እያነበባችሁ፡ ለብቻችሁ ሆናችሁ፡ ማጥናት ትችላላችሁ። በጣም ጥሩ።

300 ዘካርያስ፡ ዘካርያስ፡ አሁን የዘካርያስ ምዕራፍ 12። ይህን በእውነተኛ ጸሎት ሆናችሁ፡ ተቀበሉት። እና ይህን ማየት የምንፈልገው ስለ እግዚአብሔር ክብር ነው። አሁን፡ ወደ ዘካርያስ 12፡ በ9ኛው ቁጥር እንጀምር። በደንብ አዳምጡ። ስለሚመጣው እየተናገረ ነው። ዘካርያስ 12፡ ከ9 ቁጥር በ9ኛው እንጀምራለን።

**በዚያም ቀን...**

ዘካርያስ፡ ትንቢት ሲናገር፡ ከክርስቶስ መምጣት በፊት ከአራት መቶ ሰማንያ-ሰባት ዓመታት በፊት ነው።

**በዚያም ቀን በኢየሩሳሌም ላይ... የሚመጡትን አሕዛብ ሁሉ፡ ለማጥፋት እጋደላለሁ።** (አሰቡት።)

**በዳዊትም ቤት ላይ፡ በኢየሩሳሌምም በሚኖሩት ላይ፡ የሞገስንና የልመናን መንፈስ አፈስሳለሁ፡ ወደ እርሱም ወደ ወጉት ይመለከታሉ፡...**

301 እሺ፡ ወንጌል ወደ አይሁዶች የሚመለሰው መቼ ነው? የአህዛብ ሙላት ሲገባ፡ ወንጌል ወደ አይሁዶች ለመመለስ፡ ተዘጋጅቷል። አቤት፡ እንደው ችዬው፡ ይህ በዚህ ዘመን፡ እዚህ ጋር ከአሁን በኋላ ሊፈጸም ያለውን ነገር ለእናንተ መናገር በቻልኩ፡ አያችሁ። አያችሁ? ሊፈጸም ተዘጋጅቷል። በቤተ ክርስትያን ዘመን ውስጥ እናየዋለን። ይህም ታላቅ ነገር ለመፈጸም ዝግጅት ላይ ነው፡ ወደ ራእይ 11 ወደ እነዚያ ሁለቱን ነቢያት ይወስደናል፡ ኤልያስና ሙሴ ወደ አይሁዶች ተመልሰው ይመጣሉ። እናም ተዘጋጅተንበታል። ሁሉም ነገር ስርዓት እየያዘ ይገኛል፡ ተዘጋጅቷል። ይህ የአህዛብ መልእክት፡ አይሁዶች ወደ አሕዛብ እንዲመጡት፡ አሕዛብ ዳግመኛ ወደ አይሁዶች ይመልሱታል። ያኔ ንጥቀት ይፈጸማል።

302 አሁን ይህ፡ ከመከራ በኋላ፡ እንደሚመጣ አስታውሱ... ቤተክርስቲያን በመከራ ውስጥ አታልፍምና። ያንን እናውቃለን። መጽሐፍ ቅዱስም ይላልና። አያችሁ? በጣም ጥሩ።

303 እሺ፡ በእስራኤል ቤት ላይ (ምን፡) ያፈስሳል? የአሕዛብ ቤተ ክርስቲያን ከሄደች በኋላ፡ አያችሁ፡ ያንኑ መንፈስ ቅዱስን ያፈስዋል።

> **ወደ እርሱም** ወደ **ወጉት ይመለከታሉ፡ ሰውም ለአንድያ** ልጁ **እንደሚያለቅስ ያለቅሱለታል፡ ሰውም ለበኵር ልጁ እንደሚያዝን፡ በመራራ ኀዘን ያዝኑለታል።**
>
> **በዚያ ቀን—በመጊዶን ሜዳ... እንደ ነበረው እንደ ሐዳድሪሞን ልቅሶ... ታላቅ ልቅሶ... በኢየሩሳሌም ይሆናል።**
>
> **ምድሪቱም—ታለቅሳለች፡ እያንዳንዱ ወገን ለብቻው፡ የዳዊት ቤት ወገን ለብቻው፡ የናታን ቤት ወገን ለብቻው፡** እያንዳንዱም ቤት **ለብቻው፡** (በዳግም ምጽአቱ፡ በክብር ደመና ሲመጣ የሚሆነውን፡ ሲያዩት፡ የሚሆን ነገር ነው።)

304 እነዚያም የወጉት አይሁዶች ጊዜ ሲያዩት... መጽሐፍ ቅዱስ፡ በሌላ ስፍራ እነዚህ ቁስሎች ከወዴት አገኙት፡ እንደሚል ታውቃላችሁ።

"በወዳጄ ቤት፡" ይላቸዋል።

305 እርሱን እንደ መሲሕ ለካዱት አይሁዶች ብቻ፡ የሀዘን ጊዜ አይሆንም፡ ነገር ግን ኋላ ለቀሩት ለአሕዛብም የሀዘን ጊዜ ይሆናል፡ እርሱን በዚህ ዘመን እንደ መሲሕ አንቀበልም ብለው ለነበሩ... ላልተቀበሉት። ለቅሶ እና ዋይታ ይሆንባቸዋል። እንቅልፋምዋ ድንግል ዋይ ዋይ ትላለች። በመቅረዝዋ ዘይት አልፈልግም ያለችው ቤተ ክርስትያን ይህች ናት። አሥር ደናግል ወጡ፡ ሁሉም ጻድቃን ሰዎች ናቸው፡ አምስቱ ግን በመቅረዛቸው ውስጥ ዘይት ነበራቸው። ሌሎች አምስቱም ጥሩ ሰዎች፡ ጥሩ ሰዎች ነበሩ፡ ነገር መቅረዛቸው ውስጥ ግን ዘይት መያዝን ረሱ። "ልቅሶ ዋይታ፡ እና ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት፡ ወደ ውጭ ጨለማ ተጣሉ።"

306 እነሆ፡ "ዋይ ዋይ ይላሉ።" መጽሐፍ ቅዱስ እዚህ ጋር እንዲህ ይላል፡ "ልባቸው-እስኪሰበር፡ ድረስ፡ ዋይ ዋይ ይላሉ... "

307 እዚህ ላይ፡ ሌላ ማየት ከፈለጋችሁ፡ ዘፍጥረት 45፡ እሰጣችኋለሁ። እስቲ ለአፍታ ብቻ እንግባና፡ ያንን በዘፍጥረት... በዘፍጥረት ምዕራፍ 45 ላይ፡ ይመስለኛል። ይሄኛውን ወደዚህ ማምጣት እፈልጋለሁ፡ ዮሴፍ—ለወገኖቹ እራሱን የሚገልጥበት ነው። እና ይህን እንያዝና፡ በዚያ ዘመን የሆነውን ጥላ ወሰደን—እንመለከተዋለን፡ ከዚያ በኋላ አንድ ላይ እናያይዘዋለን።

> **ዮሴፍም በእርሱ ዘንድ ቆመው ባሉት ሰዎች ሁሉ ፊት... ሊታገሥ አልተቻለውም፡ ሰዎቹንም ሁሉ፡ ከፊቴ አስወጡልኝ ብሎ ጮኾ... ተናገረ።**

308 አሁን አስታውሱ፡ ዮሴፍ፡ እራሱን ሲያስተዋውቃቸው፡ "ሰዎቹንም ሁሉ ከፊቴ አስወጡልኝ፡" ብሎ ጮኾ።

> **ዮሴፍ ለወንድሞቹ ራሱን በገለጠ ጊዜ፡ በእርሱ ዘንድ የቆመ ማንም አልነበረም።**

**ቃሉንም ከፍ አድርጎ አለቀሰ፡ የግብፅ ሰዎችም ሰሙ በፈርዖን ቤትም** ተሰማ። (በጣም ሳይጮኽ አይቀርም።)

**ዮሴፍም ለወንድሞቹ፡ እኔ ዮሴፍ ነኝ፡ አባቴ እስከ አሁን በሕይወቱ ነውን አለ? ወንድሞቹም ይመልሱለት ዘንድ አልቻሉም፡ በፊቱ ደንግጠው ነበርና።**

**ዮሴፍም ወንድሞቹን፡ ወደ እኔ... ቅረቡ፡ አላቸው። ወደ እርሱም ቀረቡ። እንዲህም አላቸው፡ ወደ ግብፅ የሸጣችሁኝ...** እኔ ወንድማችሁ—**ዮሴፍ ነኝ።**

**አሁንም ወደዚህ ስለ ሸጣችሁኝ፡ አትዘኑ፡ አትቈርቈሩም፡ እግዚአብሔር ሕይወትን ለማዳን ከእናንተ በፊት ሰድዶኛልና።** (አቤት፡ እንዴት ያምራል!)

ይህ **ሁለቱ ዓመት በምድር ላይ... ራብ የሆነበት ነውና፡ የማይታረሰበትና...** የማይታጨድበት፡ **አምስት ዓመት** ገና **ቀረ።**

**እግዚአብሔርም በምድር ላይ ቅሬታን አስቀርላችሁ ዘንድ፡ በታላቅ መድኃኒትም አድናችሁ ዘንድ ከእናንተ በፊት ላከኝ።**

309 እስቲ አሁን ልውሰድና፡ ያንን ከ12ኛው ዘካርያስ ጋር፡ ለአፍታ ላነፃፅረው። አሁን፡ ያንን፡ በጥላ እናውቀዋለን። እኔ እንደሚመስለኝ፡ በጥላ ካስተማራችሁ፡ በጥላ—ሁሌም በትክክል ታገኙታላችሁ።

310 አሁን፡ ዮሴፍ፡ በተወለደ ጊዜ፡ በወንድሞቹ ዘንድ ተጠላ። ልክ ነው? አሁን ዮሴፍ በመንፈስ-የተሞላች ቤተክርስቲያንን እንደሚወክል፡ ላሳያችሁ እፈልጋለሁ። ዮሴፍ በወንድሞቹ ተጠላ። ለምን? መንፈሳዊ ስለ ነበር። ዮሴፍ ራዕይን ስለ ማየቱ ምንም ሊያደርግ አይችልም። ሕልሞችን ያልማል፡ እያችሁ፡ ሕልሞችም ይተረጉማል። በውስጡ የነበረ ነገር ነው፡ ምንም ማድረግ አይልም። በውስጡ ከነበረው በቀር ሌላ ምንም ማሳየት አይቻለውም። እንግዲህ፡ ወንድሞቹም፡ ያለ ምክንያት፡ ጠሉት። አባቱ ግን ነቢይ ስለነበረ፡ አባቱ ወደደው።

311 በኢየሱስ ላይ እንዴት እንደነበረ አያችሁ? እግዚአብሔር ልጁን ይወዳል። ወንድሞች ግን፡ ማለት ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ግን ጠሉት፡ በሽተኞችን ስለሚፈውስ፡ ትንቢት ስለሚናገር፡ ራዕዮችን ስለሚያይ፡ ትርጉምን ስለሚተረጉም። ምን ለማለት እንደፈለግኩ ተመልከቱ? “ያለ ምክንያት፡ ጠሉት።”

312 ዮሴፍንስ ምን አደረጉት? የሞተ አስመሰለው፡ ወደ ጉድጓድ ጣሉት። ሰባት ቀለማት ያሉት፡ በደም የተነከረ ልብስ፡ ወደ አባቱ ወሰዱለት...

313 በቀስተ ደመና ውስጥ ሰባት ቀለሞች ብቻ አሉ። ቀስተ ደመናው፡ እንደምናውቀው፡ ምናልባት፡ በኋላ፡ ማታ ላይ የምንማረው ይመስለኛል። ኢየሱስ፡ በላዩ፡ የነበረው ቀስተደመና፡ “በምስሉ እንደ ኢያስጲድ፡ እና እንደ ሰርዴስ ድንጋይ ቀስተ ደመና ነበር።” ቀስተ ደመና ቃል ኪዳን ነው።

314 ይህም በዮሴፍ ላይ የነበረ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ነው። ከዚያም ልብሱ ላይ ደም ላይ ነክረው፡ ወደ አባቱ ወሰዱለት። ይህም ለሞት ይገባ ነበርና። እና...

315 ነገር ግን ከጉድጓድ ውስጥ ተነሰቶ—ወደ... ለፈርዖን የተሸጠ፡ በግብጽም፡ በአንድ—ጀነራል ዘንድ ተጠበቀ። እርሱም በዚያ በነበረ፡ ጊዜ፡ በክፉ ተከሰሰ፡ እና ወደ እስር ቤት ወረወሩት። በዚያም ትንቢት ተናገረ፡ አንዱም ወዴት እንደሚሄድ ሁለተኛውም ወዴት እንደሚሄድ ለሁለት ሰዎች ነገራቸው፡ ጠጅ አሳላፊው—እና እንጀራ ጋጋሪው፡ ህልማቸውን ተረጎመላቸው።

316 ከዚያም ወደ ፈርዖን ቀኝ፡ ከፍ ከፍ ተደረገ። በዮሴፍ ብቻ በቀር፡ ወደ ፈርዖን መግባት የማይቻል ነበረ። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—እርታዒ።]

317 ይህ ምን። አሁን፡ ይህ... ዮሴፍ ለግብጻውያን በተሸጠ ጊዜ ነው። ዮሴፍ ያደረጋቸው ነገሮች ሁሉ፡ የክርስቶስ ጥላ መሆናቸውን፡ ተመልከቱ። ጠጅ አሳላፊውና ጋጋሪውን ተመልከቷቸው፡ ሁለቱም ሕልም አዩ። ኢየሱስም፡ በገዛ እስር ቤቱ ነበረ። ዮሴፍ በእስር እንደነበረ፡ አስታውሱ። ኢየሱስ በእስር ቤት የነበረው፡ (እንዴት ነው? ) በመሰቀል ላይ ተጠርቆ በነበረ ጊዜ ነው፡ በዚያም አንዱ ድኖ አንዱ ግን ጠፋ። ዮሴፍም፡ በገዛ እስሩ በነበረ ጊዜ፡ አንዱ ዳነ፡ አንደኛው ግን ጠፋ።

318 አሁን አስተውሉ። ኢየሱስ ከመጽቀል ከተወሰደ በኋላ፡ ወደ ሰማያት ከፍ ከፍ ተደረገ፡ በታላቁ መንፈስ፡ በጀሆቫ ቀኝ ተቀመጠ። “በእኔ በቀር ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚችል ማንም የለም።” **ሰላም ለኪ ማርያም አይሠራም**፡ **ቅዱስ** ሆይ የለም **ቅድሰት** ሆይ አይሠራም። ነገር ግን፡ “በሰው እና በእግዚአብሔር ባለው ብቸኛው መካከለኛ፡” በኢየሱስ ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔርን ሰም ይዞ፡ እግዚአብሔር፡ በመካከላችን ባደረበት በውብ ማደርያው ብቻ ነው። ለእግዚአብሔርም የሰው ሰም ተሰጠው። ለእግዚአብሔር የተሰጠ...

319 እዚ እዩ። በመጀመሪያ፡ አዳም... ከዚህ መውጣት አልቻልኩም። የሆነ ቦታ ላይ፡ አልገባ ያለው ሰው አለ መሰለኝ። ተመለከቱ፡ በመጀመሪያ... እስኪ በድጋሚ አንድ ነገር ላሳያችሁ። ይህን እንዳደርግ መንፈስ ቅዱስ እያሳሰበኝ ነው። ለአንድ ደቂቃ ከርዕሴ ወጣ ልበል። ልጅህ አዳም፡ ወደቀ የሚል፡ ሰበር ዜና ወደ አርያም በደረሰ ጊዜ፡ እግዚአብሔር መልአክ ላከን? ልጅ ላከን? ሌላውንስ ላከን? ልጁን ለመዋጀት፡ እራሱ፡ መጣ። ሃሌ ሉያ! እግዚአብሔር ከራሱ በቀር በማንም አልተማመነም። ስለዚህ እግዚአብሔር ሥጋ ሆነ፡ በመካከላችንም አደረ፡ ሰውንም በራሱ ዋጀ። ያ ነው... መጽሐፍ ሲናገር፡ “በእግዚአብሔር ደም፡” “ድናችኋል” ይላልና። እግዚአብሔር፡ በራሱ... ኃጢአትን ያስወግድ ዘንድ፡ ከመጋረጃው በስተጀርባ፡ የገዛ ደሙን ይዞ በፊቱ፡ ወደ ክብር ይገባ ዘንድ፡ በመጋረጃው ተጋረደ፡ በግ ይሆን ዘንድ፡ ሟች ሆነ፡ የማይሞተው አምላክ የሚሞት ሆነ።

320 አሁንም፡ ዮሴፍ፡ ወደ ግብፅ ወረደ። ከእስር ቤቱ፡ ወደ ፈርዖን ቀኝ ከፍ ተደረገ፡ በዚያም ተቆጣጣሪ ሆነ። በዮሴፍ ዘመንም ነገሩ ሁሉ ተሳካለት።

321 ኢየሱስ፡ ሲመለስም፡ ምድረ በዳው ሳይቀር እንደ ጽጌረዳ ያብባል። የብልጽግና ልጅ ነው፡ የዮሴፍ ጥላ ነው።

322 ዮሴፍን አስገቡት... ጄኔራሉ በቤቱ ውስጥ አኖረው፡ ሥራው ሁሉ፡ ተባረከ። ወደ እስር ቤት አስገቡት፡ እስር ቤቱ ሁሉ ተባረከ። ስራቸው ሁሉ፡ ተባረከ።

ከዚያ ከፍ በተደረገ ጊዜም፡ በፈርዖን ዘንድ፡ ከፈርዖን ቀጥሎ፡ የበላይ ከሆነ በኋላ፡ በዓለም ላይ ካሉት ሁሉ ይልቅ በግብፅ ያለው ነገር ሁሉ በለፀገ።

323 እርሱ ሲመለሰም፡ የብልጽግና ምድር ይሆናል። የጥንት ምድረበዳዎች ያብባሉ፡ ምግብ በሁሉ ዘንድ ይሆናል። እርሱ እንደ ንጉስ ሲመለስ፡ እኛም በህልውናው፡ ለዘለአለም ሰንኖር፡ ሁላችንም፡ በሳቅ እና በደስታ፡ በገዛ የበለስ ዛፋችን ሥር ማረፍ እንችላለን።

324 እርሱ የሰው ልጅ፡ ማለት ነቢይ ነበር። ኣሜን። እርሱ የሰው ልጅ፡ መሥዋዕት፡ ካህን ነበር። እርሱ የሰው ልጅ ነው፡ እንደ ንጉሥ፡ የዳዊት ልጅ ሆኖ በግርማው ዙፋን ላይ ተቀምጧል። የሰው ልጅ፡ እርሱ... እግዚአብሔር የሰው ልጅ ሆኖ ተገለጠ። ኃጢአትን ከዓለም ሊያርቅ፡ ወርዶ ሰው ሆነ። እንደ ነብይ፡ ሰው ሆነ። እንደ ካህን፡ ሰው ሆነ። እንደ ንጉሥ፡ ሰው ሆነ፡ የሰማይ ንጉሥ፣ የቅዱሳን ንጉሥ፡ የዘላለም ንጉሥ፡ ሁልጊዜ ንጉሥ ነበር፡ ሁልጊዜ ንጉሥ ይሆናል፡ የዘላለም ንጉሥ ይሆናል።

325 እንግዲህ፡ ዮሴፍን፡ አስተውሉት። ዮሴፍ ሲወጣ፡ ቀድሞ፡ ጥሩንባ ይነፋል። ሰዎችም እየጮኹ "ለዮሴፍ ሰገዱ፡" ይሉ ነበር። በምን አይነት ሰራ የቆየ ማንም ሰው፡ ጎዳናው ላይ ዕቃዎችን ሲሸጥ የቆየ ሰው፡ መለከት ሲነፋ፡ ጉልበት ሁሉ ይንበረከካል። እጁን ዘርግቶ ገንዘብ ሊቀበል የነበረ ሰው፡ ዮሴፍ እያለፈ ስለ ሆነ ግን፡ ጉልበቱን ያንበረክካል። ኦህ! የ-... አ—አ—አሰማተኛው መድረኩን ሊጀምር ሲል፡ ምን ያደርጋል? ማቆም አለበት። "ዮሴፍ እየመጣ ነው።" መለከት ተሰምቷልና።

326 ከነዚህ ቀናት አንድ ቀን፡ ሁሉም ነገር፡ ጊዜም ቢሆን፡ ይቆማል። "የእግዚአብሔር መለከት ሲነፋ፡ በክርስቶሰ የሞቱ ሲነሡ፡ ብሩህ ማለዳው፡ ውብ ሲሆን ለዘላለም።" ሁሉ ጉልበቱን ያንበረክካል። "ጉልበት ሁሉ ይንበረከካል፡ ምላሰም ሁሉ ይመሰክርለታል።"

ከአሁኑ ጀምሩት። "የአንዳንድ ሰዎች ኃጢአቶቻቸው ይቀድማቸዋል፡ ሌሎችም ይከተላቸዋል።"

327 አሁን ግን ምን እንደተፈጠረ አስተውሉ። እንዴት ያለ ክብር ነው! ዮሴፍ ያኔ... ከአሕዛብ ዘንድ አግብቶ ትዳር ከመሰረተ በኋላ፡ ልጆቹን፡ ኤፍሬምን ምናሴንም አገኘ። መጨረሻ ላይ አስተውላችኋል? ዮሴፍም... ያዕቆብ ኤፍሬምን ምናሴን ይባርክ ጀመር። የቀኝ እጅ በረከት ትልቁን ለመባረክ፡ እጁን መጫን በጀመረ ጊዜ፡ ኤፍሬምን በሰተቀኝ፡ ምናሴን በግራ አደረጋቸው። መጸለይ በጀመረ ጊዜ ግን፡ እጆቹ አጠላለፋቸው፡ በቀኙ በነበረው ፈንታ የቀኝ-እጅ በረከትን ለታናሹ ሰጠው።

328 ዮሴፍም አለው፡ "አባቴ ሆይ፡ እንዲህ አይደለም።" "ምናሴ ዘንድ እንደማድረግ በረከቱን በኤፍሬም ላይ አድርገሃል፡" አለው።

እርሱም "እግዚአብሔር እጆቼን አጠላለፈ፡" አለው።

329 ምን? ከቦክር፡ ማለት ከአይሁዶች፡ ከቀዳሚዎች-የእግዚአብሔር ምርጦች፡ ሙሽራን ለማግኘት፡ በመሰቀል በኩል በረከቱን ወደ አሕዛብ ተመለሰ። በረከት በመሰቀል በኩል፡ ከአይሁድ ወደ አሕዛብ ተሸጋገረ። ተጠላ፡ መሰቀሉን ተቃወሙት፡ በዚህም ምክንያት ከአሕዛብ ሙሽራን ወሰደ።

330 ዮሴፍም፡ ከዚህ በፊት፡ በዚያን ጊዜ... ስለ ወንድሞቹ ሰማ፡ እነርሱም... ማለት አይሁድ፡ ለብዙ ዓመታት ከህብረት ርቀው ቆይቷል።

331 አሁን ተመልከቱ። አሁን ወደ ዘካርያስ እየተመለስን ነው፡ ወደ ዋይታቸው፡ ወደ ለቅሶ እና ዋይታ። ቤተሰቦች እንኳን ከሌሎች ቤተሰቦች ለብቻቸው፡ እየወጡም፡ እንዲህ ይላሉ፡ "ይህ እንዴት አደረግን? እንዴትስ ልንፈጽመው ቻልን?" የተወጉትን እጆቹን አይተው፡ "የእጆችህ ጠባሳዎች፡ ከወዴት አገኘሃቸው?" ብለው እሱን የሚጠይቁት ጊዜ ነው። "እርሱ በደመና ይመጣል። የወጉትም አይኖች፡ ያዩታል። እያንዳንዱም ቤት ያለቅሳል፡ ዋይ ዋይም ይላሉ።" ምን ማድረግ እንደሚገባቸው አያውቁም።

332 ዮሴፍም... ወንድሞቹን ባያቸው ጊዜ። ታሪኩን ታውቁታላችሁ፡ ዕብራይስጥ ቋንቋ እንደማይችል ሆነና፡ ተርጓሚውን እንዲተረጉምለት አደረገ። እና ዕብራይስጥ እንደማይችል በመምሰል፡ መመርመር፡ ፈለገ። አንድ ቀን ግን፡ በስተመጨረሻው፡ ታናሽ ወንድሙን ባመጡ ጊዜ፡ አስተውላችኋልን? የዮሴፍን ነፍስ የነካው ቢንያም አይደል?

333 ዛሬስ፡ የእኛ ዮሴፍ፡ ኢየሱስን፡ ነፍሱን የሚነካው፡ ምንድነው? የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የጠበቀች በኢራን ውስጥ የቆየች፡ ያቺ ወጣት ቤተክርስቲያን። አሁን ግን አዲስ እንደተወለደ ህዝብ፡ ወደ ፍልስጤም ምድር ዳግም ተቃንታለች። ያቺ ባለ ስድስት-ቀስት የዳዊት ኮከብ፡ የአለማችን አንጋፋ ባንዲራ ያላት፡ አንዲት አገር በመጨረሻዎቹ ቀናት ተወልዳለች። እስራኤል ናት።

> ሌሎች እየፈረሱ፡ እስራኤል ነቅታለች፡
> የቅዱስ መጽሐፉ ምልክቶች አይታለች፡
> የአሕዛብ ዘመን አልቆ፡ ማረሻው ተላቆ፡
> "እናንተ፡ የተበተናችሁ፡ ወደ ቀያችሁ ተመለሱ።"
>
> የቤዛው ቀን ቀርቧል፡
> የሰው ልብ በፍርሃት ወድቋል፡ (ሁሉም ተመልከቷቸው፡ ቀውስ ሆኗል።)
> መንፈሱ ይሙላቹ፡ መብራታችሁ ይቆሰቆስ ያጥራ፡
> ወደ ላይ ተመልከቱ! ቤዛችሁ ቀርቧልና።
>
> ሐሰተኛ ነቢያት ይዋሻሉ፡ የእግዚአብሔርን እውነት ይክዳሉ፡
> ኢየሱስ ክርስቶስ አምላካችን አይደለም ይላሉ፡
> (ክብር!) መገለጥ ግን መጥቷልና።
> ስለዚህ ሐዋርያት በረገጡበት እንጓዛለን። (በሄዱበት ተመሳሳይ ቦታ።)
>
> የቤዛነት ቀን ቀርቦአልና፡
> የሰው ልብ በፍርሃት ወድቋል፡
> መንፈሱ ይሙላቹ፡ መብራታችሁ ይቆሰቆስ ይጥራ፡
> ወደ ላይ ተመልከቱ! ቤዛችሁ ቀርቧልና።

334 አቤት! አቤት፡ ዮሴፍ፡ ትንሹ ቢንያም ቆሞ ባየው ጊዜ! ያ ታናሽ ወንድሙ ነው። ወዲያ ማዶ... ? ... እርፎ የተቀመጠ፡ ትንሹን ቢንያም አይታያችሁምን? የአይሁድ፡ የምድር––ነገዶች፡ ክርስቶስ መምጣቱን አይተው፡ እነዚያ አንድ

መቶ አርባ-አራት ሺህ፡ እርሱን ለመቀበል ወደዚያ ተመልሰው ቆመዋል። እንዲህም ይሉታል፦ “እነሆ፡ የጠበቅነው አምላካችን ይህ ነው።” ያኔ የተወጋውን አይተው… “ከወዴት አገኘሃቸው? ”

እርሱም “በወዳጄ ቤት፡” ይላቸዋል።

335 ያለቅሱለታል ዋይ ዋይ ይላሉ። እያንዳንዱ ቤተሰብ፡ የዳዊት ነገድ እና የንፍታሌም እና ሁሉም፡ እያንዳንዱ ቤተሰብ፡ ራሳቸውን ይለያሉ፡ የወጉት ሁሉ በሰማይ ቆሞ እርሱን ሲያዩት፡ ለራሳቸው ያለቅሳሉ።

336 ያኔ መልእክቱ ምን ይሆናል? ዮሴፍ የተናገራቸውን ተመልከቱ። እርሱ ሲናገራቸው…

337 ሌላ ነገር ተመልከቱ። ዮሴፍ ልጆች በፊቱ በቀረባቸው ጊዜ፡ ሁሉንም ቃኛቸው፡ ዮሴፍም ቢንያምን አየው። ኤፍሬምን አየው፡ የቀሩትንም በዚያ፡ ጋድንና ሁሉንም አያቸው። አሥራ ሁለቱም ነገድ፡ አሥሩም ነገድ፡ በፊቱ ቆሙ። ሁሉንም እዚያ ቆመው አያቸው። ወንድሞቹ መሆናቸውን ያውቃል። ትንሹን ቢንያምን፡ ትኩር ብሎ ባየው ጊዜ ግን፡ ጉሮሮው መተናነቅ ጀመረው። እነዚህ የራሱ እንደሆነ አውቆ ነበርና። ምን አለ? “ሰው ሁሉ ይውጣ።” ሚስቱ እና ልጆቹ ምን ተደረጉ? ወደ ቤተ መንግስት ተወሰዱ።

338 የአህዛብ ቤተክርስቲያን በንጥቀት ወዴት ትሄዳለች? ወደ ቤተመንግሰት። ሙሽራዋ፡ ሃሌ ሉያ፡ ሙሽራይቱ ከምድር በንጥቀት፡ ትወሰዳለች። ከዚያም ሲመለስ፡ ራሱን ለወንድሞቹ ለአይሁድ፡ ለወጉት ለተቃወሙት፡ እራሱን በገለጠ ጊዜ፡ ሙሽራው በዚያ አልነበረችም።

339 ሚስቱ እና ወዳጆቹ፡ የቅርብ ጓደኞቹ—እግዚአብሔር-የላካቸው ወዳጆቹ ሁሉ፡ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ነበሩ። ባያቸው ጊዜም፡ ሰለነሱ እንዲህ አላቸው… አላወቁምና። እነርሱም አሉ፡ “ኡህ፡ ይህ ታላቅ ልዑል!” ሰላደረጉት ሰለእነዚህ ነገሮች፡ አንዱ ለአንዱ፡ ኡህ፡ ማለት ጀመሩ።

340 ኤፍሬም ይመሰለኛል፡ ኤፍሬም ሳይሆን፡ እንጃ አሁን ማን እንደነበረ ትዝ አይለኝም፡ እንዲህ—አለ፡ “እንደው፡ ወንድማችን ዮሴፍን፡ መግደል አልነበረብንም።” “እያችሁ፡ አሁን ዋጋችን እያገኘን ነው፡” አላቸው። ሮቤል፡ ሮቤል እንዲህ አላቸው፡ “ወንድማችንን መግደል አይገባንም ነበር፡” “ምክንያቱ፡ እንደምታዩት፡ ሰለ ሰራችን ዋጋችንን እያገኘን ነው፡” አላቸው።

341 ዮሴፍም በዚያ ቆሞ፡ ዕብራይሰጥ ይችላል ብለው አላሰቡም። እሱ ግን ያውቃል።

342 አንዳንዶች፡ መናገር አይችሉም አሉ… በልሳን መናገር ይችላል፡ በደንብ ይችላል። አዎን፡ ያውቀዋል። የአሕዛብ መንግሥት ስትገባ በልሳኖችና በትርጓሜ እየተናገረች ገባች፡ በወርቅ ራስ (የመጀመሪያው ራስ) ከመውደቁ በፊት። የመጀመሪያው የአህዛብ ዘመን እንዲያበቃ ያደረገው ምን ነበር? በግድግዳው ላይ ያልታወቁ የቋንቋዎች የእጅ ጽሁፍ፡ እና መተርጎም እና ምን እንደሆነ መናገር የሚችል ሰው መኖር። አሁንም በተመሳሳይ መንገድ ይወጣል። ኣሜን። በገባበት መንገድ በተመሳሳይ መንገድ ይወጣል።

343 እነሱ የሚናገሩትን ልሳኖች ሊረዳቸው እንደማይችል አሰበው ነበር፡ እሱ ግን በደንብ ያውቅ ነበር። “የደረሰብንን አየኸው? ” ባሉ ጊዜ፡

ዮሴፍም ባደረጉት ነገር መጸጸታቸውን ተመለከተ።

344 እርሱን ባለመቀበላቸው ሐዘናቸውን እና መጸጸታቸውን አይቷል፡ ስለዚህ ጉሮሮው ውስጥ መተናነቅ ጀመረው። ቤተክርስቲያኑን ከምድር ሊያበራት፡ ወደ ክብር ሊወስዳት ተዘጋጀ። ከዚያ ሲመለስ፡ የምድር ወገኖች ሁሉ ያለቅሳሉ።

345 ምን አደረጉ? ሮቤል፡ እና ሌሎች ሁሉ፡ ማልቀስ ጀመሩ፡ እንዲህ አሉ፡ "ኦህ! ኦህ!" ፈርተው እንዲህ አሉ፡ "አዎን እሱ ነው። በእጁ እንደወደቅን አሁን አወቅን። አሁን ይገድለናል። አሁን እሱ... ከብዙ ዘመናት በፊት ከእኛ የተለየ ዮሴፍ ነውና፡ አሁን እንደሚያጠፋን ተረድተናል። ወንድማችን ዮሴፍ፡ ራሱ ነው፡ አሁን በእጁ ወድቀናል።"

346 እንዲህ አላቸው፡ "ህይወት ለማትረፍ ስለፈለገ እግዚአብሔር ይህን አደረገ። በራሳችሁ አትዘኑ።"

347 እግዚአብሔር ምን አደረገ? አይሁዳውያን ኢየሱስን የተቃወሙት ለምን ነበር? ስለ እኛ፡ ስለ አሕዛብ፡ ስለ ስሙ የተጠራው፡ ህዝብ፡ የሙሽራይቱን ያስመልጥ ዘንድ፡ የአሕዛብን ቤተ ክርስቲያንን ሕይወት እንዲያተርፍ እግዚአብሔር ይህን አደረገ።

348 የተቃወሙት ወገኖች ሁሉ ያለቅሳሉ። በዋሻዎች፡ እና በአለት ንቃቃት ውስጥ፡ እና በነገሮች ውስጥ፡ "ደብቁን፡ ተራሮች ሆይ፡ በላያችን ውደቁ፡" ይላሉ። እነርሱን፡ ተቃወሙት። የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ። በእስራኤል ያለ እያንዳንዱ ቤተሰብ እራሱን ይለያል። "ለምን አደረግን? እሱንስ እንዴት ተቃወምነው? ቤተሰቦች አንዱ ከሌላው፡ ለየብቻቸው ያዝናሉ፡ እንዴት ይላሉ? የጠበቅነው አምላክ ይህ ነው። እነሆም ቆሟል። በእጆቹም፡ የሚስማር ምልክት አለበት፡ ይህን ያደረግነው እኛ ነን።"

349 ወንድሞቹም ተመልሰው በመጡ ጊዜ የተናገሩት፡ ይህ ራሱ ነበር እንዲህም አሉ፡ "እኛ የሸጥነው፡ ዮሴፍ ይህ ነው።"

እርሱም አላቸው፡ "እኔ እናንተ ወደ ግብጽ የሸጣችሁት፡ ወንድማችሁ፡ ዮሴፍ ነኝ።"

350 "ኦ!" ፈርተው ነበር። እነርሱም እያዘኑና እያለቀሱ፡ እርስ በርሳቸው እየተደባበቁ፡ "ምን እናድርግ?

351 እርሱም አላቸው፡ "በራሳችሁ አትዘኑ፡ ይህን ያደረገው እግዚአብሔር ነውና። እግዚአብሔርም እኔን አስቀድሞ ላከኝ።"

352 እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ፈጠረ፡ ነጭ ሰዎች፡ ጥቁር ሰዎች፡ ቡናማ ሰዎች፡ ቢጫ ሰዎች፡ ሁሉንም ሰዎች ፈጠረ። እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ ፈጠረ። አህዛብን ፈጠረ፡ አይሁድን ፈጠረ። ሁሉንም ፈጥሯል። ሁሉም ለክብሩ ነው። የአህዛብ ሙሽራን ለመውሰድ አይሁዶች መጣል ነበረባቸው።

353 የእነዚህ ጥላዎች ሁሉ ምክንያት ይህ ነበር። ስለዚህም የአህዛብ ሙሽራ እና ልጆቿም ከእርሷ ጋር፡ ያቺ የከበረች በበጉ ደም የታጠበች የጴንጤቆስጤ ቤተክርስትያን፡ በእነርሱም ውስጥ ባለው በትንሣኤ ኃይል ሁሉ፡ ተመልሶ መጥቶ እራሱን ለወንድሞቹ ለመግለጥ (ሌላውን ሁሉ ውጡልኝ፡) በሚልበት ጊዜ፡ አንድ ቀን በንጥቀት (በቅፅበት በዐይን ቅጽበት) ወደ ኢየሱስ መገኘት ትወሰዳለች።

354 እዚህ ጋር በመዝጊያ ላይ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል ተመልከቱ። ኦህ!

> **እነሆ፡ ከደመና ጋር ይመጣል፡ የወጉትም ዓይኖች ሁሉ ያዩታል፡** (አሁን የሚናገረው ስለ ሁለተኛው ምጽአት እንጂ ስለ መነጠቅ አይደለም) **የወጉትም ሁሉ...**

355 7ኛው ምዕራፍ፡ 1ኛው ቁጥር... ወይም፡ የ1ኛው ምዕራፍ 7ኛ ቁጥር።

> **... ዓይንም ሁሉ፡ የወጉትም ያዩታል፡ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ። አዎን፡ አሜን።**

356 ከዚያም ያንን ታላቅ ጥቅስ ሰጠ። ይህ ሰው ማን ነው? እርሱን ለመፈለግ ወደ እርሱ የሚሄዱት ይህ ሰው ማን ነው?

> **እኔ አልፋ እና ኦሜጋ ነኝ፡** ከ A እስከ Z፡ (የግሪክ A እና Z፡ የግሪክ ፊደል) እኔ ነኝ...

357 የሐዋርያት ሥራ 2:36፡ ጴ... ጴጥሮስም "ሰዎች ሊድኑበት ሌላ ስም ከሰማይ በታች የተሰጠ የለም፡" አላቸው። አይ፡ አይደለም፡ ሌላ ጥቅስ መጥቀሴ፡ ይቅርታ አርጉልኝ። እርሱ እንዲህ አለ፡ "ይህም እናንተ የሰቀላችሁት ኢየሱስን፡ እግዚአብሔር፡ ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው፡ የእስራኤል ወገን ሁሉ በርግጥ ይወቅ አላቸው።"

358 የዮሐንስ ወንጌል 14፡7 እና 12፡ ቶማስ እንዲህ አለ፡ "ጌታ ሆይ፡ አብን አሳየን፡ እና ይበቃናል።"

359 እርሱም አለው፡ "ይህ ሁሉ ዘመን አብሬህ ስሆን፡ አታውቀኝምን? " "እኔን ያየ አብን አይቷል። እኔና አባቴ አንድ ነን። 'አብን አሳየኝ፡' ለምን ትላለህ? " አለው።

360 አንድ ቀን ለአንድ ሴት ያንኑ ነገርኳት። ሴትዋም እንዲህ አለች፡ "ቆይ፡ አቶ ብራንሃም።" "አንተ እና ሚስትህም እኮ፡ አንድ ናችሁ፡" አለችኝ።

እኔም "በዚያ መንገድ ግን አይደለም፡" አልኳት።

"ይቅርታ ምን አልከኝ፡" አለችኝ።

"እኔን ታይኛለሽ ወይ፡" ብዬ ጠየቅኳት?

"በደንብ፡" አለችኝ።

"ሚስቴስ ትታይሻለች ወይ፡" ጠየቅኳት?

"አትታየኝም፡" አለችኝ።

361 "እንግዲያውስ፡ ሁለቱ ይለያያሉ። እርሱ ያለው፡ 'እኔን ያየ፡ አብን አይቷል፡'" ብሏልና። ስለዚህ ያ በቂ ነበረ።

362 ስለዚህ ማስታወሻ ለምትይዙ ሰዎች፡ በቅዱስ ዮሐንስ፡ ወይም አንደኛ ዮሐንስ 5፡7 እስከ 8 ላይ። አንደኛ ዮሐንስ 5፡7 እስከ 8 ድረስ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ኢየሱስ የሰጠውን ይህ ራእይ የጻፈው ሰው፡ የዚህ ተናጋሪውም ራሱ፡ እንዲህ አለ፡ "በሰማያት የሚመሰክሩ ሶስት ናቸው፡ አባት፡ ቃል (ቃል ሲባል ልጅ ነው)... አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ ናቸው፡ ሦስቱም አንድ ናቸው። በምድር

ላይ የሚመሰክሩት ሦስቱ ናቸው፡ ውሃ፡ ደም፡ እና መንፈስ፡ እና እነሱም በአንድ ይስማማሉ፡ አንድ አይደሉም፡ ግን በአንድ ይስማማሉ።"

363 ልጅ የሌለው አባት ደግሞ ሊኖረው አይችልም። መንፈስ ቅዱስ ከሌላችሁም አባት እና ልጅ ሊኖሯችሁ አይችሉም። በትክክል። ለእናንተ ግን… ውኃ፡ ደም፡ እና መንፈስ፡ እነዚህ ወደሱ ወደ ሰውነቱ ለመግቢያ የሚጥቅሙ ውህደቶች ናቸው።

364 ተፈጥሯዊ ልደት በሚፈጠርበት ጊዜ፡ አንዲት ሴት ልጅ በምትወልድበት ጊዜ የመጀመሪያው የሚሆነው ነገር ምንድን ነው? በመጀመሪያ ደረጃ፡ ውኃ ይፈሳል። ሁለተኛው ነገር፡ ደም ነው። ልክ ነው? የሚቀጥለው ነገር፡ መንፈስ ነው። ህጻኑ ትንፋሽ ይይዛል፡ መተንፈስ ይጀምራል። የተፈጥሮ መወለድን የሚያካትቱ፡ ውኃ፡ ደም፡ እና መንፈስ ናቸው።

365 መንፈሳዊ ልደትም፡ እንዲሁ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የውሃ ጥምቀት፡ በእምነት መጽደቅ፡ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን። ውኃ! የሚቀጥለው ምንድን ነው? ደም፡ መቀደስ፡ መጽዳት፡ እሷን ወደ ውጭ ማስወጣት።

366 እናንተ የናዝራውያን ሰዎች የወደቃችሁበት ቦታ ይህ ነው፡ ልክ ያን ያህል ሄዳችሁ ከዚያ በኋላ አትቀጥሉም። በመሠዊያው ላይ የተቀደሰው፡ ለአገልግሎት የተዘጋጀ ዕቃ፡ ነገር ግን በአገልግሎት ላይ ያይደለ ናችሁ። "ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ፡ ይጠግባሉና፡" ልጆች፡ "ብፁዓን ናቸው፡" ዕቃው የተቀደሰ ነው። ያ እውነት ነው።

367 ድንግል እንደ ማለት ነው። **ድንግል** የሚለው ቃል "ንጹህ፣ ቅዱስ፣ ያልተበረዘ፣ የተቀደሰ።" አምስቱ ዘይት ነበራቸው፡ አምስቱ የላቸውም፡ አምስቱ ተሞልተው ነበር፡ ሌሎቹ በመቀደስ የቀሩ ነበሩ። "ካመናችሁ **ወዲህ** መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን፡" እናንተ ባፕቲስቶች፡ ፕሪስባይቴሪያኖች?

"መንፈስ ቅዱስ መኖር አለመኖሩን እናውቅም።"

"ታዲያ፡ እንዴት ተጠመቃችሁ? " ኧሃ-እህ።

368 እጁን ከጫነባቸው በኋላ፡ ያን ጊዜ፡ ከዳኑና ከተቀደሱ በኋላ፡ በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ። ትክክል።

369 ውሃ፡ ደም፡ መንፈስ! ኢየሱስ መጥቶ ይኖርባት ዘንድ ቤተክርስቲያንን ሊያጥብ፡ ሊያነጻ፡ እና ሊቀድስ መጣ። በገዛ ደሙ፡ ከጾታዊ መወለድ ያነጻን ዘንድ፡ ከእግዚአብሔር-የተወለደው የገዛ ደሙን ሰጠ፡ እርሱ ራሱ ይገባበት ዘንድ፡ የተቀደሰ ቅዱስ ዕቃን ሰጠን።

370 "ጥቂት ጊዜ አለ፡ ከዚህም በኋላ ዓለም አያየኝም፡ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ ምክንያቱ እኔ፡" የግል ተውላጠ ስም፡ "እኔ እስከ ፍጻሜ ድረስ፡ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡ በውስጣችሁም እኖራለሁ።" አሜን። "በሁሉም መንገድ፡ እኔ ከእናንተ እና ከእናንተ ጋር እሆናለሁ። እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ። ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል።" እግዚአብሔር በቤተክርስቲያን! ኦህ፡ ማይ! አምላክነት! "በሰማያት የሚመሰክሩ ሶስት ናቸው፡ አባት፡ ቃል (ልጅ)፡ መንፈስ ቅዱስ። አንድ ናቸው።"

371 እንግዲህ፡ ሳትቀደሱ በፊት ልትድኑም ትችላላችሁ። ተቀድሳችሁም ገና መንፈስ ቅዱስ ላይኖራችሁ ይችላል፡ አዎን፡ ገና ሳትሞሉ፡ መንፈሳችሁ ሊቀደስ

ይችላል። ገና በሌላ ነገር ሳትሞሉ፡ ልባችሁ ሊቀደስ ይችላል፡ ሊነጻ ይችላል። ለዚህ ነው እርሱ እንዲህ የተናገረው፡ “ርኩስ መንፈስ ከሰው በወጣ ጊዜ፡ በደረቅ ስፍራ ይሄዳል። ተመልሶ መጥቶ፡ ቤቱን አጊጦ አገኘውና፡ ገባ። ብዙ ጊዜ የዚያ ሰው መጨረሻው፡ ሰባት እጥፍ ይሆናል፡ ከመጀመሪያው የከፋ ነው።”

372 በእናንተ ፒልግሪም ሆሊነሶች፡ ናዝሪኖች፡ እና ሌሎቻችሁ ላይ የደረሰው ይኸው ነው። ተቀብላችኋል። መንፈስ ቅዱስም መጥቶ፡ በልሳኖች መናገር ሲጀምር፡ ምልክትና ድንቅንም ሲሰጥ ግን፡ “ዲያብሎስ” ትሉታላችሁ፡ የእግዚአብሔርንም ስራ ትሳደባላችሁ “ርኩስ ነገር” ትላላችሁ። ቤተ ክርስትያናችሁ ወዴት እንደተወሰደች አይታያችሁምን? ከመካከልዋ ውጡ! ጊዜው ደርሷል፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ተምረነዋል፡ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ እና በመገለጫው ኃይል ተገለጠ። ኣሜን። የቤዛነት ቀን ቀርቧል።

373 አሁን፡ አምላክነት በእርሱ ዘንድ፡ አንደኛ ጢሞቴዎስ 3፡16።

> **... እግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፡ እግዚአብሔር በሥጋ ተገልጦአልና፡... ለመላእክት የታየ፡... በዓለም ታምኖ፡ ወደ ክብር አረገ።**

374 ኦህ፡ እንዲህ እያለ ይሄዳል ይሄዳል ይቀጥላል። አሁን ግን ምን ላይ ደርሰናል? ኦህ፡ በ 8ኛው ቁጥር መጨረሻ።

375 ዛሬ ማታ—9ኛው ቁጥር እንጀምራለን፡ **የፍጥሞ ራዕይ**። ኦህ፡ በጎተራው ትልቅ ነገር ተዘጋጅቶልናል። ትወዱታላችሁ?

> እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ
> ቀድሞ ስለወደደኝ
> መዳኔንም ገዛሁ
> በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

376 ትክክል ፈጽማችሁታል? እግዚአብሔር ለእናንተ ራሱን አሳወቀን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ፡ ኃጢአትን እንዲያስወግድ፡ እግዚአብሔር በሥጋ እንደተገለጠ ተረዳችሁን? በእነዚህ የመጨረሻ ቀናት በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ራሱን እየገለጠ ነው፡ ራሱንም እያሳወቀ ነው።

377 አሁን፡ በዚህ መልዕክት መጨረሻ ላይ፡ አሁን በቤተ ክርስትያን እየተከናወኑ ያሉትን ነገሮች፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ ይሆናሉ ያላቸውን ነገሮች፡ ልክ እንደተባለው ካልተፈጸሙ እዩና መርምሩ። በኤፌሶን ዘመን፣ በጴርጋሞስ፣ ትያጥሮን፣ እስከ ታች ድረስ፡ በሁሉም ዘመናት፡ እንደተባለ ካልሆነ እዩት።

378 ሉተር እንዴት እንደሚሰራ፡ እና ዌስሊ እንዴት እንደሚሰራ ተነግሯል። እና የጴንጤቆስጤ የኃይማኖት ተቋም ወደ ሎዶቅያ፡ ለብ ወዳለ ሁኔታ እንዴት እንደምትሄደ ተነግሯል፡ በዚያ መካከል፡ ግን፡ ሕዝቡን ያወጣል። ልክ ነው። በትክክል። በፍጻሜው ላይ ነው። አቤት፡ ደስ ብሎኛል! እና፡ ኦህ፡ እኔም እራሴ ማርጀቴን እንዳየሁ ሁሉ፡ ጓደኞቼን እና ሌሎቹን ተመልከቱ፡ ዓለም እና—የገባችበትን ማጥ እዩት፡ ከዛ በኋላ የጌታን መምጣት በደጅ እንደቀረበ አስቡ። እኛ በዘመኑ መጨረሻ ላይ ነን።

379 የሰው ልብ በፍርኃት ወድቋል። በየቦታው፡ ሁሉም ሰው፡ በሬዲዮ ላይ ተዘጋጅ፡ እየተነገረው ነው፡ “በአየር ድብደባው ዝግጁ ይሁኑ። **ይህንን** ያዙ፡ **ያንን** ያዙ፡ እና ወደ ምድር ቤት ውረዱ።” ከዚያ እንዴት ትደበቃላችሁ? ከዚያ መደበቅ አይቻልም። ያ'ኮ፡ ወደ መሬት አንድ መቶ ሐምሳ ፊት ድረስ ይዘልቃል፡ አንድ መቶ ሐምሳ ሰኰር ማይልስ፡ ይዘረጋል። ማለት፡ የዚህ መደምደሚያው... ለምሳሌ እዚህ ከመታ፡ እስከ ኢንዲያና ፖሊስ ድረስ ይደርሳል ማለት ነው። ለምን፡ እዚህ ሎስቪል ውስጥ ያረፈው፡ ኢንዲያናፖሊስን ወደ ቁርጥራጮች ይቀይራታል፡ አያችሁ፡ አንዱ ብቻ። ከዚያ በሰተጀርባ የያዙትን ለመናገር ይከብዳል።

380 እናም፡ ተመልከቱ፡ ታውቃላችሁ... ሩሲያ ይህንን ማድረግ አይጠበቅባትም፡ ይህን እወቁ። ኩባ ልታደርገው ትችላለች። ይህች ትንሽ ቦታ፡ የአልካትራዝ ያህል ሰፋት ያላት—ትንሽ አገር፡ ይህን ልታደርገው ትችላለች፡ ዓለምን ሁሉ መሸፈን ትችላለች። ማድረግ የሚጠበቅባችሁ እንዲህ ወድራችሁ አንዲት ገመድ መሳብ ብቻ ነው። ሰራዊት አያስፈልጋችሁም። ይህን ለመፈጸም፡ በዲያብሎስ እጅ ያለ አንድ አክራሪ ሰው ብቻ ያስፈልጋል። በትክክል ትክክል ነው። ሊያደርግ ይችላል፡ ከዛ በኋላ ነገር ሁሉ ያበቃለታል። ሁሉም ያበቃል።

381 ኦህ፡ ግን እሰኪ፡ ይህን የተባረከውን ነገር ልሰጣችሁ። ያንን ለመፈጸም ቀርቦ ሰናየው፡ ከመንጋቱ በፊት መሆን እንደሚችል በምናየው ጊዜ። አስታውሱ፡ ያንን ከመፈጸሙ በፊት ቤተ ክርስትያን ወደ ቤቷ ገብታለች። ንጥቀቱ ቀድሞ ተፈጽሟል።

382 አሁን፡ እናንተም እንዳትስቱ፡ አስታውሱ፡ ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ “በኖኅ ዘመን እንደነበረ፡ በሎጥ ዘመን እንደነበረ።” አስታውሱ፡ ዝናብ ገና ሳይዘንብ፡ ኖኅ መርከቡ ውስጥ ነበር። አያችሁ? ኖህ በመርከቡ ውስጥ ነበር። በዚህ በኩል፡ አወሰደ። አሁንም፡ ኖህ የአይሁድ ጥላ ነበር። ሄኖክ ግን ሳይሞት ወደ ቤት ተወሰዷል። ኖኅም ሄኖክን ሲሄድ ባየው ጊዜ፡ ጊዜው እንደደረሰ አውቆ፡ መርከብ ጀመረ። እውነት ነው። ሄኖክ ወደ ቤቱ ሲሄድ፡ የኖህ ምልክት ያ ነበር። የአህዛብ ቤተክርስቲያን እንደተወሰደች፡ ያን ጊዜ እራሱን ለእስራኤል ያሳውቃል። አያችሁ? ትክክል ነው።

383 አስታውሱ፡ በሎጥ ዘመን፡ ኢየሱስ እንደተናገረው፡ አንድም የእሳት ቅንጣት ምድር ላይ ከመውደቁ በፊት፡ መልአኩ እንዲህ አለው፡ “ከዚህ እስክትወጣ ድረስ ምንም ማድረግ አልችልምና፡ ከዚህ ውጣ። ፍጠን። ፍጠን።” እሳት ከመውረዱ በፊት ሎጥ እና ቤተሰቡ ወጥተው ሄደዋል። ስለዚህ፡ መከራው ከመጀመሩ በፊት መነጠቅ ይሆናል።

384 መከራውን በተመለከተ፡ ብዙ ሰዎች ይደባልቁታል። በዚህ ሳምንት፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ በጌታ እርዳታ እናስተካክለዋለን። አስታውሱ፡ ታላቁን የመከራውን ጊዜ እየጠበቃችሁ ናችሁ፡ ያ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ በጥላ ማየት ከፈለጋችሁ፡ ያ ያእቆብ የተቸገረበት፡ የመከራው ዘመን ነበር። ያ ከአህዛብ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። አሕዛብ ከዚያ ጋር ምንም አይገናኙም። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚያ ምንም ጥላ የለውም። የአሕዛብ ቤተ ክርስትያን ተነጥቃለች።

385 እናንተ ገና “ውኃ ወደ ደም እንዲቀየር፡” ወዘተረፈ ትጠብቃላችሁ። ይህም ሙሴና ኤልያስ፡ እንደገና ወደ እስራኤላውያን ሲመለሱ፡ የሚመጣ ነው።

ኤልያስ፡ ለአራተኛ ጊዜ፡ በመንፈስ ተመልሶ መጥቷል። ከእነዚህ ውስጥ አንዳቸውም አልሞቱም፡ ወይስ፡ ሙሴ ሞተ፡ የት እንደቀበሩት እንኳን አያውቁም። ያኔ እና በዚያ መካከል ለመነሣት በሆነ አድማስ ታስሮ ቆየ፡ ምክንያቱ፡ በደብረ ታቦር ተራራ፡ በዚያ፡ ኢየሱስን እያነጋገረ ነበር፡ አይደል? አያችሁ?

386 ስለዚህ ተመልሰው መጥተው፡ በመንፈሳዊ ጎዳና "ሶዶም" ተብላ በምትጠራ ይገደላሉ፡ ጌታችን የተሰቀለባት፡ ኢየሩሳሌም። ለአይሁዶች ይሰብካሉ፡ ምድርንም ይመታሉ፡ ሰማያትንም ይዘጋሉ፡ እና የመሳሰሉትን ያደርጋሉ። የአሕዛብም አገልግሎት ይፈጸማል ከዚህም ጋር ይገናኛል፡ አሕዛብም ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ፡ ያ አገልግሎትም ይቀጥላል። የነገር ሁሉ ጥፋት ይሆናል። የምድር ሁለት-ሦስተኛው ይወድማል፡ እና ሁሉም ነገር ይሆናል። አስከሬናቸው በጎዳና ላይ፡ ሶስት ቀን በተኛ ጊዜ፡ ምን አይነት እንደሆነ እዩት።

387 ከደቡብ አሜሪካ ያገኘኋቸውን ሥዕሎችን ተመልከቷቸው፡ ያ የጴንጤቆስጤ ሚስዮናዊ በገደሉት ጊዜ፡ ሚስቱ፡ እሱን እና ሁለት ትንንሽ ልጆችን፡ ጎዳናው ላይ ገድለው ዘረሯቸው። ትንሿ ልጃቸው፡ ሆዷ **እንዲህ** አብጦ ነበር። መቅበር እንኳን አልወደዱም። በአጠገባቸው እያለፉ፡ ለሶስት አራት ቀን ያህል፡ እየተፋባቸው ያልፋሉ። ፎቶውን ያነሣው ወንድም ኮፕ ነው። እቤት ውስጥ ይዤዋለ፡ የሚያደርጉትን፡ አያችሁ።

388 ከዚያም አንዱ ሌላውን ሰጦታ ይሰጣል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጥላ እንዴት እንደሚገለጽ ተመልከቱ፡ የትኛዋ ቤተክርስትያን እንደምትፈጽመው ተመልከቱ። ልክ ነው፡ በደጅ ነው፡ አሁን እንደ እባብ ወዲያ ወዲህ እያለች ናት፡ የነገሮች ምልክቶች፡ አሁን በተንኮል እየታዩ ናቸው።

389 ጌታ በ 33 ላይ የሰጠኝን ትንቢት፡ እንዴት እንደሚሆን ጠብቁ፡ "ሴቶች እንዲመርጡ ይፈቀድላቸዋል። በምርጫ ወቅት፡ የተሳሳተ ሰው ይመርጣሉ።" ሰባት ነገሮች ተነግረዋል፡ አምስቱም ተፈጽመዋል። የሚቀጥለው ነገር ታላቅ ሴት፡ ቤተ ክርስቲያን፡ አንድ ኃይል ወይም የሆነ ነገር፡ ዩናይትድ ስቴትስን ይቆጣጠራታል፡ ይገዛታል። ከዚያም ልክ እንደ አመድ፡ ተበታትና፡ መጨረሻዋ የሚሆንበት ቦታ አየሁት። የመጨረሻው ጊዜ ነበር።

390 "በራሷ የምትሄድ መኪና ይሰራሉ። ሹፌር አያስፈልጋቸውም፡" ተብለዋል። አሁን አሟልተውታል። አሥራ አንድ ዓመት፡ ይባላል...

391 መንፈስ ቅዱስ ለእኔ የነገረኝ። ጋዜጣው ላይ ነው። የማይካድ... ነገር ነው። መንፈስ ቅዱስ እንዳለው፡ ጋዜጣ ላይ ወጥቷል።

392 የማጂኖት ላይን ከመገንባቱ ከ11 ዓመታት በፊት፡ አልኩኝም፡ "ጀርመናውያን... አሜሪካ... ፕሬዚደንት ሩዝቬልት ከሌሎች ሁሉ ይልቅ የከፋ ይሆናል ብዬ ነበር።" እናም እንዲሁ ነበርና። ትክክል ነው።

393 እናንተ ዲሞክራቶችን ለመንካት አይደለም፡ ነገር ግን—ነገርኳችሁ። አሁን ዲሞክራትም ሪፓብሊካንም አይደለምና። እየተናገርን ያለነው ስለ እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እኔ ዲሞክራት ወይም ሪፐብሊካን አይደለሁም። ክርስቲያን ነኝ። ስለዚህ፡ እነሱ፡ ምንም ይሁኑ፡ ብቻ ያኔ አስተውሉ።

394 እንደው በቀደም ለት፡ ምን አይነት የክህደት ሰብሰብ መሆናቸውን ለማየት ከፈለጋችሁ፡ እዚህ ተመልከቱ። እነዚያን ማሽኖች ወሰደው አስተካከሏቸውና፡ ለአቶ ኒክሰን፡ በመረጣችሁ ቁጥር፡ ለሌላኛው ሰው በተመሳሳይ ጊዜ፡ ትመርጣላችሁ። ኤድ... ጄ። ኤጋር ሁቨር ማሽኖቹን ጎትቶ አወጣቸው። ሰንቶቻችሁ አነበባችሁት? እንዴ፡ አዎን፡ በየጋዜጣው፡ በየዜና ሁሉ፡ እየተሰራጨ ይገኛል። የት እንደደረሰን ተመልከቱ?

395 ከክርስቶስ በቀር ምንም ቅን ነገር የለም። ኣሜን። አቤት፡ ይህ የተባረከው ጥንታዊው መጽሐፍ! በቃ። ማን እንደሆንክ፡ ከየት እንደመጣህ፡ እና የት እንደምትሄድ የሚነግርህ እሱ ብቻ ነው (አዎን፡ ወዳጄ።)፡ የተባረከው ጥንታዊው መጽሐፍ ይህ ነው፡ ኦህ፡ እንድወደው ያደረገኝ። እናንተንስ?

> እምነት በአባት፡ እምነት በልጅ ላይ፡
> እምነት በመንፈስ ቅዱስ፡ ሦስቱም አንድ ላይ፡
> አጋንንት ይንቀጠቀጣሉ፡ ኃጢአተኞችም ይነቃሉ፡
> ጆሆቫን በማመንህ ሌሎች ይንቀጠቀጣሉ።

396 ኣሜን። ወዳጆች ሆይ፡ በፊታችን ያለው እንዴት ያለ ታላቅ ቀን ነው! "እግዚአብሔር ለመልአኩ የሰጠው የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ፡ እርሱም መጥቶ ለዮሐንስ አመለከተው፡ በጎተራው ለእኛ የያዘልን ነገር፡ በቤተክርስቲያን ዘመን ይታወቅ ዘንድ ነው።"

397 በእግራችን እየቆምን፡ አሁን ጌታ ይባርከን። እና ፒያኖ የሚጫወተው፡ ከቻልክ **የኢየሱስ ሰም ከአንተ ጋር ውሰድ**፡ የሚለውን ትንሽ ኮርድ ሰጠን።

398 አሁን አዳምጡ። ዛሬ ጠዋት፡ በጉባኤው ውስጥ፡ እንግዶች እንዳሉ ምንም ጥርጥር የለውም። እጃቸውን እንድትጨብጡ እፈልጋለሁ። ጋብዟቸው፡ ሌላም፡ ከእናንተ ጋር ወደ ቤት ይሂዱ። ሰውን ሁሉ ተቀበሏቸው። ሁላችሁ ይህን ማድረጋችሁ እርግጠኛ እንድትሆኑ እፈልጋለሁ።

399 አገልግሎቱ፡ ዛሬ ማታ በሰባት ሰአት እንደሚጀምር አስታውሱ። በሰባት ሰዓት-ተኩል፡ **የፍጥሞ ራዕይን** እሰብካለሁ። ነገ ምሽት፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ ሰለ መጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ ሰለ ኤፌሶን በቤተክርስቲያን ዘመን፡ እሰብካለሁ።

400 **የኢየሱስ ሰም ከአንተ ጋር ውሰድ** እያልን፡ የትንሿ ጉባኤያችን መሰናበቻ መዝሙር እንዘምራለን። ሁላችንም እንዘምር። በጣም ጥሩ።

> የኢየሱስን ሰም ከአንተ ጋር ውሰድ፡
> የሀዘንና የዋይታ ልጅ፡
> ደስታ እና ምቾት ይሰጣል፡
> በሄዳችሁበት አትለዩት።
>
> ውድ ሰም፡ ኦ ድንቅ ሰም!
> የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
> ውድ ሰም፡ (ውድ ሰም!) ኦ ድንቅ ሰም!
> የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

401 አሁን የሚቀጥለውን አዝማች ከመዘመራችን በፊት፡ ሜቶዲስት፣ ባፕቲስቶች፣ ጴንጤቆስጤሎች፣ ካቶሊኮች፣ ናዝሪን፣ ፒልግሪም ሆሊነስ፣

አጠገባችሁ ያለውን ሁሉ፡ ፊታችሁ ያለውን ሰው ጋር ተጨባበጡ፡ ከጎናችሁ፡ ከኋላችሁም ያሉትን፡ እንዲህ በሏቸው፡ "ክርስትያን ፒሊግሪም፡ ወዳጄ፡ ዛሬ ጠዋት እዚህ ስላየሁህ ደስ ብሎኛል። በእግዚአብሔር ነገሮች ዙሪያ፡ ከአንተ ጋር ሕብረት በማድረጌ ደስ ብሎኛል። ጥሩ ጊዜ እንዳሳለፍን አውቃለሁ። ዛሬ ማታ እንደገና እዚህ እንደምንገናኝ ተስፋ እናደርጋለሁ።" ከፊታችሁ፡ ከኋላችሁ፡ በዙርያችሁ፡ ካሉት ጋር ስትጨባበጡ፡ እንደዚ ያለ ነገር ተባባሉ።

ለኢየሱስ ሰም ሰገዱ፡ (ወንድም ኔቪል፡ ዛሬ ማታ
እንገናኝ። ዛሬ ማታ እንገናኝ።)
... እግሩ ስር፡
የነገሥታት ንጉሥ፡ በሰማይ፡ ዘውድ እናደርግለታለን፡
ጉዟችን ሲጠናቀቅ።

ኦ ውድ ሰም፡ ኦ ድንቅ ሰም!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ውድ ሰም፣ ኦ ድንቅ ሰም!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

እስክንገናኝ! እስክንገናኝ!
በኢየሱስ እግር ላይ እስክንገናኝ፡ (እስክንገናኝ!)
እስክንገናኝ! እስክንገናኝ!
እንደገና እስክንገናኝ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን!

ራሶቻችንን ዝቅ እያደረግን፡

እስክንገናኝ! እስክንገናኝ!

**የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ** AMH60-1204M

(The Revelation Of Jesus Christ)

**የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ተከታታይ ትምህርት**

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ ታሕሳስ 4፡ 1960፡ እሁድ ጠዋት፡ በዩ.ኤስ.ኤ.፡ጀፈርሰንቪል ኢንዲያና፡ ከሚገኘው ብራንሃም ተበርናክል፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይስ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግስ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2023 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org